# [illegible]

## ክፍል ሦስት

"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦
እረኛ ከአንበሳ አፍ ሁለት እግርን
ወይም
የጆሮን ጫፍ እንደሚያድን፥
እንዲሁ
በሰማርያ በአልጋ ማዕዘን፥
በደማስቆም በምንጣፍ ላይ
የተቀመጡት የእስራኤል ልጆች
ይድናሉ።"

ትንቢተ አሞጽ 3፥12

# 10

# እቴሜቴ ሂደች፣ ረቂቅ መጣች፣ ጥበቡስ?

ለመላው የቀብሪደሃር ሕዝብ ፤ ሐምሌ 17 ቀን 1969 ዓ.ም የድንጋጤ የእልቂትና የታላቅ ጦርነት ቀን ነው። ሲነጋጋ ጀምሮ ሠራዊቱም ሆነ ሕዝቡ ባልጠበቀው ሁኔታ በከባድ መሣሪያ የተደገፈ የለየለት ጦርነት ሶማሊያ በኢትዮጵያ ላይ ከፈተች። ታይቶ በማይታወቅ ሚሳይልና ከርቀት ተምዘግዛጊ መድፍ ቀብሪደሃር ይታረስና ከተማው ይደረማመስ ገባ። ላለፉት ሁለት ወራት በኢትዮጵያ ሠራዊት ታንከና መድፍ ዙሪያዋን በመታጠሯ ሰላም ሰፍኖባት የቆየቺው የቀብሪደሃር ከተማም ሐምሌ 17 ቀን ግን የገሃነም እሳት የሚንቦገቦግባት የዋይታና የጭንቅ ሥፍራ ሆነች። ከደሳሳ ጎጆ እስከ ድንጋይ ቤቶች መሣሪያዎቹ በሚተፉት እሳትና አሸባሪ ድምጽ ተደመሰሱ። ምድር ቀውጢ ሆነች። ድንገት እንደ ደራሽ ማዕበልና ሞገድ ምድሪቱን ባጥለቀለቀው ከባድ የጦር መሣሪያ የብዙ ነዋሪዎች ሕይወት እንደቅጠል ረገፈ። ከተባራሪው መድፍና መሣሪያ በሕይወት ማምለጥ የቻለ የቀብሪደሃር ሕዝብ ነፍሱን ለማዳን ሆስፒታሉ ውስጥ ታጨቀ፤ በዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ሕግ መሠረት ሆስፒታል በጦር መሣሪያ አይደበደብም በሚል እምነት። ቤታችን እዚያው ሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ ቢሆንም ቅሉ ኢያሱም እንደ አባቱና ታላቅ ወንድሙ ከሆነው ከጥበቡ ጋር ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅሎ ያን ማለዳ ሆስፒታሉ ውስጥ ነው። የቁስለኞች ብዛት በእጥፍ ድርብ በጨመረበት በዚህ ቀውጢ ማለዳ ጥበቡ ከሆስፒታል የሕክምና ቡድኖች ጋር በመሯሯጥ በሥቃይና በጣዕር ለሚገኙት ሁሉ እርዳታ በመስጠት ላይ ነው። ቀደም ሲል በዚህ ማለዳ ከጦር ሜዳ ከመጡት ቁስለኞች መሃል ለአንዱ የሕክምና እርዳታ እየሰጠው ሳለ ጥበቡ ስለጦርነቱ ሁኔታ ላቀረበለት ጥያቄ ሲመልስለት "ጦርነቱ ከተማው ጠርዝ ላይ ነው። ጦር ሜዳ ያለው የኢትዮጵያ ሠራዊት መሣሪያ አልቆበት የሚያቀብለው ጠፍቶ በመጠባበቅ ላይ ነው" ብሎ ነበር።

ሶማሊያ እንዲያ የምትርበደበድለት የተፈራውና ዝነኛው የኢትዮጵያ የጦር ኃይል፤ ምን ቢሆን ፤ ምንስ ቢገጥመው ነው ? በጦር ሜዳ ላይ ለሚዋደቀው ሠራዊት ደጀን መሆን የተሳነው ? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የጥበቡ ልብ በዚህ ጥያቄ ተይዞ መቆየት አይችልም። ምክንያቱም የእርሱን እርዳታ የሚፈልጉ በሺ የሚቆጠሩ ስቃይተኞች የሆስፒታሉን ውስጥና ውጪ ሞልተውታልና።

ሐምሌ 17 ቀን ማለዳ ግን ሕዝቡ ሙሾ እንዲያወጣ መርዶ አልተነገረውም እንጂ የብዙዎች አለኝታና ትምክህት የነበረው የኢትዮጵያው የጦር ብርጌድ ትጥቁን የሚያስፈታ ከባድ ገጠመኝ ውስጥ ወድቋል። ከርቀት ዒላማውን ሳይስት አነጣጥሮ በሚያወድም ሚሳይል የሠራዊቱን

የጦር ግምጃ ቤት ሶማሊያ በእሳት አጋይታዋለች። በጦር ሜዳ ለሚዋደቀው ሠራዊት የጦር መሣሪያ ለመላክም ሆነ ደጀን ለመሆን ያልቻለውም ለዚህ ነበር። ሠራዊቱ እንዳለ ለሶማሊያ ጦር እጁን ላለመስጠት ያለው አንድና ብቸኛ መንገድ ጓዙን ባስቸኳይ ጠቅልሎ መሸሽ ነው። እለኝታውንና ትምክህቱን በዚህ ሠራዊት ላይ ያደረገው ምስኪኑ የቀብሪደሃር ሕዝብ ግን ከፊሉ እንደ ቅጠል ረገፈ። ከፊሉም እጅና እግሩን ይዞ ከአሁን አሁን የኢትዮጵያ ጦር ምድረ ሱማሌን እንደምናምን አድርገና ድል ነስቶ፤ ሞቴን ይቀድምልኛል፤ አሁን ይደርስልኛል፤ በማለት እየጨላለመ በሄደው ተስፋው ላይ ብርሃን ሊፈነጥቅ ከራሱ ጋር ይታገላል። ጀሮቹ በቅርበት የሚሰሙትን አስደንጋጭ የጦር መሣሪያ ፍንዳታዎችም ሆነ ዓይኖቹ ማየት የጀመሩትን ጠረኞች ከራሱ ወገን አድርጎ ቆጥሯቸዋል። እሱን ከሞት ለመከላከል የኢትዮጵያው የጦር ኃይል የሚያደርግለትም ፍልሚያ መስሎታል። "ጀግና" የተባለው የኢትዮጵያው ጦር ግን በብዙ ሺህ የሚቆጠረውን የቀብሪደሃር ሕዝብ ለአሰቃቂ ሞትና ምርኮኝነት አጋልጦ ራሱን ለማዳን ፈርጥጧል።

የሚቋቋመው ኃይል የከበለለት የሶማሌው ጦር ሠራዊት በከባድ መድፍና መሣሪያ እየታገዘ ከተማይቱን ከገለባበጣት ወዲያ ዒላማውን ወደ ሆስፒታሉ ሲያነጣጥር የዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ሕግ እንኳን አላገደውም። በጣሊያን ጊዜ በከባድና በጠንካራ አርማታ የተገነባው የሆስፒታሉ ጣሪያና አንዱ የማዋለጃ ክፍል ተደረማመሰ። በውስጡና በአካባቢው የነበሩ ጤነኞችም ሆኑ በሽተኞች በአሰቃቂ እልቂት አለቁ። እንደተቆጡ ዝሆኖችና አውራሪስ ምሕረት እንደማያውቁ የተራቡ የዱር አራዊት የሶማሌ የጦር ታንኮች እየደነፉ በጭካኔ ወደ ሆስፒታሉ ገሰገሱ። እተርፋለሁ ብሎ ሆስፒታል ቅጥር ግቢ የተሰገሰገው ሕዝብ፥ ከሞት የተረፈው ቁስለኛና ሆስፒታል የከረመው የአልጋ ቁራኛ፥ ነፍስ ጡር ሴቶች፥ እርጥብ አራሶች ከነህጻናቶቻቸው፥ በዚህ እልቂትና ሽብር መሃል እናት አባታቸው የተገደሉባቸው የሙት ልጆች፣ በምርኩዝ የሚሄዱ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች፥ ጥበቡና መላው የሆስፒታል የሥራ ባልደረቦቹ፤ ባጠቃላይ ከሞት የተረፋትና በሕይወት ያሉ ሰዎች ሁሉ፤ እንደ አስፈሪ ነጎድጓድ በሚያስገመግሙት የሶማሊያ ታንኮችና ወታደሮች ተከበቡ። ወዲያውኑ የተከበበውን ያን ሕዝብ እጁን በራሱ ላይ እያደረገ ወደ ሜዳ እንዲወጣ ባለድሎቹ ሶማሌዎች በዕብሪትና በማመነጫጨቅ አዘዙት። ጦር አንስቶ ያልገጠመው የቀብሪደሃር ሲቪል ሕዝብ ከዓለም አቀፍ ሕግ ውጪ የሶማሌ መንግሥት ምርኮኛ ሆነ። ውዴ ጥበቡ ኃይለ ሥላሴ፤ እስከመጨረሻው ሰዓት ሕዝቡን በኦጋዴን ማገልገሉ ሳይበቃው፤ በምርኮኝነቱም ሊያገለግልና የክርስቶስን ፍቅር ሊያሳይ ወሰነ።

ሐምሌ 17 ቀን 1969 ዓ.ም. እኔ ሁለተኛ ልጃችንን በሚደንቅ ሁኔታ የወለድኩባት ቀን የደስታ ቀን፤ እያቴ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየችባት የኃዘን ቀን። ሆኖም ከገሃነም አምልጣ ወዳምላከዋ ጉያ በመግባቷ ደግሞ የደስታ ቀን ነው። ካለሁበት ወዲያ ማዶ በሺ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ለነበረው የቀብሪደሃር ሕዝብ ደግሞ የሞትና የእልቂት፥ የዋይታና የልቅሶ ቀን ነው። አዎን! ይህ ቀን የኃዘን ቀን ነው። ላናየውና ላያየን ከአገር ከወገን ተነጥሎ የኔ ውድ የእግዚአብሔር ሰው ጥበቡ ኃይለ ሥላሴም በምርኮኝነትና በግፍ የተወሰደበት የመራራና የለቅሶ ቀን ነው።

በግማሽ ቀን ውስጥ ጦርነቱ አከተመ። ምርጫ ቢሰጠው ኖሮ ሞቱን ይመርጥ የነበረው ኩሩው የኢትዮጵያ ሕዝብም ከሶማሊ እጅ የመትረፍ ተስፋውም አብሮ አከተመ። ሶማሌዎቹ ጠመንጃዎቻቸውን በምርኮኞቹ ላይ በመደቀን ለመግደል እያስፈራሩ የስድብና የቁጣ ናዳቸውን ያወርዱት ገቡ። ከማረኩዋቸውም ላይ ሰዓቶችን የወርቅ ቀለበቶች ያንገት ሃብሎች መዝረፍና መግፈፍ ጀመሩ። አንድ በመከከለኛ ዕድሜ የሚገኙ ሰው በዚህ መሃል የማምለጥ ሙከራ ሲያደርጉ ርህራሄ

ከማያውቁት የሶማሌ ወታደሮች በተለቀቀባቸው ጥይት ተመትተው መራራውን የሞት ጽዋ የተቀበሉት በዚያው ቅጽበት ነበር።

****

*". . ጉዞው ወዴት?"*

በዘረፋውና በድንፋታው መሃል ቀበሪ ደሃርን በቁጥጥሩ ስር ያዋለው የሶማሌው ጦር መሪ ሻለቃ አሊ ድንገት ወደ ሜዳው ብቅ አለ። ሻለቃ አሊ ዕድሜው በ30ዎቹ ውስጥ የሚሆን ጠ.ማምና መጠነኛ ቁመት ያለው፤ አማርኛ አቀላጥፎ ሲናገር ከአማራዎቹ ዝርያ የተወለደ የሚመስል ግን ፍጹም ሶማሌ ነው። "በሕይወት ስላተረፍናችሁ ደስ ይበላችሁ፤ አሁን ግን ባስቸኳይ ከዚህ ሥፍራ ካላሸሽናችሁ የኢትዮጵያ ጦር ኃይል መጥቶ አካባቢውን በቦንብ ስለሚደበድበው ሆስፒታሉ መጠለያ ሊሆናችሁ ፈጽሞ አይችልም" ሲል ለተማረከው ሕዝብ ደህንነት ተቆርቋሪ መሳይ ሃሳቡን አቀረበና ወዲያው ምርኮኛው ባስቸኳይ ስፍራውን እንዲለቅ ትእዛዝ ሰጠ። አፍታም ሳይቆይ በቁጣና በስድብ በሚደነፉ የሱማሌ ወታደሮች እየተነዳ የቀብሪደሃር ሕዝብ በከተማው ፍርስራሽ መሃል በግፍ እንዲጓዝ ተገደደ።

ነገር ግን ጉዞው ወዴትና የጉዞውም ፍጻሜ ምን እንደሚሆን ፤ ማንም መለ መምታት አልቻለም። ሆኖም ግን ሕዝቡ ሞት እንዳጠላበት ለመታረድ እንደሚነዳ በግ ፊት ለፊቱ ወደ ተደቀነው የጨለማና የመከራ ዘመን በሰልፍ ተነዳ። ሱማሌዎቹ በጠና የታመሙትንና መንቀሳቀስ የማይችሉትን በሽተኞች በቃሬዛ እንስቶ የመውሰድ አሳቡም አልነበራቸውም ። ሰው አልባ ሆና በቀረችው ፍርስራሽ ከተማ እስከፊ ሞታቸውን እንዲጠባበቁ ጥለዋቸው ሄዱ እንጂ። ምርኮኛ ያደረጉትትን ያን መከረኛ ሕዝብ ግን እያመናጨቁ እያዳፉና እያቻኮሉ ከከተማው ወጣ ብሎ ወደሚገኘው ጫካ ይዘዋቸው ነጎዱ። ከዚያም በትላልቅ የጭነት መኪናዎች እየጠቀጠቁ ሶማሌዎቹ ለረገርም ጊዜ ሲቆጣጠሩት ወደነበረና በሚገርም ሁኔታ ወደ ተደራጁበት የጦር ሰፈር ወሰዷቸው።

የመሣሪያ ከምችታቸውንና በዚያ ቦታ በስፋት የተጠናከረውን የጦር ኃይላቸውን ያየው ምርኮኛ ሕዝብ ሶማሌዎቹ የነበራቸውን ታላቅ ዝግጅትና በጊዜው የአሸናፊነታቸውን ምሥጢር ተመለከተ። የምርኮኞቹ ጉዞ ግን ከዚያም ወዲያ ቀጥሎ ወደማታ ኤል ሃር የምትባል ከተማ ሲደርሱ አዳር ከዚያ እንዲሆን አውላላ ሜዳ ላይ ካምፕ ተደረገ።

አክራሪ እስላሞችም ከምርኮኞቹ መሃል አንዱን ጠርተው የመሃመድና የአላህ ተከታይ መሆን አለመሆኑን ምርመራ የማካሄድ "የእይጥና የድመት" ዓይነት አስከፊ ጨዋታ በዚያን ምሽት ጀመሩ። ለምርመራ የተጠራው ምርኮኛ ክርስቲያን መሆኑን ካወቁ ፍርድና ብያኔው ወዲያው ይፈጸማል። ክርስቲያኑን ምርኮኛ መሬት ለመሬት እባራ ላባራ እየጎተቱ ከሕዝቡ መሃል ይወስዱታል። ደቂቃም ሳይቆይ የሚሰማው የተኩስ ድምጽ በዚያ ምስኪን ሰው ላይ የተወሰደበትን የሞት እርምጃ ገሃድ ያደርገዋል። የሰማዩን ለእግዜር ትተን በምድር የሚጠብቀው መከራና ሥቃይ ከወዲሁ ተቀጨለት እንበል ይሆን!

በጨለማው ውስጥ ምርኮኞቹን የሚጠብቋቸው ጋርዶች በተደጋጋሚ ያሰሙት የተኩስ ድምጽ ቁልጭ ያለ መልእክት አስተላልፏል። ምርኮኛው ልውስና ትንፍሽ ማለት የለበትም። የሚያደርገው ማንኛውም ዓይነት እንቅስቃሴ ሞት ያስከትላል። ስለዚህም ቋንቋ ሊገልጸው የማይችል ሁለንተናን ሽባ የሚያደርግ ታላቅ ፍርሃት በሕዝቡ ላይ ወድቋል። እነዚህ ደም የተጠሙ ወታደሮች ምክንያት እንዳይፈልጉባቸው ምርኮኞቹ ትንፋሻቸውን እንኳን ላለማሰማት እስኪጥሩ ተጨነቁ።

የኔ ውድ ጥበቡ፤ የሞት ያህል ስለደከመው በዚህ ሁሉ አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ እንቅልፍ ጥሎታል። ያን ዕለት ከጠዋት እስከማታ በእሱና በሕዝቡ ላይ የደረሰባቸውንና ያለፋበትን ሁሉ የማገናዘብ ጉልበቱ አልቋል። በሰሞኑ ሁሉ ለሰዓታት ያለማቋረጥ ሕዝቡን ያገለገለበት ሰውነቱ አሁን ዝሏል። ልቡ ግን አንድ ነገር አረጋግጦለታል። ቀኝና ግራውን ለማያውቀው ምስኪን የቀብሪደሃር ሕዝብ እግዚአብሔር በእርግጥ ይገደዋል። የጥበቡ ሁለንተና የሚታመንበት የጌታ የእግዚአብሔር የጥበቃ፥ የምሕረትና የፍቅር ዓይኖችም በእርሱና በኢያሱ ላይ ናቸው። በዚህ የሕይወቱ ዋስትና ላይ ተንተርሶ በሚገርም ዓይነት ጥልቅ እንቅልፍ ተወስዷል።

እንዳይነጋ የለምና ያም የመከራ ሌሊት አልፎ ፀሐይ ብርሃንዋን ፈነጠቀች። በደም ጥማተኞቹና በነፍሰ ገዳዮቹም ላይ ፀሐይ ብርሃንዋን ፈነጠቀች። ከምርኮኞቹ መሃል እየተነጠሉ በግፍ ተገድለው ጫካ በተጣሉት ሬሳዎችም ላይ። እንዲሁም መከራና ፍዳ በታቀደላቸው እስረኞችም ላይ ፀሐይ ብርሃንዋን ፈነጠቀች።ፀሐይ በዚህ ሁሉ ላይ እኩል ብርሃንዋን መስጠትዋ ፤ ጦር ሳይመዝ የተማረከው ሕዝብና የተቀበለው መከራ፤ በግፍ የተገደሉት ምስኪናች ደም ዘግንኗት፤ ፀሐይ ብርሃኗን ላለመስጠት አለመቆሟና ሕይወት እንደወትሮው ሊቀጥል መንጋቱ ያሳዝናል።

****

*የጫካው ክሊኒክ!*

ሲነጋ ጥበቡን ከሕዝቡ ለይተው በመኪና በአቅራቢያው ወደምትገኝ ዋቤ ወደምትባል መንደር ወሰዱት። እዚያ ወደ ደኑ ውስጥ ገባ ብሎ ሶማሌዎቹ በሚገርም ሁኔታ ያዘጋጁት ትልቅ የጫካ ክሊኒክ አለ። በደንብ የተደራጀና የተሟላ ክሊኒክ። በጦርነቱ ለሚቆስሉትና ለሚታመሙት ወታደሮች ሕክምና የሚሰጥበት ነው። ክሊኒኩ በጫካዎች መሃል የተሰራ ስለሆነ የዛፎቹ ቅርንጫፎችና ቅጠሎች ከቀን ፀሐይም ሆነ ከዝናብ መጠለያ ሆነውታል። ቁስለኞቹ ሕክምና የሚደረግላቸውና የሚተኙት ግን መሬት ላይ ነው።

ጥበቡ ከመኪና እንደወረደ የተቀበሉት ሙክታር እና ኑር የተሰኙ ሁለት የሱማሌ ሐኪሞች ናቸው። እዚህ ክሊኒክ ውስጥ ይሠራሉ። ጥበቡን ወንበር ሳብ አድርገው አስቀመጡትና "እንግዲህ ያንተ ሥራ ቁስለኛ ወታደሮችን ማከም ይሆናል" ብለውታል። ሻይ እየጠጡም ኢትዮጵያዊው ዶክተር የምርኮኝነት ጦስ እንዴት እንዳገኘው ቤተሰቡስ ወዴት እንደሆነ ጠየቁት። "መቼም ልጅህና ነፍሰ ጡር ሚስትህ አዲስ አበባ በመሆናቸው ደስ ሊልህ ይገባል። ግን እኮ አንተም እዚያው ከነርሱ ጋር ብትቀር ይሻልህ ነበር እንዲህ ለመሰለ አደጋ ራስህን ከማጋለጥ" አለው ዶ/ር ኑር። በኑር ውስጥ የሰብአዊነትና የርህራሄ ስሜት ጥበቡ አየ። ሌላኛው ሐኪም ዶ/ር ሙክታር ደግሞ ቀበል አድርጎ በመቀጠል እኛ ልንለቅህ እንችል ነበር ግን ጦርነት ጦርነት ነው ምን ይደረጋል። እዚህ ቁስለኞቹንና የጦር ጉዳተኞችን ማከሙ እምብዛም ያለ ሥራ አያስቀምጥህም። ትልቅ የሐኪም እጥረት አለብን አለ ሙክታር። ጥበቡ የሐኪሞቹ አስተሳሰብ ደስ አለው። ኢትዮጵያዊ ሆነ ሶማሊያዊ የሐኪም ሥራ ሰው ማዳን ነው። ነፍስን ማትረፍ ነው። ወታደሮች በጦር መሣሪያዎች የሰባበሯቸውን አጥንቶች ሐኪሞች ይጠግናሉ።

የጥበቡና የሁለቱ ሐኪሞች የሻይ ጊዜ አበቃ። ቁስላቸውና ስብራታቸው እንዲጠገንላቸው የሚጠባበቁ ብዙዎች ነበሩ። ጥበቡ ቀኑን ሙሉ ባልተቋረጠ ሥራ ብዛት ሰውነቱ በድካም እጅግ ዝሏል።

እንዲያ በድካም የዛለው የጥበቡ ሰውነት ግን ያን ምሽት በእንቅልፍ መደሰል አልቻለም።

በምድር ላይ በጀርባው ተንጋሎ እንደጣሪያ ከበላዩ የተጋረጡትን የዛፍ ቅርንጫፎች እያየ ድካም እንኳን ያልረታቸው ዓይኖቹ ያለአንዳች እንቅልፍ ፈጠዋል። በተወዳጁ ሐኪም ላይ የደረሰው አሳዛኝ ገጠመኝ አንጀቱን የበላው አንድ የቀብሪደሃሩ ሆስፒታል ልብስ ሰፊ የነበረ ሶማሌያዊ ያን ዕለት የሚገርም ቸርነት ለጥበቡ አድርጎለት ነበር። ፍየል አርዶ ሩዝ ቀቅሎ ምግብ በትልቅ ትሬ አዘጋጅቶ ከግመል ወተት እርጎ ጋር እንዲሁም ለሌሊቱ ቁር መከላከያ ብርድልብስም ጭምር አምጥቶለት ነበር። የአራዊትና በራሪ ነፍሳቶች ድምጽ ምሽቱን ሞልቶታል። እጆቹን ተንተርሶ በጀርባው የተንጋለለው ጥበቡ ኃይለ ሥላሴ ግን ውስጡ ከሚስተጋባው ድምጽ በስተቀር ለሌላው ሁሉ ጆሮ አልነበረውም። ጥበቡ ካለበት ትንሽ ራቅ ብሎ ቀኑን ሙሉ ምግብ ሲቀቀልበት የነበረ የእሳት ፍም አሁንም ይጫጫሳል። ለመሸሽ ወይም ለማምለጥ ሙከራ የሚያደርገውን ሁሉ ባጭር ለማስቀረት መትረየሳቸውን የደገኑ ወታደሮች በንቃት ዙሪያውን ዞብ መቆማቸው በጨለማው ውስጥ በድንግዝግዝታም ቢሆን ይታዩታል።

ዓመት የሞላት የበኩር ልጃችን የእምነት ናፍቆት፣ እኔም በእርግዝናዬ ያለሁበት ሁኔታ ትውስ እያለው መቋቋም በማይችለው ኃዘን ተመስጧል። ጥበቡ በሠርጋችን ዕለት በጌታና በሰው ሁሉ ፊት "ሞት እስኪለያየን" ደረስ ላንለያይ የገባነው ቃል ኪዳን ትዝ አለው። አሁን ግን በሞት ምክንያት ያልሆነ ክፉ መለየት በእኔና በጥበቡ መካከል መጋረጡ ጥበቡ እጅግ አባብቶታል። በውዴታ ሳይሆን ከሀገሩ ጋር ጦርነት በጫሩ አክራሪ እስላሞች ተገዶና ተማርኮ ከአገር ከወገን ከሚወዳቸው ቤተሰቡና ክርስቲያን ወገኖቹ ተነጥሎ፣ አሁን የሚገኘው በእስላሞች መካከል መሆኑ ሕልም ሳይሆን እውን ሆኗል። መቼ ይሆን መገናኛችን?

"ጌታ ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን ለታመኑ እጆችህ አደራ እሰጣለሁ! የራሴንም ሕይወት አስረክብሃለሁ" አለና በአምላኩ ፊት በእንባ ቃተተ።

ትዳር የጀመርንበት ውብ የቀብሪደሃር ቤታችን ፤ ነፋሻ አየር ለማግኘት እኔና እሱ ቁጭ ብለን የምንጨዋወትበት ሰፊው በረንዳ፤ የአትክልቱ ስፍራ፤ እኔና ጥበቡ የጨቅላው ትዳራችንን ፍቅር ማጣጣም የጀመርንበት . . . በሕይወቱ በደስተኛነት ለሁለት ዓመት የኖረበት የመጀመሪያ ቤታችን፤ የመጀመሪያ ልጃችን እምነት የዳኸችበትና መቆም የጀመረችበት በፊቱ ድንገት ድቅን አሉበት። ለእርሱና ለእኔ እንደገነት አምሳል የነበረውን የቀብሪደሃሩን ቤታችንን ዳግም ሊያየው ይችል ይሆን? በአምላኩ ፊት በእንባ ኀዘኑን አፈሰሰ። እንባው እንደገርፍ በጌታ በእግዚአብሔር ፊት ጎረፈ። የሚገርመው ኀዘን ያቆራመደውን ሁለንተና አልፎ ግን ልቡን የሚጠብቅ መለኮታዊ ሰላም ከእርያም ሲላክለት ጥበቡ ይታወቀው ነበር። ደም ለማፍሰስና ነፍስ ለማጥፋት በተጠንቀቅ ከቆሙት የሶማሌ ወታደሮች በስተጀርባ የሚጠብቁትንና የሚታደጉትን የጌታ የእግዚአብሔርን የማያንቀላፉ ዓይኖች በ ዓይነ ሕሊናው ተመለከተ። ጥበቡ ሰብአዊ ነፃነቱ ተገፎ ያለፈቃዱና ያለውዴታው ከሃገር ከወገኑ በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትሮች ርቆ በመወሰድ ላይ ቢገኝም፣ በእርሱና በአምላኩ በእግዚአብሔር መካከል ግን ከእስትንፋሱ ይልቅ የቀረበ ህብረትና አንድነት እንዳለ ታወቀው። ስለዚህ ማንኛውም ነገር በአምላኩ ቁጥጥር ሥር እንደሆነ ተገነዘበ። የእግዚአብሔር መገኘት እንዲህ ቀርቦት ሳለም በሁሉን ቻይ አምላኩ ፊት አሁንም በ ጸሎት መቃተቱን ቀጠለ፤ እንዲህ ሲል "ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! ከምወዳት ሚስቴና ልጆቼ ተለይቼ እንድኖር ያንተ ፈቃድ ከሆነ፣ በአንተ ጸጋና ኃይል ይቻላል። ከምወዳቸው ክርስቲያን ወገኖችና ከቤተክርስቲያን ተለይቼ እንድኖር ፈቃድህ ከሆነም፣ በአንተ ኃይል ይቻላል። ነገር ግን ጌታ ሆይ ያለ ቃልህ እንዴት መኖር እችላለሁ? መጽሐፍ ቅዱስ አገኛለሁ ብዬ ወደ ማላስብበት ወደ እስላም አገር እየተወሰድኩ ነው። አምላኬና አባቴ ሆይ መጽሐፍ ቅዱስ ያስፈልገኛል፤ ቃልህ ያስፈልገኛል። ያለ ቃልህ መኖር ከቶ አልችልም።"

የጥበቡ ነፍስ ሸክሟን በአምላክዋ ፊት አራገፈች። ጥበቡ አሁን ውስጡን ያነዋወጠው ኀዘን ሰቆቃና መባባት ሁሉ ጸጥና እረጭ ብሎለታል። ከዚህ ጸሎቱ በኋላ ጀርባውን ሶማሌዎች በወረሩት በኢትዮጵያ ምድር ላይ ፊቱን ወዳምላኩ ሰማየ ሰማያት አድርጎ በምርኮኝነት ሁለተኛ ሌሊቱን ሊያሳልፍ በሚገርም ዓይነት ጥሩ እንቅልፍ ተወሰደ። አዎን በጥሩ እንቅልፍ።

****

*አምቡላንሱ!*

ጊዜው ከጠዋቱ አምስት ሰዓት ጥበቡ በተማረከ በሶስተኛው ቀን ነው። የኦጋዴን ፀሐይና ሙቀት እየከረረና እየጨመረ የሚሄድበት ወቅት ነው። ጥበቡ ከአንድ ሶማሌ መኮንን ጋራ ዛፍ ጥላ ስር ቁጭ እንዳለ ዓይኖቹ ከርቀት በሚነሳ አቧራ ላይ አተኩረዋል። አቧራው እንደሚጓዝ ደመና ወደርሱ በቀረበ ቁጥር የመኪና ሞተር ድምጽም ለጆሮው እየጎላ መጣ። እሱ ወዳለበት የጫካ ከሊኒክ የሚገሰግስ አንድ አምቡላንስ ኖሯል። በመድኃኒትና መጻሕፍት የታጨቀ። ጭነቱን የሚያራግፉ ወታደሮች ከውስጡ ዱብ ዱብ አሉ። መድኃኒት የያዙ ካርቶኖች ሳጥኖች ባንድ መደዳ ሲከመሩ ጥበቡ ከነበረበት 65 ጫማ ርቀት ያህል ላይ ሆኖ ያያል። አንደኛው ወታደር ደግሞ መጻሕፍት እያወጣ አንድ ጠረጴዛ ላይ ይደረድራል።

የጭነት አውራጂዎቹን ሰዎች እንቅስቃሴ የጥበቡ ዓይኖች በሚገርም ጥንቃቄ በመከታተል ላይ ናቸው። ምናልባት ሐኪም በመሆኑ የሚያራግፉት የመድሐኒት ዓይነትና ምንነት ገዶት ይሆን? ብቻ ያም ሆነ ይህ እሱ ለራሱ እስኪገረም ድረስ ዓይኖቹን ከእንቅስቃሴያቸው ላይ ማንሳት አልቻለም። ጥበቡ ካለበት ርቀት ሆኖ ከአንቡላንሱ የሚራገፉትን መጻሕፍት እየቈመለከተ በልቡ፤ "እነዚህ ሰዎች! መድኃኒትስ እሺ ይበዝብዙ። ይሄን ግን ጭነው የሚያመጧቸው መጻሕፍት ደግሞ ምን ዓይነት ይሆኑ? የሕክምና ወይስ የፖለቲካ?" እያለ በአእምሮ ሲያወጣ ሲያወርድ ድንገት ካለበት ረቀት ሆኖ አንድ ጥቁር ሽፋን ያለው መጽሐፍ ሲወርድ አየ። መጽሐፍ ቅዱስ ይመስላል! "ቢሆንስ?" አለ በአሳቡ። የልቡ ምት ፍጥነቱ ጨመረ! ጥበቡ ሳያሰበው ከተቀመጠበት ተነስቶ በፍጥነት አምቡላንሱ ወዳለበት ሥፍራ አመራ። ከርቀት የያው መጽሐፍ በእርግጥም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። "ቶምሰን ቼን ሬፈረንስ" <Thompson Chain Reference> የተሰኘው የእግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ ዓይኖቹ የሚያዩትን ማመን አቃታቸው። ሰውነቱን መሸከም እስኪቸግራቸው ድረስ እግሮቹ ተብረከረኩ። እራሱን መግታት አልቻለም። መጽሐፉን ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ ገለጥ ሲያደርገው "ጥበቡ ኃይለ ሥላሴ" ይላል። የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት አዘወትሮ ይጠቀምበት የነበረው የገዛ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ። ሶማሌዎቹ የኢትዮጵያን መንግሥትና የኦጋዴን ነዋሪዎችን ሀብትና ንብረት በዝብዘው ማጋዛቸው ነው። የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ግን ጥበቡ ከሚገኝበት ትክክለኛ አድራሻ ድረስ ክርስትናን አጥበቀው በሚጠሉ እስላሞች ጫንቃ አሸክሞ ቃሉን እንዳመጣለት አስተዋለ። ባለፈው ምሽት ወደ ሁሉን ቻዩ ጌታ ለጮኸው ጩኸት የመጣ አምላካዊ ምላሽ መሆኑ የገባት ነፍሱ በውስጡ ጮቤ ረገጠች። ብቻውን ይህን ተአምር ላደረገለት አምላክዋና ጌታዋ የሚገባው ምስጋናና ሃሌ ሉያ በውስጥዋ ተሰተጋባ።

ከሶማሌዎቹ ዶክተሮች አንዱ ሙክታር አምቡላንሱ ያወረዳቸውን የመድኃኒት ክምሮች በዓይነት በዓይነታቸው እያስተካከለ በመደርደር ላይ ነው። ከቀብሪደሃሩ ሆስፒታል የተበዘበዙ መድኃኒቶች ናቸው። ከተደረደሩትም መጻሕፍት መሃል ከመኖሪያ ቤታችን የመጡ ሌሎች ለሕክምናም ሥራው የሚረዱ የጥበቡ የግል መጻሐፍቱ አሉ። ይሁን እንጂ ጥበቡ በእጆቹ መሃል ጠበቅ አድርጎ

ከያዘው መጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ልቡንና አእምሮውን የሞላው ተጨማሪ አሳብ የለም።

ትልቁ ጥያቄ ግን መጽሐፍ ቅዱሱን ከእነዚህ የክርስትናና የኢትዮጵያ ጠላቶች ከሆኑ የሶማሌ ወታደሮች እጅ እንዴት መረከብ እንደሚችል ነው። ለጥበቡ ይሄም ቅንጣት ያህል አላስጨነቀውም። ጸሎቱን በድንቅ ለመመለስ መንቀሳቀስ የጀመረውን የእግዚብሔርን ክንድ ማንም ሊገታ እንደማይችል ጥበቡ እርግጠኛ ነው። "ዶ/ር ሙክታር፡- ይሄ የኔ መጽሐፍ ነው። ልወስደው እችላለሁ?" ሲል አምቡላንሱ ያወረዳቸውን መድኃኒቶች በመኮልኮል ላይ ለነበረው ሶማሊያዊ ሐኪም ጥበቡ ጥያቄ አቀረበለት። ዶ/ር ሙክታር የመድኃኒት ድርደራ ሥራውን ቆም አደረገና ጥበቡ በእጁ የያዘውን እንድና ብቸኛ "ሃብት" ትኩር ብሎ እያየ መጽሐፍ ቅዱስ ነው?" (Is this the Bible?) ሲል ጠየቀው። ጥበቡም ለአፍታ ያህል መልስ ከመስጠቱ በፊት ምን ማለት እንዳለበት አሰበ። ይህ ሰው በእምነቱ ክርስቲያኖችን የሚጠላ እስላም ነው። ስለሆነ ጥበቡ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ብነግረው ሊከለክለኝ ብሎ በማሰብ ምን ብለው ይሻል ይሆን? ምን ዓይነት አማራጭና የጥበብ ቃል ወይንም መንገድ ቢጠቀም ይሻል ይሆን? የሚል ይመስለኛል። ነገር ግን ለጥበቡ ኃይለ ሥላሴ ያለው ብቸኛና አማራጭ የሌለው የእውነት መንገድ ብቻ ነው። እግዚአብሔር አምላኩ እጆቹ ያስገባለትን ይህን ውድ "ሃብት" ማንም ሊነጥቅ ስለማይችል ከእውነት በቀር ውሸትን ላይናገር ወስኖ "አዎን መጽሐፍ ቅዱስ ነው" አለ ጥበቡ እምነትና ድፍረት በተሞላው አነጋገር። "ልትወስደው ትችላለህ።" ይሄን ብሎ ሙክታር ወደ መድኃኒት ኩልኮላ ሥራው ጎንበስ ሲል ጥበቡ በቆመበት ስፍራ እንዳለ የድል የደስታና የምስጋና ማዕበል ሁለንተናውን አጥለቀለቀው። በአምላኩ ፊት እንደ ሕፃን ልጅ ጮቤ መርገጥ አሰኝቶታል። ሆኖም ግን ስሜቱን ሁሉ በልቡ አምቆ ይህን ከሰማይ የተሰጠውን ታላቅ "ሃብት" በእጆቹ ጥብቅ አድርጎ ይዞ በትናንትናው ምሽት እንዲያ በእንባ ወደ ቃተተባትና በሚገርም እንቅልፍ ወደ ተወሰደባት መጠለያው አመራ። እንደደረሰም ያ ደግ ሶማሌያዊ በሰጠው ብርድልብስ መጽሐፍ ቅዱሱን ጥቅልል አድርጎ በጥንቃቄና በክብር አስቀመጠው።

****

*የሰቆቃ ሌሊት!*

ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ ጥበቡንና ሌሎች ምርኮኞችን ወደ ሞቃዲሾ ከተማ የሚያጓጉዙ ሦስት ትላልቅ የጭነት መኪናዎች ሶማሌዎቹ አዘጋጁ። ከአንድ ቀን መለያየት በኋላ ኢያሱና ጥበቡ ዛሬ ተገናኝተዋል። ብቻ የትም ይሁን የት ኢያሱ ልጁ እንደሆነና ከእርሱም መለየት እንደሌለበት ጥበቡ ለሱማሌዎቹ አስታውቋል። በዚያን ቀን ረፋዱ ጠዋት ላይ ተአምራታዊ በሆነ አሰራሩ እግዚአብሔር በእጁ ያስረከበውን የገዛ መጽሐፍ ቅዱሱን በብርድልብሱ ጠቅልሎ ይዞ ከኢያሱ ጋር በአንደኛው የጭነት መኪና ላይ ተሳፈረ። አፈሙዛቸውን በምርኮኞቹ ላይ ደግነው በዓይነቁራኛ የእያንዳንዳቸውን እንቅስቃሴ በሚከታተሉ ወታደሮች ተከበው ምርኮኞቹ ለእርድ እንደሚጋዝ የከብት መንጋ እየተሽጋሸጉ በጭነት መኪናዎቹ ላይ ተጠቀጠቁ።

የከባድ መኪና ሾፌሮች ኦጋዴንን አቋርጠው እንደሰርዱን በጀርባቸው የጠቀጠቋቸውን ምርኮኞች ጭነው አቀበቱንና ቁልቁለቱን አባጣውና ጎርበጥባጣውን መንገድ ሲከንፉ እንኳን ያን ሁሉ ሕዝብ ትንኝም የያዙ አልመሰላቸውም። ያን መከረኛ ሕዝብ እንደ ኳስ ወደ ሰማይ እያነጠሩ በታላቅ ፍጥነት ሲነጉዱ ሰብዓዊ ፍጡሮችን ሳይሆን ለገበያ የሚያቀርቡት ሽንኩርትና ድንች የሚያጓጉዙ ይመስል ነበር።

በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ የቀኑ ሙቀትና የፀሐዩ ንዳድ ሌላው አስጨናቂ ጉዳይ ነበር።

በኀዘን፥ በዱላና በስድብ የተኮራመተውን ሰውነቱን ለማፍታታት ከዚያ መሃል አንድ ሰው ቢቆም ወይም ፎ...ራራ ርህራሄ በሌላቸው ወታደሮች ጠመንጃ ሰደፍ ተደብድቦ እንዲቀመጥ ይደረጋል፤ ከምርኮኞች መሃል አንዱ የሲጃራ ሱስ ያለበት መቼም የሱስ ነገር ይገባቸዋል በሚል ይመስላል ወታደሮቹ ከሚያጨሱት ሲጃራ አንድ ሁለቴ እንዲያስጨሱት ሲለምናቸው አንተ የሚያስፈልግህ ሲጃራ ሳይሆን አንድ ጥይት ለዚህ ጭንቅላትህ ነው ሲል አንደኛው ወታደር በትዕቢትና በጭካኔ ተሞልቶ በሰጠው ምላሽ የቀሩት ወታደሮች አስቂኝ ቀልድና ጨዋታ የተናገረ ይመስል ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲስቁ መስማት በራሱ ያሳምማል።

የጉዞው ሰዓት በጨመረ ቁጥር የምርኮኛውን ክብረ ሰብእና የሚደፍሩና የሚገፉም ብዙ አሳዛኝና ቀፋፊ የሆኑ ትዕይንቶች ሶማሌዎቹ ያለርህራሄ ማሳየታቸውን ቀጠሉ። እንዲህ የመሰለውን ውርደት ተከናንቦ እንደ አሮጌ አዳፋ ጨርቅ በሶማሌዎቹ ሰደፍ ጫማና ስድብ ያ ሁሉ ሕዝብ ተረጋገጠ። በታሪኩ በባህሉም ሆነ በአኗኗሩ በዙሪያው ካሉት ጎረቤት ሀገሮች ይልቅ የበላይነት የሚሰማው ኩሩው የኢትዮጵያ ሕዝብ። ከወረደበት የዱላና የስቃይ ማዕበል ይልቅ ያየለበት የወታደሮቹ አጸያፊ ስድብና ሕሊናን የሚነካው ንቀታቸው ከሕይወት ይልቅ ሞትን አስመርጦታል።

ባንጻሩ ደግሞ ያልጠበቁት ድል ያስከራቸው እነዚህ የሶማሌ ወታደሮች ያገኙትን አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም ወዳልታወቀ ጨለማ የሚወስዱትን ሕዝብ ሰብዓዊ ክብር በመግፈፍ ማዋረዳቸውን ቀጥለዋል። የጫኑዋቸውን ምርኮኞች በዱላ ፥በእርግጫ፥ በስድብና በጩኸት ማዕበል እያከናነቡ ከአሮጌ ጨርቅ እንደተሠራ ኳስ በእነዚያ የጭነት መኪናዎች የብረት ወለል ላይ ይረጋግጡታል።ድመት የያዘቻትን አይጥ በጫጭቃ ከመብላቷ በፊት በነፍሷ እንደምትጫወተው ዓይነት አሰቃቂ ጨዋታ ይጫወቱበታል። ያ የመከላከል አቅም የሌለው ምስኪን ሕዝብ ቀፋፊው ጨዋታ በመራራ የሞት ጽዋ ሊደመደምም እንደሚችል በተደጋጋሚ ተነግሮታል።

ሰዓታቱ በነጎዱ ቁጥር ሶማሌዎቹ ጦር መዞ ያልተዋጋውን ሲቪልና ሰላማዊ ሕዝብ ምርኮኛ አድርገው የኦጋዴንን ክፍለ ግዛት ለመልቀቅ በብዙ ብዙ ኪሎ ሜትር ከነፉ። ጠቅጥቀው ከጫኑዋቸው ሕዝብ ብዛት የተነሳ መኪናዎቹ አቀበት ሲወጡ እንደቆሰለ አንበሳ ያቃስታሉ። ቁልቁለት ሲወርዱ ደግሞ ያላቸውን የመሽቆልቆል ፍጥነት ለሚመለከት በፍሬን ብልሽት ባፍጢማቸው የሚደፉ ይመስላሉ። በዚያው መጠን አቧራው እንደደመና እየተነሳ በፀሐይ ሙቀትና በመተፋፈጉ ብዛት ላብ ባጠለቀው መከረኛ ሕዝብ ላይ መቆለሉን ቀጥሏል።

ጥበቡ ኃይለ ሥላሴም በዚህ የመከራ ምሽት በአምላኩ ፊት ያነባል። የሚያነባው ለራሱ ሳይሆን በመከራውና በፍዳው እንዲመስለው ከአምላኩ ለተሰጠው ለዚህ ምስኪን ሕዝብ ነበር። እሱ ለራሱ ከሰማይ በደረሰው ዕጣ ክፍል ምክንያት፣ ከሀገሩ ጋር ጠበኛ ወደሆነ ባዕድና አክራሪ እስላሞች ምድር ለልዩ መለኮታዊ ተልዕኮ፣ ይሄን ልዩ ጉዞ እንደተያያዘው በጥቂቱ ገብቶታል። ነገር ግን ያላንዳች ርህራሄ ሶማሌዎቹ በዱላና በስድብ የቁም ስቅላቸውን ለሚያሳዩአቸው ለሚያዋርዷቸው ወንዶችና ሴቶች፥ አረጋውያንና ወጣት ወገኖቹ ጥበቡ በአምላኩ ፊት በታላቅ ኀዘንና ሰቆቃ ያን ሌሊት በእንባ እንዲቃትት መንፈስ ቅዱስ ረድቶታል። ያች ሌት እንቅልፍ አልባ የሆነች የጣዕር ሌሊት ነበረች። ሥጋው እንዲያ በሚንገላታበት በዚያ የጭንቅ ሌሊት እንኳን በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ፊት ከቀረበችበት ብርቱ አጀንዳ የነፍሱን ውሳኔ ሊያናጋ የቻለ ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ኃይል አልነበረም። የእግዚአብሔር ይቅርታ ምሕረትና ጸጋ ከሰማይ ካልወረደ በስተቀር ያ ሕዝብ የሚጠብቀውን መከራ ሊቋቋመው እንደማይችል ጥበቡ አውቆታል። ስለዚህ ስለምድሩ ስለሕዝቡና ስለራሱም በአምላኩ ፊት ንስሐ በመግባት ዓይኖቹ በእንባ ሲታጠቡ ሌሊቱ ተገባደደ።

ፀሐይም እንደወትሮዋ ብርሃንዋን በግፍና በቁከኔ በተሞላው ምድር ላይ ልትሰጥ የማለዳ ጮራዋን ፈነጠቀች። ወታደሮቹ ትናንሽ የሰርዲን ቆርቆሮዎች ለቁርስ ባስቸኳይ አደሉና በእጆቻቸው እያወጡ እንዲበሉ ምርኮኞቹን አዘዙ። ብርድ ሲያቆራምደውና ሲያንዘፈዝፈው ባደረው እጃቸው እያወጡ ለመብላት ባደረጉት ትግል፤ በጥንቃቄ ባልተከፈቱት የሰርዲን ቆርቆሮዎች የብዙዎች እጅ በመቆራረጡ የበሉት ከደማቸው ቀላቅለው ነበር።

ረፋዱ ላይ ደግሞ የፀሐይ ግለት ያስከተለው ሙቀትና ወበቅ በተራው ምርኮኛውን ሕዝብ ያሰቃየው ጀመር። ለቀናት ጾዳት ከጎደለው በአቧራና በላብ ሲታፈግ ከቆየው ሰውነት በፀሐይ ብርታት የሚተነው መጥፎ ጠረን በራሱ ነፍስን ያስጨንቃል። በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ በዱላ ብዛት ጉዳትና ቁስል ከደረሰባቸው ከንዳንዶች የሚሰማው የጣዕር ድምፅ የእስረኛውን ዓይን በፍረሃት ሞልቶታል። በዚህ ዕለት ከቀኑ ስምንት ሰዓት ገደማ የጭነት መኪናዎቹ የኢትዮጵያን ግዛት ተሻግረው ወሰኑ ላይ ወደምትገኝ የጦር ሰፈር ያለባት ከተማ ለምሳ ቆሙ። ወታደሮቹ ጠመንጃዎቻቸውን እያወዛወዙ ከጠላታቸው ጋር የገጠሙትን ጦርነት ድል ነስተው መምጣታቸውን ለመግለጽ በአሸናፊነት ሆታ ነበር ወደ ከተማይቱ የገቡት። ለሕዝባቸው የሚያሳዩአቸው የከብር ዋንጫዎቻቸው ደግሞ እንዲያ ጸጉራቸው የተንጨባረረ ሰውነታቸው እጅግ የተጎሳቆለና ጾዳት የጎደለውን ምርኮኞቻቸው ነው።

በከተማይቱ መንገዶች ግራና ቀኝ ተሰልፎ ይጠባበቅ የነበረው ሕዝብ ምርኮኞቹን የጫኑትን መኪናዎች አላሳልፍ እስኪል ድረስ በጭፈራቸውና አስቀያሚ ንግግራቸው ምድር ተሸበረች። "እስረኞቹ የት ናቸው? ልጆቻችንን የገደሉብን የኢትዮጵያ ውሾች የት ናቸው? ስጡን ለእኛ፤ በቀላችንን እንወጣባቸው፤ ቦጫጭቀን እንገደላቸው፤" ይሄን ከመሳሰለውና ከሚስተጋባው ጩኸት ጋር የሶማሊያ ሕዝብ ለኢትዮጵያውያን ያለው ታላቅና መራራ የሆነ ጥላቻ በአየሩ ላይ ይስተጋባ ነበር። ከኢትዮጵያ ጋር በነበረው ጦርነት የብዙዎቹ ዘመዶች በጦር ሜዳ አልቀዋል። ስለዚህ በእነዚህ እጃቸው በገቡ ኢትዮጵያውያን ላይ የበቀል እርምጃ ይወስዱባቸው ዘንድ እንዲሰጧቸው ነበር ሰልፍ የወጣው ሕዝብ ጥያቄ። ለዚህ ጥያቄው መልስ ያላገኘው ሕዝብ ምርኮኞቹን መግደል ቢያቅተው ፈንከክቶ ለማቁሰል ከፍተኛ ጉዳት ለማድረስ የድንጋይ እሩምታውን ማዝነብ ጀመረ። ከንዱ መኪና ወደ ሌላኛው ትዕዛዝ ተላለፈና ወታደሮቹ ወደ ሞቃዲሾ የሚወስደውን አውራ ጎዳና ባስቸኳይ ለመቀየስ ተገደው ከከተማይቱ ወጡ።

ከጥቂት ሰዓታት ጉዞ በኋላ በመንገዱ ግራና ቀኝ የተሰሩ ደሳሳና አስቀያሚ የቆርቆሮ ቤቶች ወዳሉበት አንዲት ትንሽ መንደር ደረሱ። ምርኮኞቹን የጫነውን አንዱን መኪና ወደ ሌላ ስምሪት ሊልኩ ተፈለገና የያዛቸውን ምርኮኞች እንዲያራግፍ ተደረገ። የመከራው ገፈት ገና ከሁኑ ያንገሸገሸውን እስረኛ ባስቸኳይ ከመኪናው እንዲወርድ ወታደሮቹ ያጣድፉት ገቡ። አቅም ያጡትንና ቁስለኞቹና ሴቶቹን የሚታገሱበት ትዕግሥት ፈፅሞ አልነበራቸውም። በሰደፍና በዱላ እያዳፉና ከመኪናው አውርደው እየከሰከሱ ወደ ሌሎቹ ሁለት የጭነት መኪናዎች ላይ ሲያሳፍሯቸው ቅንጣት ታህል ርህራሄ አይታይባቸውም ነበረ። ከፊት ይልቅ አስጨናቂና መተፋፈሻ በሌለው ሁኔታ አንዱ በሌላው ላይ ተጫነ።

በዚህ ሁኔታ የታጨቀው ሕዝብ በቁሙ ተጠጋግቶ እንዳይጓዝ ይባስ ተብሎ መኪናው ወለል ላይ እንዲቀመጥ ራስ ራሱን በጠመንጃ ሰደፍ ይወገር ጀመር። እስረኞቻቸውንና አካባቢያቸውን በቁጥጥር ስር ለማዋል እንዲችሉ የወታደሮቹን እይታ የሚከለክል አንዳች ነገር መኖር የለበትም። ስለዚህ ቁጢጥ ብለው በጭንቅ እንዲጓዙ ምርኮኞቹን አስጨነቋቸው። ከፍጥነታቸው ጋር ጠመዝማዛውን መንገድ ሲዞሩ እስረኞቹ እርስ በርሳቸው ይደራረቡም ነበር። በዚህ መሃል አንዲት ሴት አእምሮዋን

ስታ ወደቀች። አየር የምታገኝበት እርዳታ ሊሰጣት ቀርቶ በግፊያውና በመረጋገጡ ብዛት ልትሞት እንደነበር መመልከት የሚዘገንን ነበር።

****

*ወህኒው!*

እንደማይደረስ የለምና እኩለ ሌሊት ሲሆን ሞቃዲሾ ከተማ ደረሱ። ሞቃዲሾ በመግባታቸው ከሠላሳ ሰዓታት በላይ የተጓዙት የጭንቅ ጉዞ አበቃ። የጭነት መኪናዎቹ የጠቀጠቋቸውን ምርኮኞች በሶማሊያ ማዕከላዊ እስር ቤት ቅጥር ግቢ ካራገፉና ሞተሮቻቸውን ካጠፉ በኋላ የነበረው የሌሊት ቀፋፊነትና ጭርታ ለብዙዎች አስደንጋጭና አስፈሪ ስሜትን ፈጠረባቸው። ለረዥም ሰዓታት ባልተቋረጠው ጉዞአቸው የተሳሰረው ሰውነታቸውን ለማፍታት እስረኞቹ መንጠራራት የቻሉት አሁን ገና ነው። ነገርግን እግረመንገዱን ዙሪያውን የሚቃኘው ዓይናቸው በሚመለከተው ሁሉ ምርኮኞቹ ዘንድ አንዳችም የተሰፋ ጭላንጭል የሚሰጥ አልነበረም።

ብርቱውን ጨለማ ለማሸነፍ ባልቻለ ደካማ የኤሌክትሪክ ብርሃን ውስጥ እስረኞቹ ብዙም ዙሪያቸውን አገናዝበው ማየት አልቻሉም። አመድማ መልክ ያለው የወህኒው የማይበገር ግንብ አጥር ውስጥ የሚገኙ የእስር ቤት ህንፃዎች በድንግዝግዝም ቢሆን ይታያሉ። ግቢው ውስጥ ብዙ ወታደሮች ይንቀሳቀሳሉ። በጠላት እጅና ግዛት መሆናቸው ምርኮኞቹ ይበልጡን ታውቋቸዋል። ድንገትም አንድ መኮንን ወደፊት እየተራመደ መጣና ዓይን ሁሉ ወደርሱ እስኪመለከት ሕዝቡ ጸጥ እንዲል አዘዘ። "ቋሚ የሆነ ውሳኔ ነገ እስኪወሰን ሁላችሁም እዚሁ ውጪ ሜዳ ላይ ነው የምትተኙት" አለ መኮንኑ፤ ቋሚ የሆነ ውሳኔ የሚለው የዛቻ ቃል እንደሆነ ብዙዎቹ ተሰማቸው። የቃሉን ትርጓሜ ለማወቅም ሆነ ለመጠየቅ እስረኛው ምንም ዓይነት አቅም የለውም። እጅግ ከባድ ብረት የደረቀው እጅና እግራቸው የእንቅልፍ እጦት የሚለበልበው ዓይናቸው አሁን የሚፈልገው የትም ይሁን መተኛትና መገላገል ነው። በረሃብ ያረረው አንጀታቸው ሆዳቸው ውስጥ የሚያሰማው ድምጽ እሚያስተኛም አይመስልም እንጂ። ስለዚህ አንዱ ቢገድሉትም እንኳን በነፍሱ የቆረጠ ይመስል መኮንኑ ንግግሩ እንደጨረሰ በሰለለና በጠወለገ ድምጽ ፣ "ምግብ... ...! ምግብ... መብላት ያስፈ. . ." ብሎ ገና ሳይጨርስ "ዝም በል! ይመጣላችኋል!" በማለት የመኮንኑ ድምጽ አቋረጠው። አንድ ኩባያ ወተትና ዳቦ ለእያንዳንዱ እስረኛ ታደለ። አንዳንድ እጅግ የደከሙና የጠወላለጉ እስረኞች እጆቻቸው ከመንቀጥቀጣቸው የተነሳ የተሰጣቸው ብርቅዬና ውድ ወተት ሲደፋባቸው ከምግብ አዳዮቹ ያገኙት የሚያንገጥጥ ዓይን እንጂ በተደፋባቸው ምትክ ሌላ ወተት አልነበረም።

ይህን ከመሰለው አንጀት ጠብ ከማይል ራት በኋላ ምርኮኛው ሕዝብ ትቢያና አቧራ በሞላበት የወህኒው ሜዳ ላይ እንዲተኛ ታዘዘ። ጥበቡ ያቺን ብርድልብሱን ሜዳው ላይ ዘረጋና ሰዎች ተጠጋግተው አብረውት እንዲተኙ አደረገ። በመጨረሻም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር የምሕረት ዙፋን ፊት እንደልማዱ ቀረበ። "ጌታ አምላኬ ሆይ! አንድ ነገር አውቃለሁ አንተ በሥራህ ሁሉ ጻድቅ ነህ። በደረሰብንና በሆነብን ነገር ሁሉ አንተ ልክ ነህ። ኦ ሊሻን የኔ ውድ ሊሻን! . . ትንሿ ብላቴናዬ እምነት! ጌታ ሆይ! ...በታመኑት እጆችህ ውስጥ አስቀምጣቸዋለሁ። የሚያስፈልጋቸውን ጥንቃቄ ሁሉ እንደምታደርግላቸው አምንሃለሁ። አምላኬ ሆይ እነርሱ ያንተ ናቸው . . ." ስዕላችንን በዓይነ ህሊናው ስሎ እየቃተተ ሳለ የተንገላታው ሰውነቱ በኃይለኛ እንቅልፍ ተሸነፈ። ጥቂትም ቢሆን ሁሉን ሊያስረሳው የሞት ዓይነት እንቅልፍ ገላገለው። ጠዋት በማለዳ እስረኞቹ ትኩስ ሻይና ዳቦ በነፍስ ወከፍ ታደላቸው። ብርድና ቆፈን ያደረቀው ሰውነታቸውን ትንሽም ቢሆን ለማፍታታት ረድቷቸዋል። ከዚህ በኋላ ወደ አንድ ትልቅና ሰፊ የእስር ቤት እንዲገቡ ታዘዙ። ከወለሉ እጅግ ከፍ ባለ ጣሪያ

የተጋጠመ ትናንሽ መስኮቶች ከግድግዳዎቹ አናት ላይ ያሉት የሲሚንቶ ክፍል ነው። ክፍሉ ውስጥ አንዳችም መቀመጫ ወንበርም ሆነ አልጋ አይታይም።

አዳራሹ ቀደም ሲል በተማረኩና ወደ አምስት መቶ በሚያህሉ ኢትዮጵያውያን ተሞልቷል። እስረኞቹ ወታደሮች፥ ሰላማዊና ሲቪል ሰዎች ቅልቅል ናቸው። ብዙዎች የቆሰሉ የታመሙና የሚያቃስቱም አሉባቸው። ጥበቡና አብረውት የነበሩት ምርኮኞች ከእነዚህኞቹ ጋር ሲቀላቀሉ ለመኝታ የተሰጣቸው አንዳችም ነገር የለም። በደረቅ ሲሚንቶ ወለል ላይ እንዲተኙ ነው የተነገራቸው። እያንዳንዱ እስረኛ ጎኑን የሚያሳርፍበት ያህል ቦታ እንጂ እንደልብ የሚያንቀሳቅስም ቦታ በአዳራሹ የለም።

መጋረጃም ሆነ መከለያ ያልተደረገለት የመጸዳጃና ገላ የመታጠቢያ ስፍራ በአዳራሹ አንድ ጥግ ይገኛል። ከመጸዳጃው ወደ አዳራሹ የሚተነው ቁናሰና ግማት አስጨናቂ ነው። በዚያ አከባቢ እንዲተኙ ዕጣው የደረሰባቸው ደግሞ የመጸዳጃውንና የገላ መታጠቢያውን ውሃ ፍንጥቅጣቂ ሊያመልጡት ፈፅሞ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ነበሩ።

በምሳ ሰዓት እስረኞቹን ከአዳራሹ ወደ ደጅ አወጡአቸው። ከአጥሩ ውጪ ያለውን የሰዎችንም ሆነ የመኪና እንቅስቃሴ ማየት አይቻልም። የወህኒው ቅጥር እጅግ ከፍ ያለ ከመሆኑ የተነሳ በውስጡ ያሉትን እስረኞች ከውጪው ዓለም በሚገባ የመለየት ሥራውን ሰርቷል። በወህኒው ቅጥር ውስጥ ያለው ሰው ሁሉ ማየት የሚችለው ጥቂት ደመና በተን ያለበትን ሰማይና ሙቀትዋን ያለገደብ የምትለቀውን የፀሐይ ኃይል ነው። የሙቀቱና የወበቁ መጠን እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ከምድር የሚነሳው አቧራ ከሰሩ የሚረግድ ይመስል ነበር።

ትንሽዬ ስጋ ጣል የተደረገበት ከበቆሎ ግርድፍ የተሰራ ቀጭን ሙቅ /ሾርባ ለምሳ ሱማሌዎች አቀረቡላቸው። ከምሳው በኋላ ግን ወደዚያው ትልቅ የእስር ቤት ገብተው እንዲታጎሩ አዘዟቸውና በሮቹን በጥንቃቄ ቆለፉባቸው። ወደፊት ምን ሊደርስባቸው እንደሚችል እጅጉን ያሳሰባቸው እስረኞች በተዘጋው ወህኒ ውስጥ ዝግ ባለ ድምጽ እርስ በርስ ስጋታቸውን ተወያዩ። ሕይወታቸው ባንዲት ቀጭን ክር ላይ እንደተንጠለጠለች ያህል ተሰማቸው። ማን ያውቃል ምናልባትም እዚያ ወህኒ ውስጥ ያጩቋአቸውን እንዳሉ በሞት ሊቀጧቸው ሊሆን ይችላል።

በዚህ የጭንቅ አሳብ ተመስጠው ሳለ ነበር አንድ የሱማሌ መንግሥት ተወካይ መጥቶ ለሞት የሚያሰጋቸው ጉዳይ እንደሌለ የገለጸላቸው። ስጋቱ የቀነሰላቸው ቢሆንም እዚያ ማእከላዊ እስር ቤት በቆዩበት ሁለት ሳምንት ውስጥ ወታደሮቹ የባለስልጣኑን አነጋገር ከጉዳይም አልጣፉትም። ደም በተጠሙ ዓይኖቻቸው እስረኞቹን በሰበብ ባስባቡ ጠመንጃ ሲደግኑባቸው ሲረግጧቸውና ሲደበድቧቸው ነው የሰነበቱት።

እንደ ፀሐዩ ንዳድና ትኩሳት የጥላቻውም ከፍታ ቀኑን ሙሉ ሲንር ይውላል። የማታው ቁርና ቅዝቃዜ ደግሞ በእስረኛው ላይ ያጠላውን የሞት ትኩሳት በረድ አድርጎት ያድራል።

****

*"ታዲያ ጥበቡ የት ነው?"*

እኔና ወላጆቼ የጥበቡን በሱማሌ ወታደሮች ተማርኮ የመወሰድ አስደንጋጭ መርዶ ገና አልሰማንም። ከፊታችን የተደቀነውን ታላቅ ኀዘን ያላወቅን ናዝሬት የምንገኘው እኛ በፊናችን ሐምሌ 17 ቀን ያፈራረቀብንን ደስታና ኃዘን እንዴት እንደምናስተናግደው ተደነጋግረናል። በአያቴ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ምክንያት ወላጆቼና መላው ቤተዘመዱ ኀዘን ላይ ናቸው። አለማወቃችን እንጂ በመልክም ሽምግልናና ፍጻሜ የአያቴ ከዚህ ዓለም በሥጋ ሞት መሰናበት፣ የቀብሪደሃሩ ድንገተኛ ጦርነት

ከስከተለብን ኀዘን ጋር አይወዳደርም። በአንጻሩ ደግሞ በዚያ በማይረሳ ልዩ ቀን እኔም ሁለተኛዋን ልጃችንን በድንገት ወልጄ በአራስ አልጋ ላይ ተኝቻለሁ። ሊገባኝና ልቆጣጠረው ባልቻልኩት ኀዘንና ልቅሶ በተኛሁበት አልጋ ዓይኖቼ በእንባ ይታጠባሉ። ለወትሮው የየጣቢያውን ዜና የመከታተል ልማድ የነበረው አባቴም በኀዘኑ ምክንያት ሰሞኑን ምንም ዓይነት ዜና አልሰማም። ሶማሊያ በሀገራችን ላይ ስለከፈተቺው ያልታሰበ ጦርነትም ሆነ በብዙ ሺህ ስለተቆጠሩት ኢትዮጵያውያን ምርኮኞች በኢትዮጵያ ዜና ማሰራጫዎች አንዳች ይፋ የወጣ መግለጫ አልነበረም። ሁኔታውን ከሚያውቁ ከጦር ሰዎች በቀር፣ መሃል አገር ያለው ሕዝብ ሶማሊያ በኦጋዴን አውራጃ ስለተከፈተችብን ታላቅ ጦርነት ተደብቆታል።

ሰሞኑን ግን የሶማሌን የሬዲዩ ጣቢያ ያዳመጡ አንዳንድ ሰዎች ሶማሊያ በኦጋዴን ስለተቀዳጀችው ድል ቀብሪደሃርንና ሌሎቹንም የታወቁ የኦጋዴን ከተሞች መደምሰሷን የምታወራው ወሬ አጠያይቋቸዋል። ወዲያውኑ የወሬው ጭምጭምታ ወላጆቼ ጆሮ ደርሶ አባቴ የሶማሌን የጀርመንና የአሜሪካን የአማርኛ ሬዲዮ ጣቢያዎች በጽኑ መከታተል ይዟል። ይህ አስደንጋጭ ዜና ግን በምንም ዓይነት ወደ እኔ ዘንድ እንዳይደርስ ጥንቃቄ ለማድረግ ቤተሰቡ ተስማምቷል። የወላጆቼም ሆነ የመላ ቤተሰቡ እንዲሁም በቅርብ የሚያውቁን ክርስቲያን ወገኖቻችን ትልቅ ጥያቄ ግን ቀብሪደሃር ከተደመሰሰች ታዲያ ጥበቡ የት ነው የሚል ነበር። ስለሁኔታው የማውቅ መስሏቸው ሊያጽናኑኝም ሆነ ስለ ጥበቡ ሊጠይቁኝ ድንገት ሰዎች ደውለው እንዳያስደነግጡኝ ጥንቃቄ ለማድረግ መኝታ ቤት የነበረውን ስልክ ወላጆቼ "ዕረፍት እንዳይነሳሽ ከዚህ ብናነሳው ይሻላል" ብለው ካጠገቤ ሲወስዱት ቅንጣት ታህል አልጠረጠርኩም።

ብዙም ሳይቆይ የኦጋዴኑ ወረራ መሳከት ሱማሌን የልቁ ልብ ስለሰጣት ዘመቻዋን ወደ ሐረርጌ አውራጃ ቀጠለች። ስለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት ሶማሊያ ያደረገችውን የወረራ ሙከራ የኢትዮጵያ የአየር ኃይሎችና የምድር ጦር ሰራዊቱ መከቶ እንደመለሰ በመግለጽ ማስተባበያ ዜና ማቅረብ ጀመረ። ወዲያውኑ የሐረርና የድሬዳዋ ሕዝብ በሁኔታው እጅግ አሳሳቢነት ምክንያት ወደመሀል አገር እንዲሸሹ ስለተነገራቸው ሕዝቡ ባገኘውና መንግሥት ባቀረበለት ትራንስፖርት ወደመሀል አገር መጉረፍ ጀመረ። ከእነዚህ ዕለታት በአንዱ ምሽት ግን ቤተሰቤ በድብቅና በሚሥጥር ሲሰማው የቆየውን የኦጋዴኑን አውራጃ ጦርነት የኢትዮጵያ ሬድዮ ከርቀት ሲያወራው ድንገት ጆሮዬ ጥልቅ አለ። በታላቅ ድንጋጤ ውስጥ ተዋጥኩ። ዓይኖቼ እንባ እያጎረፉ ዋይታዬን ስቀጥል ወላጆቼና አብረዋቸው የነበሩ ቤተዘመዶቻችን ወደምገኝበት መኝታ ቤት ተደናግጠው ተሰባሰቡ። "ውዴ የት ነው? ጥበቡ የት ነው? ተርፏል ወይ ከዚህ መሃል" እያልኩ አለቅሳለሁ። እንደአጋጣሚ በዚያ ምሽት ወላጆቼን ለቅሶ ለመድረስ ከአዲስ አበባ ናዝሬት የመጣ የቅርብ ዘመዳችን ስለነበር፣ አጠገቤ ቆሞ ሊያረጋጋኝ ከሚሞክረው አባቴ ቀበል አድርጎ እንዲህ አለኝ። ኮሬኔል ግርማ ተሰማ ይባላል። ሊሻን አንዳች አሳብ አይግባሽ። የዶ/ር ጥበቡን ደህንነት በሬድዮ ግንኙነት አማካይነት ከእኛ ጦር አረጋግጫለሁ። እያፈገፈገ በመምጣት ላይ ከሚገኘው ከቀብሪደሃሩ ሠራዊት ጋር ወደ ሐረር እየመጣ ነው። የጊዜ ጉዳይ ነው እዚሁ እቤት ድረስ ነው ከተፍ የሚልልሽ ሲለኝ አመንኩት። በሬዲዮ መገናኛቸው የጥበቡን ከእነርሱ ጋር መሆኑን ለዚህ ዘመዴ ካረጋገጡለት እንግዲያስ በቅርቡ እየዋለሁ ብዬ ጥቂት ተረጋጋሁ። አሁን የምጠባበቀው የሚያፈገፍገው ሠራዊት ሐረር የሚገባበትን ቀን ነው። ለወትሮው የአንድ ቀን መንገድ የነበር ጉዞ ከሳምንትና ከዚያም በላይ ሲዘገይብኝ ግን አሁንም ያን ኮሬኔል ዘመዴን በስልክ አናገርኩት።

የሚያፈገፍገው ጦር የሚጓዘው መንገድ እየመረጠና ከጠላትም እየተከላከለ ስለሆነ ትንሽ

ጊዜ ይፈጃል። እኔ በሬድዮ መገናኛ ሁኔታውን እየተከታተልኩ ስለሆነ አታስቢ ብሎኛል እንደገና። ሆኖም ልቤ አላርፍ ብሎኝ እኔ ተቸግሬያለሁ። በዘመዴ የተሰጣትን ሪፖርት አሜን ብላ መቀበል ነፍሴ አቅቷታል። ከእኔ ሚሥጥሩን ደብቀው ነው እንጂ ሰሞኑን ያልተረጋገጡ ወሬዎች ወላጆቼ ሰምተው እነርሱም በጭንቅ ውስጥ ናቸው።

እናቴ የታያት ከክርስቲያን ወገኖች ጋር በልዑል እግዚአብሔር የምሕረት ዙፋን ሥር በመውደቅ ጸሎትን ሰምቶ ወደሚመልስ በአርያም ወዳለ ጌታ መጮህ ነው። ስለዚህም ናዝሬት ባይብል አካዳሚ ውስጥ ይካሄድ ወደነበር ዓመታዊ የወንጌላውያን አብያተክርስቲያን መሪዎች ኮንፍራንስ ፈጥና ሄደች። መድረክ ላይ ወጥታ ልጄ በሕይወት ይኑር አይኑር አልታወቀምና እባካችሁ ጸልዩልኝ ብላ በሕዝቡ ፊት ወድቃ እየጮኸች ስታነባ የነበረውን ለቅሶና የምልጃ ጸሎት በስፍራው የነበሩ ብዙዎች ያስታውሱታል። ይህ ሁሉ ከበስተጀርባዬ ሲካሄድ ከእኔ ተደብቆ በሚሥጢር ነው። ወላጆቼ በሁኔታው ሲታወኩና መላው ሲጠፋባቸው ከቤት ውጪ እንባቸውን ጨርሰው ይመጣሉ። ከእነዚህ ባንዱ ቀን ነበር እናቴን በኀዘን ፊቷና ልቧ ከብዶ እንባ እየተናነቃት በቤታቸው አጠገብ ስታልፍ ያዩአት አንድ ወዳጅ፤ ምነው የኔ እህት እንዲህ ፊትዎን ከፍት ብሎዎት ወዴት ይሄዳሉ? ምነው የኔ እህት ሲሏት እማለቅስበት ቦታ አጥቼ ነዋ ብላቸዋለች። ውይ የኔ እህት እኔን ይከፋኝ። ኑ ግቡና አብረን እናልቅስ። ኑ ግቡ ብለው ካስገቧት በኋላ እናቴ እዬዬዋን ስታዥጎደጉደው እኚያም ወዳጅዋ አብረዋት እንባቸውን እያዘሩ ካንጀት አላቀሷት። ሁለቱም ለቅሷቸውን ከጨረሱና ጥቂት እናቴ መለስ ካለላት ወዲያ፤ እኚያ ወዳጅዋ ኧረ እንዲያው ለመሆኑ ምን ሆነው ነው እንዲህ አልቅሰው የሚያስለቅሱኝ ብለው ቢጠይቋት እናቴ በሰሞኑ እሷንና መላው ቤተሰቡን ስላስጨነቀው ስለ ጥበቡ ጉዳይ፣ በሕይወት ይኑር አይኑር አለመታወቁን ትነግራቸዋለች። እኛም ወዳጅዋ እጅግ በጣም በሚገርም እርግጠኛነት አይ! እሱ በሕይወት ነው።እንዳችም አልሆነም። አንድ ቦታ እንዲያው በደህና እዳለ ነው እኔ በልቤ የሚሰማኝ ሲሏት ልክ የጥበቡን በሕይወት መኖር እርሷም አረጋግጣ የጨበጠችው ያህል ልቧ እርፍ አለላትና ፊቷን ተጣጥባ፣ በእንባ ያባበጡትን ዓይኖቸዋን በነጠላዋ ሸፋፍና፣ ኀዘኗን የተካፈሉላትን የልብ ወዳጇን አመስግና፣ ወደ ቤት መንገዷን ተያያዘችው። ጥበቡ በሕይወት የመኖሩን ተስፋ ከአምላክዋ በእምነት ተቀብላ በተጽናና ልብ ወደ ቤትዋ ስትደርስ ግን፣ ግቢያችን አጠገብ የቆሙትን መኪናዎች ስታይ ልብዋ ደንገጥ አለ።

ከአዲስ አበባ የእኔና የጥበቡ የቅርብ ጓደኞች፤ ለዓመታት በጸሎትና በጌታ ሕብረት አብረን ብዙ ያሳለፍን የሚወዱት ጓደኛቸው ነገር ሲያዋትታቸው የከረሙና የአያቴን ለቅሶም ሆነ እኔ በመውለዴ ምክንያት ካጠገባችን ያልተለዩን ወገኖቼ ናቸው። ግን በዚህ ሰዓት ምን አመጣቸው? ከወላጆቼ ጋር በስልክና በሚሥጥር የየዕለቱን ስጋታቸውን ሲለዋወጡ ቀናቶች አልፈዋል። አንዳንዶች ዶ/ር ጥበቡ ተማርኳል ይላሉ። አንዳንዶች እያፈገፈገ ከሚመጣው ሠራዊት ጋር ነው ይላሉ። አንዳንዶች በሕይወት ይኑር አይኑር ምንም የታወቀ ነገር የለም ይላሉ። የተረጋገጠ ዜና ሳይኖር ግን ምን ይዘው ወደኔ ይምጡ። ከዚህም የተነሳ እነዚህ ወገኖቻችን በጾም በጸሎት በእንባ አምላካቸውንና አምላካችንን ሲማፀኑት ከርመዋል። ዛሬ ግን በተጨባጭ ጥበቡ ከመማረኩ ጥቂት ሰዓት በፊት ድረስ ከጎኑ የነበረ የዓይን ምስክር አንድ ሰው እግዚአብሔር አምላክ አገናኝቷቸዋል።

የእርዳታ ማስተባበሪያ ሬዲዮ ኦፕሬተር ምናልባት በሃያዎቹ ዕድሜ ክልል ውስጥ የነበረ፤ በዚህ ሥራው ቀብረደሃር ተመድቦ በቆየባቸው ጊዜያቶች የወጣቱ ሐኪም የዶ/ር ጥበቡ ኃይለ ሥላሴ ትጋትና ተወዳጅነት ልቡን የማረከው ወጣት ነው። ምድር ቀውጢ በሆነቺባት በዚያች ማለዳም ሆስፒታሉን ካጨናነቀት ሕዝብ መሃል አንዱ ይህ ወጣት ነበር። የሶማሌ ጦር ዒላማውን ወደ ሆስፒታሉ

እያንጣጠረ ሲገሰግስ ጥበቡ ለቁስለኞቹና ለበሽተኞቹ ሲሯሯጥ አይቷል። ዶ/ር ጥበቡ እስከመጨረሻ ትንፋሹ ሕዝቡ የሚጠጣውን ጽዋ ከመካፈል በስተቀር ራሱን ለማዳንም ሆነ ለማምለጥ ሃሳብ እንዳልነበረውም ወጣቱ ተገንዝቧል። "ዶ/ር ኧረ ነፍሳችንን እናድን! እንዴት ዓይናችን እያየ እዚህ እናልቃለን" ለሚለው የአንዳዶች የጭንቅ አስተያየትና መጫጫህ "ይህንን ሕዝብ በዚህ ሁኔታ ጥዬ ወዴት እሄዳለሁ?" ነበር የጥበቡ ቆራጥ መልስ እንደ ወጣቱ አገላለፅ ። ይህ ወጣት ግን አሰቃቂ ሞቱን እጅ እግሩን አጣምሮ በመቆም መጠበቅ አልታየውምና ነፍሳቸውን ለማዳን የሆስፒታሉን አጥር ዘለው ወደ ቀብሪደሃር የጦር ሰፈር መሮጥ ከጀመሩ አራት ሰዎች ጋር ተቀላቀለ። ከነዚህ ግን ሶስቱ በተባራሪው ፈንጂ ሞተው መንገድ ሲቀሩ፣ ጦሩ ሠፈሩ የደረሱት ሁለቱ ብቻ ነበሩ። የጦር ሠራዊቱ ጓዙን ጠቅልሎ ከቀብሪደሃር ሊፈረጥጥ ሲዘጋጅ በደመነፍሳቸው ደረሱበት! ዓይኑን አፍጥጦ ከመጣባቸው አስደንጋጭ ሞት እንዲያስጥላቸው ሠራዊቱን ሲማጸኑት ግን "እኛ ወደ ጦር ሜዳ ለውጊያ ነው የምንሄደው ከእኛ ጋር ልትሄዱ አትችሉም" ነበር የተሰጣቸው ከእውነት የራቀ መልስ። "የትም ቢሆን የት ሞት እንደሁ አይቀርልንም። ስለዚህ ወደምትሄዱበት እንሄዳለን!" በማለት ሁለቱ ሰዎች ያለጦሩ ፈቃድ በመንቀሳቀስ ላይ በሚገኘው ኮንቮይ ተንጠላጥለው ይሳፈራሉ። ለካስ የኢትዮጵያው ጦር የቀብሪደሃርን ሕዝብ ለአስከፊ ሞትና ምርኮኝነት አጋልጦ መሸሹ ኖሯል። እስከመጨረሻ የደም ጠብታው ለሕዝቡ ላገሩ ሊዋደቅ ይገባው የነበረው ጦር ምስኪኑን ሕዝብ ጥሎ የቀሩትን 14 ታንኮችና ትጥቁን ይዞ ሲያፈገፍግ ያ ወጣት ሰው የኋላ ኋላ ሲገባው የተሰማውን ኀዘን ለመግለጽ እንባ ይተናነቀዋል።

ሆስፒታሉን ዒላማ አድርጎ እንደ አሰፈሪ ማዕበል ከነዋወጠው የጦር መሣሪያ ፍንዳታ መሃል ከቶ ማን በሕይወት ይተርፋል፤ ያስ ዶ/ር ጥበቡ ምን ዕጣ ደርሶት ይሆን ብለዋል ያ ወጣትና አንዳንድ የሠራዊቱ አባላት።

ነፍሱን ለማትረፍ ፈርጣጩን ጦር የሙጥኝ ያለው ይህ ወጣት የጥበቡን በሶማሊያ መማረክ የተረዳው በማፈግፈግ ላይ የሚገኘው ሠራዊት ከፍቶ ያዳምጥ ከነበረው ከሶማሊያ የሬድዮ ጣቢያ ነበር። የተወዳጁን የቀብሪደሃር ሐኪም የዶ/ር ጥበቡን መማረክ የሰማ አፈግፋጊው ጦር እርስ በርሱ "ኤዲያ! እሱን ነበር የጦር መሪ ጀኔራል ማድረግ ሲል፤" ገሚሱ እንዴ! "እሱን ሞትም ሆነ ምርኮ እንዳያገኘው ሠራዊቱ የማፈግፈግ ውሳኔ ላይ ሲደርስ እኮ ከጦሩ እንዲቀላቀል ተነግሮት ነበር። የሥራ ጓደኞቹስ? ሕዝቡስ? ሁላችንንም ካልሆነ የምታወጡትን ጥያቸው መሄድ አይሆንልኝም፤ ብሎ ነው ለዚህ የተዳረገው። ይበለው በጦር ሠራዊቱ ያልተገኘ አጉል ጀብደኝነት" ብለው የሚተቹት እንዳሉ ሁሉ፤ ጥበቡን ቀረብ ብለው የሚያውቁትና የሚያደንቁት ደግሞ "እንኳን ብቻ የቅንነቱ አምላክ ታደገው፤ በሕይወት ካለ እግዜር ያውቅለታል" የሚሉም አሉ። ለወትሮው በሰላሙ ጊዜ የሕዝብ መመላለሻው አውቶቡስ ከሐረር ከተማ ከጠዋቱ በአንድ ሰዓት ተነስቶ ከሰዓት በኋላ ወደ 11 ሰዓት ገደማ ቀብሪደሃር ከተማ ይገባ ነበር። ሆኖም ግን የሶማሌው ጦር አጋዴንን በአብዛኛው ተቆጣጥሮት ስለነበር አፈግፋጊው የኢትዮጵያ ጦር ከቀብሪደሃር ይዟቸው ከተነሳው 14 ታንኮች አንድ ብቻ ሲቀረው ሸሽቶ በ23ኛ ቀኑ በጭንቅ ሐረር ከተማ ገብቷል። ጀግናን ማስተናገድ የለመደው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅስሙ ተሰብሯል። ስለዚህ በቁጣና በቁጭት የተሞላው የሐረር ከተማ ሕዝብ ሸሽቶ ገቢውን ጦር በእልልታ አልተቀበለውም። "ሞት ለእነ እከሌ! ሞት ላፈግፋጊው ጦር" በማለት የጦር ብርጌዱን መሪዎች ስም በትልልቁ ጽፎ ለተቃውሞ በሰልፍ ወጥቷል።

ከሞትና ከምርኮ የተረፈው ያ ወጣት፣ ለወሬ ነጋሪ የበቃውና አዲስ አበባ የገባው ይህን በመሰል የታሪክ ገጽታ ውስጥ አልፎ ነበር። አዲስ አበባም በገባ ዕለት በጾም በጸሎት በአምላካቸው

ፊት ከሰነበቱት ከቅርብ ጓደኞቻችን መሃል በወቅቱ የፖሊስ ሆስፒታል ሐኪም የነበረው ዶ/ር ፍስሐ ጉርሜሳ ያገኙዋል። የወጣቱ ሃሳብ አዋሳ ወደሚገኙት ወላጅ እናቱ ወዲያውኑ ተሳፍሮ መጓዝ ቢሆንም "ዶ/ር ጥበቡ የደረሰበትን ትክክለኛውን ሁኔታ በማጣራት ላይ ስለነበርን የተረጋገጠና ተጨባጭ ወሬ እስክናገኝ ለባለቤቱ ለመንገር ተጨንቀን እስከሁን በሚሥጥር ይዘነው ቆየን። አሁን ግን ፈቃድህ ቢሆን አብረኸን ወደ ናዝሬት ብትሄድልን ምናልባት ከአንተ እንደበት ብትሰማ ኀዘኗን ያቀልላት ይሆናል" ሲል ላቀረበለት ልመና ወጣቱ ሳያመነታ "በደስታ እሄዳለሁ። ሕይወቱን ለሕዝብ ሲል ለሰዋው ለዶ/ር ጥበቡ እንኳን ይሄን ሌላም ባደረግሁ ደስ ባለኝ" ብሎታል። ጓደኞቹ ታላቅ ወንድሜን ገብሩን ጨምረው ያን ዕለት ናዝሬት የመምጣታቸው ምክንያት ይሄን መራራ መርዶ ለእኔ ለማርዳት ነበር።

እኔ ከማለዳ ጀምሮ ልቤ ይሸበራል። ከረምት የማይበረታበት የናዝሬት ከተማ እንኳን ኃይለኛ ዶፍ ዝናብ የጣለበት ቀን ነው። አባቴ ወጣ ብሎ ከነበረበት ገና መግባቱ ነው። በሚሥጥር ከእኔ በስተጀርባ የሚያጣራውን የጥበቡን ጉዳይ እንዳንዱ መማረኩን ሌላውም መሞቱን ሲነግረው ልቡ በኀዘን ቁጋግ ተሞልቶ መግባቱ ኗሯል። ሁሉንም ያላወቅሁ እኔ ግን ገና እንደገባ ሳሎን አብሬው ቁጭ ብዬ የምጠይቀው ጥያቄ "አባዬ! በማፈግፈግ ላይ አለ የተባለው የጦር ሠራዊት እንዴት እስከሁን ሐረር መግባት ይሳነዋል" የሚል ነበር። ለሚወዳት ልጁ እንኳንስ ይህን ገና ያላጣራውንና ያልተጨበጠውን ከፉ ወሬ ቀርቶ፣ እውን ቢሆን እንኳን እንዲህ ብቻውን ቁጭ አድርጎ የሚያረዳት መርዶ እንዳይደለ ያውቃል። ላቀረብኩለት ጥያቄ ጥንቃቄ የተሞላውን መልሱን ሊሰጠኝ በልቡ ሲጨናነቅ ድንገት የሳሎኑ በር ተንኳኳ። ፊጥኜ በመነሳትም በሩን ስከፍት ቁጥራቸው ትንሽ ያይደለ የቅርብ ጓደኞቻችንና ታላቅ ወንድሜ በመካከላቸው ከሚገኘው አንድ እንግዳ ሰው ጋር ሰላምታ እየሰጡን ገብተው ተቀመጡና ጥቂት የሚቀፍ ጸጥታና ዝምታ በሳሎኑ ውስጥ ሆነ፤ ወዲያው ታላቅ ወንድሜ ጉሮሮውን ጠራረገና ዛሬ ስለወንድማችን ስለ ዶ/ር ጥበቡ ሁኔታ ትክክለኛውን የሚነግረን ይሄን ወንድማችንን ስላጋጠመን ከእርሱ እንድንሰማ ይዘነው መጥተናል፤ ሲል ልቤ በታላቅ ድንጋጤ ተሞላ። ነፍሴን ወጥሮት የነበረውን ጥያቄዬን ሳስተጋባ እፍታም አልቆየሁም። "እ! እሺ! የት ነው ጥበቡ ? የሚያፈገፍገው ሠራዊት የት ደርሷል?" ለሚለው ሰቆቃዬ ምላሹ ግን "ዶ/ር ጥበቡ በሶማሌዎች ተማርኮ ባሁኑ ጊዜ የሚገኘው ሞቃዲሾ ውስጥ ነው። በሕይወትና በደህና ሁኔታ ላይ። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ትገናኛላችሁ።" ከእንግዳው ሰውዬ አንደበት የወጡት እነዚህ እንግዳ ቃሎች በሕልሜም ሆነ በእውኔ ፈጽሞ ያልጠበቅኳቸውና እጅጉን አስደንጋጭ ሆኑብኝ። ስለዚህም ነፍሴ በታላቅ ጨለማና ነውጥ ውስጥ ተዋጠች። መኖሪያ ዓለማቸው ድንገት ሳያስቡት እንደፈራረሰባቸው የሰው ልጆች፤ ነፍሴ ይህ ነው በማይባል አስፈሪ፥ ነጎድጓድና ድቅድቅ የኀዘን ጨለማ በድንገት ተከበበች። የእናቷን ጡት እንዳስጣሏት ሕፃን ሰቅቅ እያለች በመራራ ለቅሶ መንፈራፈር ጀመረች። የእኔን እርብትብትነትና ኀዘን አጥባቂነት የሚያውቁ ወዳጅ ዘመዶቼ የፈሩትና የሰጉትም ይሄንኑ ነበር። ያን አስደንጋጭና ማንም ያልጠበቀውን አሳዛኝ ዜና የሚስከትልብኝን ከባድ የልብ ስብራት ነበር የፈሩት። በዓይናቸው ፊት ኀዘን ላነካከተው ማንነቴና በጠላት እጅ ለወደቀው ጥበቡ እነርሱም በየፊናቸው እንባቸውን ማፍሰስ ጀመሩ።

እናቴ ከእኝያ ወዳጅዋ አፍ የተነገራትን አጽናኝ ቃል ጨብጣ ቤቷ የደረሰችው እኔ በመራራ ሁኔታ በማልቀስ ላይ ሳለሁ ነበር። የኀዘን ድባብ የወደቀበትን ሳሎን በር ከፈት አድርጋ እንደገባችም እንባዬ ውስጤን እየፈነቀለው "እማዬ የምንጠብቀው ጥበቡ የለም! ሶማሌዎች ማርከው ወስደውታል! ጥበቡ ተማርኮአል.." አልኳት። የእናቴ ምላሽ ግን "እሰይ! እሰይ! እምላኬ

ተመስገን!" የሚል ቢሆንብኝ ግራ ተጋብቼ "ምነው እማዬ ጥበቡ ተማረከ ነው እኮ ነው የምልሽ! መማረክ ምን እሰይ ያሰኛል" ብዬ እሪታዬን ለቀቅሁት! እናቴም በተረጋጋና ጠንከር ባለ ድምፅ "ልጄ ስሚኝ! እኔ የፈራሁት አምላኬንም የተማፀንኩት "ሞተ" የሚለውን ቃል ጆሮዬ እንዳይሰማ ነበር። አሁን ግን ጥበቡ በሕይወት አለ፤ትገናኛላችሁ። ሰው ከሞተ ወዲያ ከወደት ይመጣል? የፈራሁትን ሞት የከለከለ እግዚአብሔር ይመስገን።" እኔ ለራሴ ፍቺ ባላገኘሁላቸው አስደንጋጭ ቅዠቶችና በተወሳሰቡ መራራ ጥያቄዎች ተከብቤ እናቴ ጌታን የምታመሰግንበት ምክንያት አልታየኝም። የዚያ መልክም የእግዚአብሔር ሰው፣ የጥበቡ ኃይለሥላሴ አምላክ ወዴት ነው? የትዳሬና የቤቴ አምላክ ወዴት ነው? ሌላ ሌላም . . ! ከጎኔ ተቀምጦ የነበረው ዶ/ር ፍስሐ ጉርሜሳ በኀዘን የሚንዘፈዘፈውን ትከሻዬን ያዝ አደረገና "ቆይ እስቲ ስሚኝ ሊሽዬ! አንቺ እኮ የወለድሽው ጥበቡ በተማረከበት በዚያው ሐምሌ 17 ቀን ነው። ልትጽናኚ ይገባል..." ብሎ ሲናገረኝ ጆሮቼ ሰሙት። ጥበቡ የተማረከው ሐምሌ 17 ቀን ነው። ሁለተኛ ልጃችንን የወለድኩበት ...እያቴ ያረፈችበት... ሐምሌ 17 ቀን ነው ።

ድንገትም አንድ የሚያስደንቅ ነገር በውስጤ ተካሄደ። ቅጽበታዊ ወደሆነ አስገራሚ ተመስጦ ነፍሴ ሳታውቀው ገባች። ነፍሴ በሰመመን ሆና በመንፈስ የምትሰማው የመለኮት ድምጽ ከአርያም ሲምዘገዘግ መጣ። ልትከደው የማትችለው እውነት በፊቷ አሁን እያለፈ ነው። ተራ በተራ ነጥብ በነጥብ እንደፊልም በፊቷ በሚታያት ትእይንት ሁሉ፣ በእርግጥ የአምላከዋን እጅ ትመለከት ጀመር። እኔና ጥበቡ ሁለተኛዋን ልጃችንን ቀብሪደሃር ሆስፒታል ለመውለድ በነበረን እቅድ ጌታ እግዚአብሔር ጣልቃ መግባቱ፤ በጦርነት ቀን ምጤ እንደሚሆን ያወቀ ጌታ በኪነጥበቡ ከቀብሪደሃር እንድንወጣ ማድረጉ፤ መንግሥት ያወጣው ሕግ ጥበቡን እንዳያግደው ማንም የጤና ባለሞያ የዓመት ፈቃድ እንዳይወስድ ደርግ ከበተነው ሰርኩላር ጋር በአውሮፕላኙ መተላለፋችን፤ ከጥበቡ ጋር ወደ ቀብሪደሃር ለመመስ ሁለት ቀን ሲቀረን የሥራ ባልደረባው ባደረገለት ስልክ ምክንያት ጥበቡ ከእኛ ተለይቶ መሄዱ፤ ዲያብሎስ መላ ቤተሰባችን ለመደምሰስ ካዘጋጀው ወጥመድ ጌታ እኛን መታደጉ፤ የሰው ልጅ እንደቅጠል ከረገፈበት የሞት ማዕበል ውስጥ፣ እግዚአብሔር በሕይወቱ ላለው ዓላማ ጥበቡን ማትረፉ፤ ለብርቱ ሰልፍ እንደሚዘጋጅ ንቁ ወታደር፣ ጌታ እግዚአብሔር የጥበቡን ሕይወት ለዓመታት ሲያዘጋጀው መቆየቱ፤ በምርኮ ምድር አምላካቸውን ስላስከበሩት ስለነዳንኤል፣ ሲድራቅ ሚሳቅና አብድናጎ፣ ስለ አስቴርና መርዶክዮስ፣ ስለነንህምያና እዝራ... ቀብሪደሃር እንደ ቤተሰብ ባሳለፍናቸው ወቅቶች አበክረን እድናጠና ጌታ እግዚአብሔር ማድረጉ፤ እኛን ደካማዎቹንና ኋላም ታናሽ ወንድሜን አስወጥቶ ለዚህ ሥራው የሚፈልገውን ጥበቡንና በጸሎት የሚረዳውን ኢያሱን ለይቶ መውሰዱ፤ የስንቱ ንብረትና ሃብት እንዳለ ሲወድም፣ ጠፊና ከንቱ ለሆኑት የቤት እቃዎቻችን እንኳን ሳይቀር ጌታ ጥንቃቄ ማድረጉ፤ ነፍሴ የማታስተባብላቸው እውነቶች ነበሩ። ስለዚህም እነዚህና ሌሎች ልከዳቸው የማልችላቸው ሐቆች ስረዳ "እግዚአብሔር ጥበቡ ረቂቅ ነው። በሥራውም ሁሉ ጻድቅና ትክክል፤ የሚያደርገውንም ሁሉ የሚያውቅ አምላክ ነው" የሚሉ ድምጽየለሽ አዋጆች በመላ ሰውነቴ ውስጥ ይሰተጋቡ ጀመር። ተሰባብሬ ከተወረወርኩበት የኀዘን ሸለቆ መንጥቆ የሚታደገኝ አዋጅ፤ የተወረወረችበትን ድቅድቅ ጨለማ ጥሶ የሚያልፍ የሰማይ ብርሃን ኀዘን ባኮራመተው የውስጥ እኔነቴ ላይ በራ። ጨለማዬን የሚያበራ የሰማይ ብርሃን፤ የውዴም የእግዚአብሔር ቃል በክበቡኝ አስፈሪ ተራራዎች ላይ እየዘለለ እንዲህ ሲል መጣልኝ። "ልጄ ሆይ! የማደርገውን የማውቅ አምላክሽ እኔ እግዚአብሔር ነኝና አይዞሽ። ባሪያዬን ለሥራዬና ለከበረ ዓላማዬ ወስጄዋለሁ፤በዚያ ያለኝን ዓላማዬን ስጨርስ አመጣዋለሁ። እርሱ የሚተወውን ሸለቆ እኔ እሞላዋለሁ።" በቤት ውስጥ ከሞሉት ሰዎች ሁሉ እጅግ የቀረበ የጌታዬ መገኘት ዙሪያዬን የሚዳስስና የሚጨበጥ ያህል ይሰማኛል። ይገርማል!

ቅዱስ እግዚአብሔር እኔን ለማጽናናት ከሰማይ ወርዶ ጎኔ ያለ ያህል ቅርበቱ ሲታወቀኝ፣ በቤት ውስጥ የሞሉት ወገኖቼ ግን ከበስተውጭ ፊንጠር ብለው እንደቆሙ ያህል ነበሩ! ነፍሴ በሚገባት መንገድ ለጥያቄዎቼ ሁሉ በቂ ከበቂም በላይ የሆነ መለኮታዊ ምላሽ አገኘች! ደመናትን ሰንጥቆ ለረድኤቷ ደርሶላታልና ፈጥናም ከአምላክዋ ጋር ነፍሴ ተስማማች! አእምሮንም ሁሉ የሚያልፈው መለኮታዊ ሰላም ሁለንተናዬን ሲያጥለቀልቀው ታወቀኝ። በእርግጥ እግዚአብሔርን ለምንወደው እንደሃሳቡም ለተጠራነው ለእኛ ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሚሆን የሚያምን ጉልበታም ልብ ተሰጠኝ፤ አዎን የሚደንቅ ነው። ከዚህ ሁሉ በስቲያ አምላካችን በእኔና በጥበቡ በልጆቻችንም ላይ ያለው የፍቅር ዓላማ ቁላንቁሉ ታየኝ።

በእርግጥ ጌታዬ ሆይ አንተ የምታደርገውን የምታውቅ አምላክ ነህ። በፍጹም እምነት፤ በጾም በጸሎት በፊትህ ስሌን አንጥፎ ቆሎ ቆርጥሞ ራሱን ማዋረድ ያስተማረከው ፤ አንተን መሻት ጥበቡን ያለማመድከው፤ ለዚህ ከባድ ጥሪ እንደሁ አሁን ገብቶኛል። ብርቱ እምነትና ጸጋ የሰጠኸው፤ ጥበቡ ትክክለኛ የፍቅርህ መልእክተኛ ነው። አምላኬ ሆይ! ወደዚያ እርሱን የወሰድክበትን ዓላማ ስትጨርስ ደግሞ ወደ እኛ እንደምታመጣው ስለተናገርከኝም አመሰግንሃለሁ። እንግዲህ እኔን ደካማዋን የሚረዳው ጸጋህ አይለየኝ! ያልከውን እስከታደርግም አንተን በትዕግሥት የምጠብቅበትን ጸጋ ስጠኝ በማለት በፍጹም ልቤ ከአምላኬ ጋር ተስማማሁ። እናም ከሰው እይታ ውጭ በውስጤ ከተከሄደው መለኮታዊ ገለጻ የተነሳ ነፍሴ ለገጠማት እንቆቅልሽ ፍቺዋን አግኝታ የከበባትን ጨለማ ጥሳ ወጣች። የደካማዋና የእርብትብትዋ ሊሻን ታሪክ ብርቱና ሁሉን ችሎ በሚያስችለው እግዚአብሔር ተለወጠ። ነፍሴ በተጽናናችበት መጽናናት ከእኔ ውስጥ ኃዘንተኞችን የሚያጽናና መልእክት መፍለቅ ጀመረ። በዚያን ሰሞንም የጥበቡን በሶማሌዎች መማረክ አስደንጋጭ ዜና የሰሙ ክርስቲያን ወገኖች ከቅርብና ከሩቅ በአካል በስልክ በደብዳቤ እኔን ለማጽናናት ይጎርፉ ጀመር።

አንዳንዶች በሁኔታው ከተሰማቸው ኀዘን የተነሳ እላዬ ላይ እየተጠመጠሙ ድምጽ አልባ ንግግራቸውን በእንባቸው ተረኩልኝ።

አንዳንዶች ባለማስተዋል የስንፍና ቃል ሲናገሩ ሌሎች አምላኬንና አምላካቸውን የማይገባ ጥያቄ ይጠይቁት ነበር። ከነዚህ መሃል አንድ የማልረሳው ገዛኸኝ የተባለ ወጣት ነበር። በቀብሪደሃሩ አገልግሎታችን ወደ ጌታ ከመጡት መሃል በመንፈሳዊ ሕይወቱም ገና ለጋ የነበረ። ለእኛ ከነበረው ፍቅርና ቅርበት የተነሳ ሲያስተዛዝነኝ እንባውን ትከሻዬ ላይ እያዘራ "እኔ ሊገባኝ አይችልም። በእርጥቡ እንጨት በጋሽ ጥበቡ ላይ እግዚአብሔር እንዲህ ከደረገ እኛንማ ቢያገኘን ምን ሊያደርገን ነው" ያለው ትዝ ይለኛል። ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ሁሉ የእኔ መልስ ግን "አይዟችሁ! ጌታ እግዚአብሔር በእኔና በእናንተ አይታማም። እርሱ ባሪያውን ለብርቱ የፍቅር ተልዕኮ ወደ ሶማሊያ ልኮታል። ሥራውን ሲጨርስ ወደ እኛ ይመልሰዋል። ጥበቡ ለሰልፍ እንደሚዘጋጅ ወታደር ለዓመታት እግዚአብሔር ሲያዘጋጀው የቆየ የጌታ ባሪያ እንደነበር እናንተም ምስክሮች ናችሁ። ይልቁኑ በዚያ የሄደበትን የጌታ ዓላማ አጠናቆ በህያዋን ምድር እንዲያገናኘን በእምነት አብራችሁኝ ቁሙ" የሚል ነበር። ከአንደበቴ የሚወጣው ቃል ብዙ ጊዜ ራሴንም ይደንቀኝ ነበር። በእርግጥ ተፈጥሮዋዊዋ ሊሻን ይህን ማለት እንደማትችል አውቀዋለሁና። ነገር ግን ከአምላኬ ከተቀበልኩት የተስፋ ቃል የተነሳ ነበር። ባለመናወጥ የሚያናግረኝም ከአምላኬ የሰማሁት ያ ድምጽ ነበር።

****

# 11

## ደናን

ጥበቡና አብረውት በማእከላዊ ወህኒ ቤት የተጨመሩት ከሁለት ሳምንት ቆይታ በኋላ ደናን በምትባል የሶማሊያ ወደብ ወደሆነች አንድ ጥንታዊ የሶማሊያ እስር ቤት ተወሰዱ። የደናን እስር ቤት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ጣሊያን ደቡብ ሶማሊያን ወርራ በነበረበት ጊዜ የተቋቋመ ወህኒ ነው። ከውጭ ለሚያየው የማይደፈር ጥንታዊ ምሽግ ይመስላል። ከምድር ወደ ላይ ከፍታ እና በረዥሙ የታጠረው የድንጋይ ቁንብ የወህኒውም የውስጥ ግድግዳ ስለሆነ ትናንሽ መስኮቶች በግንቡ ዙሪያ ይታያሉ። በቅጥሩ ግቢ ውስጥ የሚገኙት እስር ቤቶች በዚሁ የውጭ አጥር ላይ ዙሪያውን በክቡ ተገጥመው ተከፋፍለዋል። ወታደሮቹ በየቀኑ እስረኞቹን ከክፍላቸው እያወጡ በግፍ እየደበደቡና እያዳፉ ወደ ተለያየ የጉልበት ሥራ የሚያሰማሩበት ትልቅና ሰፊ ክፍት ሜዳ ግቢው መሃል አለ። በየጊዜው ቁጥራቸው እየናረ የመጣውን ኢትዮጵያውያን ምርኮኞች ሁሉ ለዘጠኝ ወራት ሶማሊዎቹ አፍነው የያዙት እዚሁ ግዙፍ ምሽግ ውስጥ ነበር። የደናኑ እስር ቤት ሲቪሉንም ሆነ ወታደሩን ወንዶችንና ሴቶችን ሕፃናትንም ጨምሮ በአንድነት ያስጎነጫቸው መራራ የመከራ ጽዋ አልበቃውም። በሕመም በጉስቁልና ከወታደሮቹ በሚሰነዘርባቸው ከባድ ድብደባና ስቃይ ብዙዎች ወገኖቻችንን በሞትም አስናብቷል።

የሴት እስረኞች የታጎሩበት ከወንዶቹ እስር ቤት ወጣና ፈንጠር ብሎ ነው። የእያንዳንዷ ሴት እስረኛ የመኝታ ቦታ ልኩ አሥራ ስድስት ኢንች ስፋት ስድስት ጫማ ርዝመት አለው ለየግል ተለክቶ የተሰጣቸውን ቀጭን ስሴን አንጥፈው ደረቁ መሬት ላይ ስለሚተኙ ወሰንና ድንበራቸውን ያውቁታል። አንዳንድ ብርድልብስና መጠጫ የቆርቆሮ ጣሳም ታድሏቸዋል።

በሴቶቹም ሆነ በወንዶቹ እስር ቤቶች መሀል የሚገኝ ትንሽ ከፍተት ያለው አንድ ስፍራ የተያዘው በትልቅ ጉርድ በርሜል ነው። በርሜሉ እንዲከደን አይፈቀድም። እስረኞቹን ወደ የክፍላቸው አጉረው ከቆለፉባቸው ወዲያ መጸዳዳት የሚያስፈልገው ሁሉ ችግሩን የሚወጣው እዚያ ጉርድ በርሜል ውስጥ ነው። ሌሊቱን በሙሉ የተከማቸው ሽንትና ዓይነምድር ወጥቶ የሚደፋው ጠዋት እስረኞቹ በሩ ሲከፈትላቸው ነው። እያንዳንዱ እስር ቤት ካለው የሕዝብ ብዛት ጋር ሙቀቱና ላቡ በየጉርድ በርሜሉ ከተጠራቀመው ቆሻሻ ጋር ተቀላቅሎ የሚፈጥረውን አስጨናቂ ግማትና ሽታ

በሰው ቃላት ለመግለጽ ይቸግራል።

እስር ቤቱ አንድ ክሊኒክ ነበረው። ጥበቡ ወደ ክሊኒኩ የተጠራው ደናንን እግሩ እንደረገጠ ነበር። ነጭ ጃኬት የለበሰ አንድ ወጣት ሶማሌያዊ ሰው ከአንድ ትንሽ ጠረጴዛ ኋላ ተቀምጧል። ሞቅ ባለ ሰላምታ ጥበቡን ከተቀበለው በኋላ ራሱን ሲያስተዋውቀው ስሙ አብዲ አብዱሌ እንደሚባል ነግሮታል። የዚህ ክልልና የደናን እስር ቤትም ሐኪም ነው። ጥበቡ ኃይለሥላሴ፤ አንተ የአዲስ አበባ ሐኪም ነህ። ምን እግር ጥሎህ ለዚህ በቃህ!

ወጣቱ ሐኪም በጥበቡ ላይ ለማሾፍ ወይንም ለመቀለድ ሳይሆን ከልባዊ ኀዘኔታ መሆኑ ከፊቱ በግልጽ ይታያል። ጥበቡ የሆነውንና ለዚህ የበቃበትን ምክንያት ገለጸለት። ቤተሰቦቹ የት እንዳሉ ጥበቡን ሲጠይቀው በሰማው ነገር ሁሉ የተሰማውን ኀዘን አብዲ አብደሌ መሸሸግ አልቻለም። አንተ የኦጋዴንን አውራጃ ለቀህ ወደ ቤተሰብህ ገና ድሮ መሄድ ነበረብህ። ይሄ ሁሉ አሳዛኝ ገጠመኝ ባልደረሰብህም ነበር። የሶማሊያዊው ሐኪም ሰብአዊ ርህራሄና አስተሳሰብ፣ እርሱንም በጠላትነት ዓይን አለመመልከቱ ጥበቡን ደስ አሰኘው። ከዚህ ሰው መገናኘቱና ውይይቱም ወዴት እንዲያመራ ጥበቡ በልቡ ሲያሰላስል ሳለ አንተ የጦር ምርኮኛ ነህ። ያን በሚመለከት ምንም ላደርግ አልችልም። አንድ ነገር ግን እንድታውቅ እፈልጋለሁ። ለዚህ ወህኒ ቤት እጅግ ታስፈልጋለህ። በጦርነቱ ምክንያት ብዙ ህመምተኞችና ቁስለኞች አሉ። እኔ እዚህ ወህኒ ቤት ውስጥ እነርሱን ለማከም የምችልበት ጊዜ የለኝም። ስለዚህ የእስርቤቱን ክሊኒክ ሥራ አንተ ትረከባለህ። ጥበቡ የተሰጠውን ኃላፊነት ገና በማሰላሰል ላይ ሳለ አብዲ አብዱሌ፤ የግል የመኝታ ቤት እንዲዘጋጅልህ ደግሞ አሁኑኑ አደርጋለሁ በማለት ከመቀመጫው ተነሳና እጁን በሰላምታ ዘረጋ። ከዛሬ ጀምሮ አንተ የዚህ ወህኒ ቤት ዶክተር ነህ። ተስማማን አይደል?

ጥበቡ ምን መልስ መስጠት እንዳለበት ግራ እስኪጋባ ድረስ ድንገተኛና ያልጠበቀው ሁኔታ ነው የገጠመው። የዚህን ሥራ ኃላፊነት ሶማሌዎቹ ለእርሱ ይተውለታል ብሎ ማንም ቢሆን አይገምትም። ጥበቡ የአብዲ አብዱሌን የተዘረጋ እጅ ጨበጠና ስምምነቱን አረጋገጠ። አብዲ ወዲያውኑ ጥበቡን ይዞ ወደ ወህኒው አመራር ወሰደውና ለጥበቡ ያዘጋጁለትን የመኝታ ቤት ቁልፍ ተቀብሎ ሰጠው፤ ወደዚያውም ይዞት አመራ። የጥበቡን መኝታ ቤት ሁኔታ በዓይኖቹ ለማየት አብዲ አብሮት ወደ ክፍሉ ገባ። አብዲ በክፍሉ ውስጥ ወዳለው የጣውላ አልጋ እያመለከተ፤ ፍራሽ ባስቸኳይ እንዲገዛልህ አደርጋለሁ። በጠላት ተማርከው በታሰሩ የሀገሩ ወገኖች መከከል እርሱም እራሱ እስረኛ ሆኖ ሳለ ለእርሱ የተለየ ምቾትና እንክብካቤ ሲደረግለት ማየቱ አሳፋሪና ለልቡም ከባድ ሆኖ ተሰማው። ስለዚህ ይህን ድንገተኛና ያልጠበቀውን እንክብካቤ ከወገኖቹ ተነጥሎ መቀበል ተናነቀው፤ አያስፈልገኝም ሲል ጥበቡ ተቃወመ። ስሌንና ብርድልብስ አለኝ በዚያ እጠቀማለሁ አለው።

በዚያ ምሽት ጥበቡ በዚያ ደረቅ አልጋ ላይ መጽሐፍ ቅዱሱን ይዞ ቁጭ አለ። አሁን ምርኮኛ ሆኖ ወደ ሶማሊያ የተወሰደበት ምክኒያት ስለበራለት ጌታ እግዚአብሔር አምላኩን ከልቡና ከነፍሱ በመነጨ ምስጋና አመሰገነው። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትንና ለከባድ ስቃይ የተዳረጉትን ወገኖቹን የሚረዳበትን መንገዱን ትኩር ብሎ ተመለከተ።

መጽሐፍ ቅዱሱን ከፍቶም የዮሴፍን ታሪክ አነበበ። ዮሴፍ በወንድሞቹ ተሸጦ ወደ ባዕድ ምድር ከተወሰደም በኋላ አሳዛኝና ከባድ ፈተናዎች ውስጥ አልፏል። ወንድሞቹ ያደረጉበትን ክፋ ሁሉ ግን እግዚአብሔር አምላክ ወደ መልካም ለውጦ ወገኖቹን ከጽኑ ረሃብ የእስራኤልንም ሕዝብ ከመደምሰስ ለማትረፍ ዮሴፍን ተጠቀመበታል።

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! እኔንም ባሪያህን ኢትዮጵያዊው ዮሴፍህ አድርገህ ትጠቀምብኝ

ዘንድ ራሴን በፊት እጥላለሁ በማለት ከጸለየ በኋላ ደረቅ አልጋው ላይ ሰሌኑን አንጥፎ በከባድ እንቅልፍ ተወሰደ።

****

## ያ ወጣት ማንነው?

በሚቀጥለው ቀን ማለዳ አብዲ የውስጥ መቀያየሪያ ልብሶች፣ የሽንት ቤት ወረቀቶች፣ ፎጣና የሐኪም መመርመሪያ መሣሪያዎች ይዘለት መጣ። ጥበቡ ለእስረኞች የታደለውን የወህኒ ልብስ ሳይሆን የፈለገውን የራሱን ልብስ መርጦ እንዲለብስ ተፈቀደለት። በወቅቱ አስፈላጊውን ሁሉ ስላመቻቹለት ጥበቡ ሥራውን ዕለቱኑ ለመጀመር ጊዜ አልፈጀበትም። የሥራው ብዛት እጅግ ከመጠን ያለፈ ነው። ጥቂት ሳይቆይም የዝናብና የሙቀት ወራት እንደአሸን ያፈላቸው የወባ ትንኞችና ንፅህና የጎደለው ውሃ፣ ይህ ነው የማይባል ታላቅ የጤና ቀውስ በምርኮኞቹ ላይ አስከተለ። በወባና በተቅማጥ በሽታ ብዙ ሰዎች ተረፈረፉ። በተለይ በተመጣጠነ ምግብ እጦት የተጎዳው የልጆች ሰውነት ተቅማጡ ያስከተለበትን ችግር ሊቋቋመው አልቻለም።

ጤና ገንቢ በሆነ ፕሮቲን/የተመጣጠነ የገንፎና የአጥሚት እህል ባስቸኳይ እንዲዘጋጅ ጥበቡ የወህኒውን አመራር ኮሚቴ አስረድቶና ተሟግቶ አሳመነ። በዚያም ምክንያት የብዙ ልጆች ሕይወት ከሞት ተርፏል። ሆኖም ግን ያም ሊረዳቸው ሳይችል ቀርቶ የሞቱ ሕፃናቶች በርካታ ነበሩ። እስረኛ እናቶቻቸው መሪር ለቅሶ እያለቀሱ የልጆቻቸውን አስከሬን ከወህኒው ቅጥር ውጪ ቀብረዋል።

ጥበቡ በደናን ክሊኒኩ ውስጥ የሚያክመው ሲቪሉንና በጦርነቱ ቆስለው የተማረኩትን ወታደሮችንም ጭምር ነው። የቀብሪደሃር ሆስፒታል ልምምዱ በተለይ በእነዚያ በማይረሱ የመጨረሻ ቀናት የጦር ቁስለኞቻችንን ማከሙ ለአሁን ሥራ በእጅጉ ረድቶታል። የቆሰሉትን በማከም ፤ ቆዶ ጥገናም ቢሆን የሚያስፈልገውን እርዳታ በመስጠት፤ እግዚአብሔር አምላኩ፣ ጥበቡን ለምርኮኛው ሠራዊት አለኝታ አድርጎታል። ከምድር በሞት የሚሰናበቱት ወገኖቹ የልብ ትርታ እስከትቆም እስከመጨረሻ ትንፋሻቸው ከጎናቸው ሆኖ ወደ ዘላለሙ ኑሮ ሸኝቷቸዋል። ነፍሰጡር እንደሆኑ የተማረኩ እናቶች በምጥ ሲያዙ በሰላም እስኪገላገሉ ድረስ ጥበቡ ከአጠገባቸው ሳይጠፋ ምርኮኛ እራሶቻቸውን ወደዚህ ዓለም ተቀብሎላቸዋል።

የኦጋዴን ጦርነትና ፍልሚያ በቀጠለ መጠን የምርኮኞቹም ብዛት በየዕለቱ እየጨመረ መጣ። ከሕዝቡም ብዛት የተነሳ የደናን እስር ቤት ጠበበና ምርኮኞቹ የራሳቸውን ወህኒ እንዲሰሩ እንቅስቃሴ ተጀመረ። ተጨማሪ ወህኒ ቤቶች የሚሰራበት አሸዋ ከሕንድ ውቅያኖስ ያግዙ ዘንድ ምርኮኛው በፀሐይና በሀሩር መከራውን ይበላ ጀመር። ሲሚንቶ እየፈጨ ድንጋይ እየጠረበ የሚታገርበትን ጉርኖ እንዲሰራ ተገደደ።

የደናኑ ወህኒ ቤት ግንባታ ሲነሳ ብዙ የመረረ አሳዛኝ ትዝታንም አብሮ የሚቀሰቅስ ይሆናል። ረሃብና ግርፋት እንዲያ ያጨማተራቸው ኢትዮጵያውያን ምርኮኞች ደፋ ቀና ሲሉ በተቀዳጁት ድል የሰከሩት የሶማሌ ወታደሮች ደግሞ እንደኩሩ አውራ ዶሮ በዚያ አሸዋማ ወደብ ሲጎማለሉ ይታያሉ። አጋጣሚውን ባገኙ ቁጥር ደግሞ በቁጥጥራቸው ስር ያደረጓቸውን ኢትዮጵያውያን ጠላቶቻቸውን የመደብደብና የማሰቃየት ሱስ ይዟቸዋል። በተለይ የኦጋዴን ሶማሌዎች በኢትዮጵያ እንደተጨቆኑና እንደተበደሉ ስለሚቆጥሩ በእስረኞቹ ላይ ክፉ ነበሩ። ቂማቸውን ለመወጣት እድሉን ሲጠሙት ይታያል። ራሳቸውን መከላከል የማይችሉትን እስረኞች ያለምክንያት ይደበድባሉ። ትጉ ሠራተኞች አይደሉም በሚል ሰበብ አዛውንትና ሽማግሌዎችን ይረግጣሉ። ዱላቸውንና ስድባቸውን ፈርተው በሚንቀጠቀጡ ሴቶች ላይ ይጮሃሉ። ጭንቅላታቸው በጥይት ተበሳስቶ አሸዋ ውስጥ ወድቀው የተገኙ

ሙታን እስረኞች ቁጥራቸው ብዙ ነው። በኢትዮጵያውያንና በሶማሌዎች መካከል ከእሬት የመረረ ጥላቻ እስከሰማይ ወጣ! ቢሆንም ግን ኢትዮጵያውያን ጥላቻቸውን በተግባር የሚገልጹበት መንገድ አልነበራቸውም።

ይህን በመሰለ አስጨናቂ ሁኔታ የደናኑ ወህኒ ቤት ግንባታ ቀስ በቀስ ተገነባ። እስረኞቹ እዚያ ባሳለፉት የዘጠኝ ወር ጊዜ ውስጥ እያንዳንዳቸው መቶ መቶ ሰዎች የሚይዙ አ ሥራ አምስት እስር ቤቶች ሠርተዋል። በዚህ ሁሉ ጨለማ መሃል ግን አንዳንድ ርህራሄና ደግነት የተሞላ መልካም ነገር አልፎ አልፎ ሲታይ የሰውን ልብ የሚደግፍና የሚያጽናናም ነበር። ከጨካኝ ወታደሮች መሃል በመብራት ተፈልገው የተገኙ ያህል ለእስረኛው የሚራሩና የሚያዝኑ ደጋግ ወታደሮች ነበሩ።በኢትዮጵያውያኑ መካከል ደግሞ እጅግ ልብ የሚነካ ህብረትና አንድነት መንጸባረቅ ጀመረ። ወላጆቻቸውን በጦርነቱ ያጡትን ትናንሽ ልጆች አዋቂዎቹ ሊንከባከቧቸው ወሰኑ። ወጣቶቹና ጉልበት ያላቸው ጎልማሶች ደግሞ በሥራ ቀንበር ስር ሚወድቁ የሚነሱትን አቅመ ደካማ አዛውንቶችችና አሮጊቶች ለመርዳት ከጎናቸው ቆሙ።

ጥበቡ የወህኒ ቤቱ ሐኪም በመሆኑ በግቢው ውስጥ በልዩ ዓይንና በልዩ ክብር እንዲታይ እግዚአብሔር ሞገሱን በላዩ አድርጓል። የወህኒ ቤቱ መኮንኖች በሻይ ሰዓት አብሯቸው እንዲሆን ይጋብዙታል።

የወህኒው ሽቀጥ አቀባይ አንድ ሐብታም ሶማሌያዊ ነጋዴ፤ ጥበቡ ከአለባበሱ አንስቶ ከእስረኞቹ ለየት ስላለበትና ከመኮንኖቹም ጋር በነጻነት በእንግሊዘኛ ሲነጋገር ስለሰማ፤ "ያ ወጣት ማንነው?" ሲል አንዱን መኮንን ጠየቀ። "ከቀብሪደሃሩ ሆስፒታል የተማረከ ሐኪም ነው። የእስረኞቹን ጤና እንዲከታተል አድርገነዋል።" ብሎ ይነግረዋል። ነጋዴው ጥበቡን መተዋወቅ ስለፈለገ መኮንኑ ሰውየውን ጥበቡ ወዳለበት ይዞት መጣ። በዕድሜው በሰል ያለ ሰው ነው። ቀጥሎ የተናገረውን ግን ጥበቡም ሆነ መኮንኑ አልጠበቁትም። "ከዛሬ ጀምሮ አንተ ልጄ ነህ! በየዕለቱ ሁለት ኪሎ ስኳር አንድ ሊትር ወተት አንድ ኪሎ ስጋ ሰላጣ ቲማቲም.... እልክልሃለሁ ሩዝ ፓስታ ዘይትና የመሳሰሉትን ሳሙና . . ደግሞ በየሳምንቱ እልክልሃለሁ..."

ነቢዩን ኤልያስን በቁራ የመገበው ጌታ እግዚአብሔር ይሄንንም ሐብታም ነጋዴ ለባሪያው ለጥበቡ ቀለብ ሰፋሪ አደረገው። ምግብ ብቻ ሳይሆን ሸሚዞች ሱሪዎችና የውስጥ ልብሶችም ለጥበቡ እያቀረበ እንደልጁ የሚገርም እንክብካቤና ቸርነት በእስር ቤት ዘመኑ ሁሉ አደረገለት።

ከዚህ ሐብታም ነጋዴ ሌላ አንዳንድ የአካባቢው ሶማሌዎችም ነበሩ። ፍጹም ቅንነትና ርህራሄ በተሞላው አገልግሎቱ ልባቸው የተነካ። በሕክምና ሙያው ስለረዳቸው ገንዘብ ሊከፍሉት ሲፈልጉ ጥበቡ አይቀበላቸውም። ስለዚህ ምስጋናቸውን ለመግለጽ ምግብና የመሳሰሉትን አስፈላጊ ነገሮች ያመጡለት ጀመር። ምንም እንኳን የሚያገኘውን መልካም ነገር ከወገኖቹ ተነጥሎ የግሉ እንደማያደርገው ቢያውቅም ለእርሱ ተለይቶ በሚደረግለት ቸርነትና ስጦታ እስኪሰማው ድረስ ሆነ። እናም እግዚአብሔር አምላኩ በጠላቶቹ ምድር የከፈተለት የቸርነት በር መሆኑን አስተውሎ ሰዎች የሚያመጡለትን ምግብ ታመው ለሚተኙትና ጉልበት ላጡት ወገኖቹ የሚያጠራቅምበት ግምጃ ቤት አዘጋጀ። የእስረኞቹ ቁጥር እየጨመረ በመጣ ጊዜም የመኝታ ክፍሉን ከእርሱና ከኢያሱ ጋር እንዲጋሩ ለሌሎች ወገኖቹም በሩን ከፍቷል።

****

## ኢየሱስን ከምክድ ሞቴን እመርጣለሁ!

ጥበቡ ከመጀመሪያ አንስቶ ስለክርስትና እምነቱ ለማንም ሰው ቢሆን ግልጽ ለማድረግ ቁርጥ ውሳኔ አደርጓል። ስለዚህ የመኝታ ቤቱን እንዲጋሩት የፈቀደላቸውንም ሰዎች ሆነ ሌሎች ወገኖችን በየማለዳውና በየማታው ለጸሎት መጋበዝ ጀመረ። ስለዚህም መኝታ ቤቱ በጥቂት ጊዜ ውስጥ የጸሎት ፕሮግራም ማካሄጃ የመጀመሪያዋ የ ጸሎት ቤት (ቻፕል) ሆነች። አጋጣሚውንም በመጠቀም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጥናትና ውይይትም ማካሄድ ጀመረ። በነዚያ የመጀመሪያ ዘጠኝ ወራት ውስጥም ሕይወታቸውን ለጌታ እየሰጡ የአማኖች ቁጥር ቀስ በቀስ ማደግ ጀመረ።

ጥበቡ ስለእምነቱ ግልጽ ለመሆን የወሰነው በሀገሩ ተወላጆች መሃል ብቻ አልነበረም። በማረኩትና ከምድሩ አፍልሰው ወደ ሶማሊያ በወሰዱት አክራሪ እስላም ወታደሮችም ፊት ጭምር እንጂ! ከመጀመሪያዎቹ ቀናት በአንዱ መኮንኖቹ አብሯቸው እንዲበላ ወደ ምግብ ቤታቸው ጠርተውት ሳለ፣ ከመብላቱ በፊት እንደልማዱ በፊቱ ስለቀረበው ማዕድ አምላኩን በጸሎት ሊያመሰግን አንገቱን ሲያቀረቅር የሁሉም ዓይኖች በጥበቡ ላይ ወደቁ። ጥበቡን ለጸሎት አንገቱን ሲያቀረቅር ከተመለከቱት መሃል አንደኛው መኮንን፤ ምነው ምን ሆነሃል ጤንነት አልተሰማህም እንዴ አለ ። ፍጹም ጤነኛ ነኝ እግዚአብሔር ይመስገን ብሎ መለሰ ጥበቡ። መኮንኑም "አይ! አንገትህን አቀርቅረህ አይንህን ስትጨፍን ዶክተሩ ራሱን ታመመ ወይ ብዬ አስቤ ነው" ሲል ሌላኛው መኮንን ከት ብሎ ሳቀ። ጥበቡም በበኩሉ ፈገግ አለና አንገቱን በአምላኩ ፊት ዝቅ አድርጎ መጸለዩ ይሄን ያህል አስቂኝ መሆኑ እየገረመው "ሁልጊዜ ምግብ ከመብላቴ በፊት እግዚአብሔር አምላክ ምግቡን እንዲባርክልኝ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጸለይ ልማዴ ነው" በማለት መልስ ሰጠ። ነገሩን የጀመረው መኮንንም ቀጠል አድርጎ "እ! ሃይማኖተኛ ነህ ማለት ነዋ? አንተ እስላም ነው መሆን ያለብህ። እንዳንተ ያለ ጥሩ ሰው-አላህን ሊያመልክ ይገባዋል" አለ። ጥበቡ ወዲያውኑ ምላሽ ሳይሰጥ በፊቱ የቀረበውን ሾርባና ዳቦ መመገቡን ቀጠለና የዚህ ውይይት አቅጣጫ ወዴት ሊሄድ እንደሚችል ማሰላሰል ጀመረ።

ቁጣና ጭካኔ የተሞላም ባይሆንም፣ "አላህ ታላቅ እንደሆነና መሃመድም የእርሱ ነቢይ እንደሆነ ማመን ይገባሃል፤" የሚል ጠንከርና ጎላ ያለ ድምጽ ከመኮንኑ አንደበት ወጣ። ጥበቡ ግን ያበጠው ይፈንዳ ብሎ "እኔ የማምነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው" አለ። የዚህን ዕለት ውይይት በምግብ ጠረጴዛው ዙሪያ የነበሩት መኮንኖች ሁሉ የተከታተሉት በታላቅ ንቃትና የጋለ ስሜት ነበር። ከነዚህም አንደኛው ወጣት መኮንን አጠርና ቀጠን ባለ ፊቱ ላይ በተሰኩ ትላልቅ ዓይኖቹ ጥበቡን ኮስተር ብሎ በማየት "እዚያ ጫካ ከነበሩት ወታደሮች አንዱ ቢያፋጥጥህ ኖሮ ይሄን ያልከውን አትደግመውም ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስን ከደህ በአላህና በመሃመድ እመን ብሎ ቢያስገድድህ በአላህ አታምንም ኖሯል?" ሲለው ጥበቡም ጥያቄውን የሰነዘረውን መኮንን ትኩር ብሎ በማየት አጠፌታውን "በጭራሽ አላደርገውም ነበር" የሚል ሆነ። መኮንኑ በሁለቱ መካከል የተጋጋለውን ምልልስ በሚከታተሉት መኮንኖች ፊት ጥበቡን ማፋጠጡ ቀጠለ። "ብትሞት ይሻልሃል ማለት ነው?" "አዎን! አዳኜንና መድኃኒቴን ክርስቶስ ኢየሱስን ከምክድ ሞቴን እመርጣለሁ!" ነበር የጥበቡ ቆራጥ መልስ። ታላቅ ጸጥታ በዚያ ምግብ ጠረጴዛ ዙሪያ ወደቀ። ከመኮንኖቹ መሃል አንዳንዶቹ በእስልምና እምነታቸው ጥብቅ ሃይማኖተኞች ናቸው። እነርሱም በበኩላቸው ስለሃይማኖታቸው ያላቸው አቋም ጠንካራ ነው። ስለዚህ ወጣቱ ዶክተር ስለእምነቱ ሕይወቱን እንኳን ሊሰዋ ዝግጁ መሆኑን በማየታቸው አከበሩት።

የጥበቡ ፍላጎት ሁሉንም ሰው በእኩል ዐይን በማየት የሚያስፈልጋቸውን የሕክምና እርዳታ

መስጠት ነው። ሱማሌዎችም ሆኑ ኢትዮጵያውያን ለጥበቡ ልዩነት የላቸውም። ለወህኒው አመራር ቡድን የሚገባውን አክብሮት ቢሰጣቸውም ሥልጣናቸውን ተደገፈው ከገደብ ያለፈ ትምክህተኝነት ሊያሳዩት ሲፈልጉ አይቀበላቸውም። ከቀን ወደቀን የጥበቡ አቋምና ማንነት እንደማይበገር በሶማሌዎቹ መኮንኖች ዘንድ የታወቀ ሆነና በሚያደርገው ሁሉ ከፍተኛ እምነት ይጥሉበት ጀመር።

****

*ጋዜጠኞቹ!*

ደናን በገባ ጥቂት ጊዜ ውስጥ የሶማሌ መንግሥት ሬድዮ ጣቢያ ለጥያቄና መልስ ፕሮግራም ጥበቡን ፈለገው። ቃለ ምልልሱን ባይፈልገውም የማይቀር ጉዳይ ሆነና ጥበቡ ሕመምተኞቹን ከሚመረምርበትና ሕክምና ከሚሰጥበት ክሊኒክ ድረስ ሁለት ጋዜጠኞች ሊያነጋግሩት መጡ። የመጀመሪያ ጥያቄአቸው ስለራሱ እንዲናገር ነበር። ጥበቡ አጠርና መጠን አድርጎ መልስ ሰጠ። ቀጥሎም ጋዜጠኞቹ ከጥበቡ መስማት ወደ ሚፈልጉት ትልቅና ዋና የፖለቲካ ጥያቄ መጡ።

ስለ ኢትዮጵያ መንግሥት... ስለ ደርግ አመራር ምን ታስባለህ? ጋዜጠኞቹ ከጥበቡ እንደበት እንዲወጣ የፈለጉት የጊዜውን የኢትዮጵያን መንግሥት የሚያጥላላ ፖለቲካውንና አመራሩን የሚቃወምና የሚያወግዝ አነጋገር ነበርና አፍ አፉን በጉጉት ሲጠባበቁ፤ "እኔ የሕክምና ባለሙያ እንጂ የፖለቲካ ሰው ስላይደለሁ ለዚህ መልስ የለኝም። ጤናን በሚመለከት ለምትጠይቁኝ ጥያቄ ግን በደስታ መልስ ልሰጣችሁ እችላለሁ" ሲል ዲፕሎማሲ የተሞላው መልስ ሰጣቸው። የጋዜጠኞቹ ዓላማ የኢትዮጵያን መንግሥት የሚያወግዝ የሚያጥላላም አነጋገር ከጥበቡ አንደበት ሲወጣ ባየር ለማሰራጨት ነበር። ሀገሩንም ሆነ መንግስቱን የሚነቅፍ አንዳችም ቃል ላለመተንፈስ ግን ጥበቡ በውስጡ ቆርጧል። አንድ የቀራቸው ጥያቄአቸው ምናልባት ፍላጎታቸው ያሟላ ይሆን ?

"በኢትዮጵያ ሕክምናን በሚመለከት በደርግ መንግሥትና በቀድሞ የኃይለሥላሴ መንግሥት መካከል ያለውን ልዩነት አወዳድረህ ልትነግረን ትችላለህ?" "ያሁኑ መንግሥት ጥረት የሚያደርገው በህክምና እርዳታ ተጠቃሚው፣ ኑሮ የተመቸው የከተማው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ በየዳራገሩ ያለው ገጠሬውም ጭምር እንዲሆን ነው። ይህን መሰሉን የጤና ፖሊሲ ደግሞ እኔ በሙሉ ልቤ እደግፈዋለሁ።" ጋዜጠኞቹ እዚሁ ላይ በቃቸው። እነሱ የፈለጉት በኢትዮጵያ ላይ ጥላቻን የመንዛት ፕሮፓጋዳቸውን የሚረዳ አነጋገር ነበር። እንደተመኙት ጥበቡን መጠምዘዝና የፖለቲካ መሣሪያቸው ማድረግ አልተሳካላቸውም። ጋዜጤኞቹ ብስጭት ደርሶባቸው ተመልሰዋል።

ደናን ወህኒ ቤት ውስጥ ባሳለፋቸው ዘጠኝ ወራት አብረውት በዚያ ወህኒ ስለተያዙት ምርኮኛ ወገኖቹ የጤንነት ይዞታ ከሚመለከታቸው የሶማሊያ ትላልቅ ባለሥልጣኖች ጋር ሕዝቡን በመወከል ተወያይቷል። ሞገስና ክብር የሆነለት ጌታም የእነዚህን ባልስልጣኖች ሰሚ ጆሮም ሰጥቶት ነበር። የሕዝቡን የጤና ችግር፣ ስለሚያስፈልገው የመድኃኒትና የምግብ ዓይነት የሚያቀርበውን ሃሳብ ተቀብለውት ወገኖቹ ከባሰ አስቃቂ ወረርሽኝና የበሽታ ኃይል ተርፈዋል። ክፋትና ጥላቻ የተሞላበት አድራጎታቸውን በምርኮኛው ሕብረተሰብ ላይ ያለርህራሄ ይፈጽሙ የነበሩት በአብዛኛው ተራ ወታደሮቹ ነበሩ።

በዘጠኝ ወር የደናን ወህኒ ቤት ቆይታው መጨረሻ ገደማ በአንድ የማይረሳ ቀን አብዲ አብዱሌ ወደ ወህኒው ክሊኒክ መጣ። ከኢትዮጵያዊው የሥራ ባልደረባው ከጥበቡ ፊት ለፊት ተቀምጦ ዓይን ዓይኑን ያየዋል። የአብዱ አብዱሌ አመጣጥ እንደልማዳቸው ስለእስረኞቹ ጤንነትና አስፈላጊ ስለሆኑ መድኃኒቶች ሊያነጋግረው ስለመሰለው በጥንቃቄ ያዘጋጀውን ስታቲስቲክስና ሊስት ጥበቡ



ረቂቅ ጥበቡ በሁለት ወሯ

አንገቱን አቀርቅሮ ያገላብጣል። አብዱ አብዱሌ ግን የመጣበት ዋና ጉዳይ እሱ አልነበረምና ጥበቡ ስለሚያገላብጠው መዝገብ ደንታም አልሰጠውም። "ዛሬ የመጣሁት ዜና ይዤልህ ነው" የሚል ድምጽ ከአብዱ አብዱሌ መውጣቱን የሰማው ጥበቡ፣ አንገቱን ቀና አድርጎ ቢመለከተው አብዱ አብዱሌ በደስታና በፈገግታ ተሞልቷል። "ምን ሊሆን ይችላል?" አለ ጥበቡ በልቡ። "ሚስትህ ለዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ያቀረበቺው ጥያቄ ወደዚህ ደርሷል!" አለው አብዱ። የጥበቡን ደህንነት ለማወቅ እኔ ስለማደርገው ፍለጋና ጥረት ሚሥጥራዊ ዜና ነገረው! ኢትዮጵያ ለሚገኘው ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ያቀረብኩት ጥያቄ ወደ ዋናው ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ጀኔቫ ተላልፎ ጥያቄው ለሶማሌ መንግሥት እንደቀረበ አጫወተው።

ጥበቡም "ባለቤቴ አሁን ያለሁበትን ታውቃለች ማለት ነው?" ሲል አብዱን ጠየቀው። "በእርግጥ የባለቤትህ ጥያቄ፡- ቀብሪደሃር ሆስፒታል ይሰራ የነበረው ዶ/ር ጥበቡ ኃይለሥላሴ በሶማሌ መንግሥት እጅ መኖር አለመኖሩ ይጠየቅልኝ የሚል ቢሆንም የሶማሌ መንግሥት ግን ለጥያቄዋ መልስ መስጠቱን ላረጋግጥልህ አልችልም። ሆኖም ግን አግባብ ባለው ዓለም አቀፍ ድርጅት በኩል እየፈለገችህ መሆኑን መረዳቴ ደስ ስላለኝ ነው ልነግርህ የመጣሁት" አለው። በእርግጥ ሶማሊያ ጦር መዘው ያልተዋጉትን ጥበቡንና አብረውት የተጋዙትን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሲቪል ኢትዮጵያውያን እንደ ምርኮኛ ቆጥራ ስትፎክርና በአየር ማሰራጫዎቿም ኢንተርቪው ስታቀርባቸው ሰንብታለች። የጦር ሠራዊት ያልሆነውን ያን ሁሉ ሲቪል ሕዝብ በምርኮኝነት አፍና ማስቀመጧ ጀግንነት እንጂ ህገ ወጥነት መሆኑ ገና ሊዋጥላት አልቻለም። ስለሆነም በዚህ ህገ ወጥ ሥራዋ የውጪው ዓለም እንዳያወግዛት ያላት መውጫ መንገድ እነዚህን ሲቪሎች በተቻለ ፍጥነት ወደ ሀገራቸው በጨዋ ደንብ መመለስ ነበር። ይህን ጨዋነት ታደርገው አታደርገው እንደሁ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ግልጽ ይሆናል።

ብቻ ያም ሆነ ይህ ያን ዕለት ጥበቡ ከአብዱ አብዱሌ በሰማው ዜና በጣም ተጽናና። ስለቤተሰቦቹ ከዚህ ጓደኛው ከሰማው በላይ ዝርዝርና ሰፋ ያለ ዜና ቢያገኝ በወደደ ነበር። ሆኖም ግን እርሱ አምላኩን የሚያመሰግንበት ጉዳይ በዚህ ዕለት አግኝቷል።

"ጌታ ሆይ! የሊሻንን ደህንነት ስለእኔም ለማወቅ የምታደርገውን ጥረት እንድሰማ ስላደረግኸኝ በጣም አመሰግንሃለሁ። አምላኬ ሆይ የሚስቴና የልጆቼ አባት እረኛና ታማኝ ጠባቂ ስለሆንክልኝ አመሰግናለሁ። አሁንም ለታመኑ እጆችህ አደራ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ" በማለት ያን ዕለት ምሽቱን በአምላኩ ፊት ረዘም ባለ የምስጋናና የጸሎት ጊዜ አሳለፈ። በእንቅልፍ ተሸንፎ ሲወሰድ ከጥበቡ አንደበት ይወጣ የነበረው የመጨረሻ ቃል "ጌታ ሆይ! ሊሻን በሕይወት መኖሬን እንድታውቅ ከረዳሃት ኀዘኗ እንደሚከፈልላት አምናለሁ። ልጅህን እርዳት ጌታ ሆይ! . . ." የሚል ነበር።

ምናልባትም ዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ድርጅት በዚህ ጉዳይ ጣልቃ መግባትና ሶማሊያንም ማሳመን ከቻለ፣ የጥበቡና የወገኖቹ ወደ ኢትዮጵያ የመመለስ እድል በቅርቡ ሊሆን ይችል እንደሁስ ማን ያውቃል? ምናልባት! ምናልባት... የመከራንና የችግርን ዘመን በትዕግሥት ለመወጣት ለሰው ልጅ "ተስፋ" ትልቅ ጉልበት ነው። በተለይ ተስፋው ሕያው ለሆነ ለእግዚአብሔር ሰው!

*"እርሱ የሚተወውን ሸለቆ እኔ እሞላዋለሁ"*

ይህ ቃል በአካል ከጥበቡ በብዙ ሺህ ኪሎሜትር ርቀት ሳልወድ ለተነጠልኩት የቀረልኝና አለኝ የምለው፥ የከበበኝን ጨለማና አጠራጣሪ ሁኔታ የማሸንፍበት፥ ከአምላኬ የተቀበልኩት የተስፋ ቃል ነበር። የጥበቡን መማረክ ከባድ መርዶ በሰማሁ በዚያን ዕለት፥ በኀዘን ተመትቼ ሳለ ነፍሴ ከአርያም የመጣላት የተስፋ ቃል ነበር። አዎ! እንደተናገረው እንዲሁ የሚፈጽመው ጌታ እግዚአብሔር ጥበቡን ወደዚያ የወሰደበት ዓላማ ሲጠናቀቅ፥ ወደእኔና ወደልጆቹ እንደሚመልሰው ተስፋ ሰጥቶኛል። በዚህም ምክንያት የኔ ነገ በተስፋ የተሞላ ስለሆነ፥ ነገን በጉጉት መጠባበቅ ጀመርኩ፤ ማን ያውቃል? ውዴ ጥበቡ ወደ ምንወደውና ወደሚወደን ቤተሰቡ፣ ወገኖቹ፣ ዘመድ አዝማዶቹና አገሩ የሚመለሰው ምናልባት ነገ ቢሆንስ?! እነዚህን ሁለት ውብ ሴት ልጆቹን አቅፎ የሚያጫውታቸው ምናልባት ከነገ በስቲያስ ቢሆን ማን ያውቃል?! . . .

ትልቋ ልጃችን እምነት የአንድ ዓመት የልደት በዓሏን ስናከብርላት ጥበቡ ቀብሪደሃር ስለነበር አልተገኘም። ሁለተኛ ልጃችን የተወለደችው ጭራሹኑ እሱ ተማርኮ ሶማሊያ በተወሰደበት ቀን ስለነበር ያው እሷንም እስካሁን አቅፎ ለመሳም አልበቃም። እንዲያው ለመሆኑ ይቺን ባለታሪክ ልጅ መጠሪያ ስሟን ማን ልበለው? "ረቂቅ ጥበቡ" ነው የምላት በቃ! ከተወለደችባት ከዚያች ታሪካዊ ቀን አንስቶ የአምላካችንን ጥበበኛነት ለመግለጥ የተፈጠረች። ለእኔም ሆነ ለሌሎች የቤተሰባችንን ታሪክ ለሚሰሙ፣ ጌታ እግዚአብሔር ለዕውቀቱና ለማስተዋሉ ዳርቻ የሌለው መሆኑን የምትገልጥ ብላቴና ናት።

ረቂቅን ጡት ሳጠባ እምነትን ምግብ ሳበላ፣ ጥበቡ ፊቴ ድቅን ድቅን ስለሚል ከእንባዬ ጋርም የምታገለው በዚያው ፍጥነት ነው። ደግነቱ በዚህ የሕፃንነት ዕድሜያቸው ከጨዋታና ከቡረቃ፣ ሲርብ ሲጠማቸው በልቅሶ ስሜታቸውን ከሚገልጹት ሌላ እኔን የሚያብሰለስለኝ ጥያቄ የነሱ ጥያቄ አልነበረም። እኔ ባማረ ቤት ስኖር፣ ቤተሰብ ተጨንቆ ጣዕም ያለው ምግብ ሲያቀርብልኝ፣ ምቹ ፍራሽና አልጋ ላይ ስተኛ ... "ውዴስ እንዴት ይሆን?" ማለት የዕለት ጭንቀቴና ሃሳቤ ሆነ። ላቆመው ያልቻልኩት አንድ ችግር፣ በሃሳብ ጅው ብሎ ጭልጥ ብሎ ሶማሊያ መግባትን ነበር። ድንበርና ኬላ በማያግደው መንፈሴ እሄዳለሁ እንጉዳለሁ... በተለይም አንድ ቀን በጸሎት ተንበርክኬ ሳለ፦

"ውዴ የኔ ፍቅር ጥበቡ! እንዴት ውለህ አድረህ ይሆን? ርህራሄ በሌላቸው ጠላቶች እጅ የወደቅኸው ውዴ፣ ሁልጊዜ በቅንነትና በእውነት የምታመልከው አምላክህ እግዚአብሔር ሊያስጥልህ ሊጋርድህ ችሎ ይሆንን? ."

ቃሌ ከአንደበቴ ካመለጠ በኋላ መልሼ ደነገጥኩ፤ ምን አይነት ቅዠትና ጥያቄ ውስጥ ገባች ደግሞ ነፍሴ? የአሕዛቡ ንጉሥ ዳርዮስ የጠየቀውን አይነት ጥያቄ ሆነብኝና ራሴ ስደግመው ያገኘሁት አዘንኩ። ያ ጥያቄ፣ ነቢዩ ዳንኤል በተራቡት አናብስት ጉድጓድ በተጣለ ጊዜ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔርን ማንነት ያላወቀው የንጉሥ ዳርዮስ ጥያቄ ነበር። ነፍሴን ገሰጽኳት! የአምላኬ ችሎታማ በአንቺ አይጠየቅም አልኳት! አስደንጋጩን ዜና በሰማሁ ዕለት እግዚአብሔር ያለኝን አሰብኩ።

"ልጄ ሆይ! የማደርገውን የማውቅ አምላክሽ እኔ እግዚአብሔር ነኝና አይዞሽ! ባሪያዬን ለሥራዬና ለከበረ ዓላማዬ ወስጄዋለሁ። በዚያ ያለኝን ዓላማዬን ስጨርስ አመጣዋለሁ። እርሱ የሚተወውን ሸለቆ እኔ እሞላዋለሁ።"

"ስለዚህ" አልኳት ነፍሴን፣ "ስለዚህ፣ በጥንት ዘመን ታላላቅ ተአምራት በማድረግ ከነቢዩ ከዳንኤል ጋራ የተገለጠው የእግዚአብሔር ክንድ ዛሬም ከባሪያው ከጥበቡ ጋራ ነው! እኔና ጥበቡ የምናመልከው እኮ ይሄን ያልተለወጠውን የዳንኤልን አምላክ ነው። የአምላኬ የዘላለም ክንዶች ደግሞ ሊጋርዱት ሊንከባከቡት ከውዴ ከጥበቡ ጋራ ናቸው።"

በቃ! የዚያን ዕለት አንድ ትልቅ መንፈሳዊ ለውጥ በውስጤ ተካሂዷል። ወደ ጥልቅ ኀዘንና ጥያቄ ነፍሴን የሚከትብት የጠላቴ አንድ መሣሪያው እንደ ተደመሰሰበት፣ በእግዚአብሔር እሳት እንደተበላ ተሰማኝ።

ስለዚህ በአምላኬ ተጽናንቼ ሌሎችንም የማጽናናበት ጉልበት ከእርሱ ተቀብዬ በተሰፋ የተሞላውን የእምነት ጉዞዬን ተያያዝኩት። ደካማው ማንነቴ በዚህ የተሰፋ ኃይል ጉልበት አገኘ። ድንገትም የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ ያመጣ እምነት ተላብሼ ራሴን አገኘሁት። እኔን ሊያጽናኑ የመጡ ወገኖች ከውስጤ በሚወጣው ቃልና ጸጋ በተገላቢጦሽ እነርሱ ተጽናንተው ይመለሱ ጀመር። የሚያበረታው የእግዚአብሔር እጅ በእጅጉ ሲረዳኝ አየሁ። በተጨማሪም የሚወዱኝ ወላጆቼ፥ የቅርብ ጓደኞቻችንና፥ ባጠቃላይ የእግዚአብሔር ሕዝብ በዙሪያዬ ታላቅ የፍቅርና የጸሎት ተጋድሎ ሲያደርጉ አየሁ። እግዚአብሔርም የጥበቡንና የእኔን ጉዳይ የሕዝቡ ጉዳይ እንዳደረገው ተረዳሁ።

****

የዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ድርጅት ምርኮኞችን ጉዳይ በሚመለከት ክትትል የሚያደርግ አግባብ ያለው መ/ቤት በመሆኑ ባስቸኳይ የጥበቡንና የኢያሱን ስም አስመዘገብኩ። የሥራ ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ ሳለ በሶማሊያዎች ተማርኮ መወሰዱን እኔም በበኩሌ ማረጋገጤን የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንዲያውቀው አደረግሁ። በሥራ ገበታው የነበረበትን የሐምሌ 1969 ዓ.ምን ደሞዝ ብቻ ሰጥቶኝ እኔና ሁለት ሕፃናት ልጆቻችን መንግሥት እስኪወስንልን እንድጠብቅ ተነገሮኛል። ይህም ማለት ደግሞ ያስተዳድረን የነበረው የጥበቡ የወር ደሞዝ ያለንዳች ማስጠንቀቂያ ቀጥ ብሎ ቆመ ማለት ሆነ።

አስታውሳለሁ ወላጅ አባቴ ሊያጽናናኝ እናም ደግሞ ከእንግዲህ በእጄ ያለውን ጥሪት በጥንቃቄ እንድጠቀም አጠገቡ አስቀምጦ ሊመከክረኝ የሞከረበትን ቀን። ጥበቡ ቀብሪደሃር ተመድቦ በሚሠራበት ጊዜ ሁሉ ሌላ ሥፍራ ከተመደቡት ሐኪም ጓደኞቹ በላይ እጥፍ የወር ደሞዝ ያገኝ እንደነበር አባቴ ያውቃል። ጥበበኛው ጥበቡ መቼም ጥቂት ሺዎች ብር በባንክ ሳያከማች አይቀርም በሚል እርግጠኝነት ይመስላል እጠየቀ።

"እንግዲህ አንቺ እግዜር ረድቶሽ ሥራ እስክምታገኚ ያላችሁን በአግባብና በቁጠባ መያዝ ነው። አይዞሽ ልጄ! እንዲያው ለመሆኑ ምን ያህል አላችሁ በባንክ?" መልሴ አባቴ ሊሰማ የሚጠባበቀው ዓይነት እንዳልሆነ ባውቅም ትክክለኛውን ሁኔታ መረዳት ይገባው ነበርና፡- "ምንም ተቀማጭ ገንዘብ የለንም አባዬ" አልኩት። የአባቴ መልክ በዐይኔ ፊት ሲለዋወጥ ሲደናገጥም አየሁ! ከፊቱ የማነበው፡- "በኀዘን የቆሰለውን የልጄን ልብ የሚነካካ አጉል ጥያቄ ለምን ጠየቅኋት?" እንደሚል ገባኝ።

ወላጆቼ እንኳን ለእኔ ለልጃቸው ለሌሎችም የሚተርፉ ቸር ሰዎች ነበሩ። ዛሬ ግን በኮምዩኒስቱ ደርግ ሃብት ንብረታቸውን ተወርሰው በብዙ መዘርጋት የለመደው እጃቸው የታሠረበት ወቅት ነው። አባቴ ልቡ በኀዘን ሲዋጥ ስላየሁት ፈጠን ብዬ እንዲህ አልኩት። "አይዞህ አባዬ! የኛ ገንዘብ የት እንደሄደ... ምን እንዳደረግንበትም እግዚአብሔር አምላክ ያውቃል"።

ከዚህ ዕለት ጀምሮ በልቤ አንድ የተቀረጠ ነገር ሆነ። ከእንግዲህ የኔና የልጆቼ የዕለት ተዕለት ኑሮ፣ ሁሉን በሚችለው በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር እጅ እንጂ በእኔ እንደማይመራ። ጥበቡ ባጠገቤ ኖረ አልኖረ ሙሉ ኃላፊነቱን የወሰደ የኔና የልጆቻችን የሕይወታችን ባለቤት ከእኛ ጋራ ለመሆኑ እርግጠኛ ሆንኩ። በራሴ በኩል ጥንቃቄ ላደርግ የሚገባኝ ከአምላኬ ጋር ስለሚኖረኝ የማያቋርጥ ግንኙነት፣ ስለእግዚአብሔር መንግሥትና ስለጽድቁ ሊሆን እንደሚገባ አውቄያለሁ። ሰዎች

በዚህ ጉዳይ ሲጨነቁልኝ ማየት ወይንም አንዳንዶች ከዚያም እንኳን አልፈው ኑሮዬን በሚመለከት አንዳንድ ሃሳብ ሲያቀርቡ ይከብደኝ ነበር። አምላኬ የተናገረኝ አለ። "....እርሱ የሚተወውን ሸለቆ እኔ እሞላዋለሁ።...."

እግዚአብሔር አምላካችን ጥበቡ የተወውን ክፍት ቦታ መሸፈን ብቻ ሳይሆን፣ በስጋ በነፍስ በመንፈስ ለሚያስፈልገን ለማናቸውም ጉዳይ የቤተሰቡ ሙሉ አስተዳዳሪ ነው። ይህ እውነት ለእኔ ገብቶኛልና ሰዎች ባይቸገሩብኝ እንዲያው ዝም ብለው ብቻ ከአምላኬ ጋር ቢተዉኝ መረጥሁ። "ይሹሩን ሆይ በሰማያት ላይ ለረድኤትህ በደመናትም ላይ በታላቅነት እንደሚሄድ እንደአምላክህ እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም።"

ጥር 1 ቀን 1970 ዓ.ም። የጥበቡን መማረክ በሰማሁ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ዜና ማዘጋጃ ክፍል ክፍት የሥራ ቦታ መኖሩ እቤት ድረስ ስልክ ተደውሎ ተነገረኝ። ቀድሞ እሰራ የነበረው የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ዜና አዘጋጅነት ነው። እስከማውቀው በጋዜጠኝነት ሙያዬ ተስማምቶኝ ስድስት ዓመት የሰራሁበት ስለነበረ ሥራውን የተቀበልኩት በደስታ ነበር። ከተሻሻለ ደሞዝ ጋር። ግር ያለኝ ግን እንደነባር ሠራተኛቸው ሳይሆን በሠራተኛ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት፣ እንደ አዲስ ሠራተኛ ከስድስት ወር የሙከራ ጊዜ ጋር መቀጠሬ ነበር።

የሥራ ሰዓትን በሚመለከት አሁን የልጆች እናት ከሆንኩ በኋላም ተመችቶኛል። ዜናውን የምናዘጋጀው በየተመደብንበት የተረኝነት ሰዓት ስለሆነ ከልጆቼ ጋራ ለመሆን የተመቻቸ ነበረ። ልጆቼን፣ ከሞግዚት ሌላ ወላጆቼ ስለሚናፍቋቸው ከናዝሬት እየተመላለሱ ያዩዋቸዋል። ሰፊ ቤተሰብ መሀል ስለተወለዱ ታናናሽ እህቶቼና ወንድሞቼ ሁሉ እምነትንና ረቂቅን በፍቅር ሲቀባበሏቸው ማየት ያጽናናኝ ነበር። የዕድሜ ልዩነታቸውም አንድ ዓመት ከሀያ አራት ቀኝ ብቻ ነው። ረቂቅ ሁለትና ሦስት ዓመት ካለፋት በኋላ እምኑንና እሷን ይዤ ስሄድ ለሚያየን ሁሉ መንታ ይመስሉ ነበር። ሱሪዎች፣ ቀሚሶች፣ ካፖርቶች ከቀለም አመራረጥና አገባብ ጋር፣ ሬዲ ሜድ አስመስዬ እሰፋላቸዋለሁ። ውብ የሆኑ ቆንጆ ቆንጆ ሹራብ ሥራዎች እኔም እናቴም በያይነቱ እናለብሳቸዋለን። ከወጪ አገር በውድ የተገዙ ልብሶች የለበሱ፣ ሁሉ የሞላላቸው ልጆች ይመስሉ ነበር! "መንትያ ናቸው? ውይ ሲያምሩ! እንዴት ቆንጆ ልጆች ናቸው?" መባልን፣ እኔም በደስታ ለጥያቄያቸው ምላሽ መስጠትን ለምጃለሁ። በዚህ መልኩ አዲሱን አይነት የሕይወት ምዕራፍ ካለውዴ ጥበቡ ተያይዤዋለሁ። በሥራዬ ቦታ የተከሂደውን ስር ነቀል ለውጥ ግን መልመድ አቅቶኛል። እንደማልከርምበት አወቅሁት!

****

*የውሳኔ ሰፍራዎች!*

ብዙ አውጥቼ አወረድኩ። በእርግጥ ሥራው ያለአባት ለማሳድጋቸው ልጆቼ ዳቦና ወተት መግዣ የተዘጋጀልኝ መንገድ ነው ብዬ የተቀበልኩት ሥራ ነበር። ነገር ግን አብዮት የተጧጧፈበት ጊዜ ስለነበር ሁለት ዓመት ተለይቼው የተመለስኩበት የዜና ማደራጃ ክፍል ተለውጧል። በዜናዎቹ ይዘት ላይ አብዮት አካሄደባቸው ነው ያገኘሁት። ሚድያው ለኮምዩኒዝም አይዲኦሎጂ በስፋት ማሰራጭያና ማስፋፊያ ሆኗል። ለደርግ መንግሥት እያንዳንዱ ዜና አብዮታዊ መሆን ነበረበት።

የኮምዩኒዝም አይዲሎጂ ቤተክርስቲያኔን የዘጋ የእምነቴ ጠር ነው። የእምነት ነጻነቴን የገፈፈ ነው። ለደርግ ከሁሉም በላይ አብዮቱ ነው። ለእኔ ደግሞ ከሁሉም በላይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ደርግ ተፈጥሮን እንቆጣጠራለን ባይ ነው። እምነቴ ደግሞ የተፈጥሮ ገዢና አዛዥ፣ እርሱ ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ነው ይላል። አይዲኦሎጂው የሕያዋን ፍጥረታት ጅማሬ አንድ ሴል

ወይንም ሕዋስ ነው፤ ሰውም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ከዝንጀሮ ነው ይላል። እምነቴ የሰው ልጅ በፈጣሪው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ክቡር ፍጡር እንጂ፣ የዝንጀሮ ዝርያ የለውም ይላል። አይዲኦሎጂው ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብት ምድርም የመጡት፣ ከዘመናት በፊት በተከሄደ በአንድ የኃይል ግጭት፣ ቢግ ባንግ (big bang) ነው ይላል። እምነቴ ግን ሁሉ ከእርሱና በእርሱ እንዲሆን ባደረገ፣ ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብትን ባስቀመጠላቸው ሥርዓት እንዲኖሩ ባደረገ በእግዚአብሔር ነው ይላል። አይዲኦሎጂው የሃሳባውያን ሃሳብ ነው እንጂ እግዚአብሔር የሚባል ስለሌለ በተጨባጭ ማሳየት አይቻልም ይላል። እምነቴ የዚህን የፈጣሪ ኩሉ ዓለምን ሕያውነትና በግል ሕይወቴም የእርሱን ሕልውና ያረጋገጡልኝ ብዙ ሁኔታዎችን አስጨብጦኛል። ቋንቋውም ሆነ ፍልስፍናው የማላምንበትና የማይስማማኝም ነው!

ወሰንኩ። ለዳቦ ብዬ እምነቴን በሚጻረር የሥራ መስክ ላይ ላለመሰማራት። ውሳኔዬን ለቤተሰብ ስነግር፤ በመጀመሪያ የወንድሜ የገብሩ ቃል፡- (በዚህ ጊዜ ገና ለእግዚአብሔር ልቡን አልሰጠም ነበር ወንድሜ)

"አትችዪም! አላወቅሺም እንዴ??"

"ለምን? ምንድነው ያላወቅሁት?"

"ለማንም የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ መልቀቂያ ወረቀት እንዳይሰጥ ደንብ ከወጣ ሁለት ዓመት ሆኖታል።"

ነገሩን ሳሰላው ከጥበቡ ጋር ተጋብተን ቀብሪደሃር ለመሄድ የሥራ መልቀቂያ መንግሥት ከሰጣቸው ከመጨረሻዎቹ መኻል አንዷ ነበርኩ ለካ! ያኔ ያስመለጠኝ አምላኬ አሁንም ሌላ መውጫ መንገዱን ብልጭ አደረገልኝ! ወንድሜን እንዲህ አልኩት።

"ገብሩ! እችላለሁ! እኔ እኮ የሠራተኛ መተዳደሪያ ደንብ የሚፈቅድልኝ ጊዜያዊ ሠራተኛ ነኝ! ስለዚህ የመልቀቅ መብቴ የተጠበቀ ነው።"

"ሊሻን! ሕጉ ሊፈቅድልሽ ይችላል፤ ሌላ ሥራ ሳታገኚ ጥለሽ ብትወጪ ግን ትልቅ ስህተት ይሆናል። እነዚህን ሕፃናት ይዘሽ፤ ኋላ ነግሬሻለሁ!"

እኔ በበኩሌ ሥራ ተገኘ አልተገኘ ለምወስደው እርምጃ ውስጤ ቆርጧል። ስድስት ወር ሊሞላኝ ዘጠኝ ቀን ብቻ ቀርቶኛል። አንድ ቀን የጠዋት ተረኛ ሆኜ ዜና ላዘጋጅ ቢሮ ገብቻለሁ። ለጠዋት የሚቀርበውን ዜና አዘጋጆቹ ተጨማሪ ካለ በመጠባበቅ ላይ ሳለሁ አንድ ጊዜው ያለፈበት የሥራ ማስታወቂያ ላይ ዐይኔ አረፈ። መከላከያ ሚኒስቴር የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት ክፍል የሬድዮ ፕሮግራም አዘጋጅ ይፈልጋል። በጋዜጠኝነት የቢኤ ዲግሪ ወይንም የሰባት ዓመት የሥራ ልምምድ ያለው ይላል። ጊዜው ማለፉን እያየሁ ሠራተኛ አስተዳደር ቢሮ ሄጄ እንድጠይቅ አጥብቆ ተሰማኝ። እዚያ ቢሮ ሄጄ የተነገረኝ ገረመኝ።

"የጠየቁትን ኳሊፊኬሽን የሚያሟላ የለም፤ ስለዚህ አልቀጠሩም። ብትሄጂ ሥራው ይጠብቅሻል እርግጠኛ ነኝ፤ እንዲያውም ለምን ስልክ ደውዬ አልጠይቅልሽም ከምትለፊ" ሰውዬው እንደገመተው ነው። ሠራተኛ አላገኙም። ባስቸኳይ ሊቀጥሩኝ እንደሚፈልጉ የመከላከያ ሰዎች ገለጹልኝ።

"አልችልም ይቅርታ! ማስታወቂያ ሚኒስቴር የጥቂት ቀናት ግዴታ አለብኝ ስጨርስ ነው የምመጣው። አ! ደግሞ የኮንትራት ሠራተኛ እንጂ በቋሚነት መፈራረም አልፈልግም"።

መከላከያ በፍላጎቴ መሠረት በኮንትራት ሠራተኛነት፣ በበለጠም ደሞዝ ሊቀጥረኝ ተፈራርሜ ጨረስኩ። ለማስታወቂያ ሚኒስቴር የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ ሳስገባ ነባሯን ሠራተኛቸውን እንደ አዲስ የመቀጠሬ ምክንያት ሊገባቸው አልቻለም።

የገባው በማይወጣበት ዘመን የማምለጫ ዐለቴ የሆነው አምላኬ፣ በከፈተልኝ በር ወጥቼ ሕዝብ ግንኙነቱ ክፍል የሬድዮ አዘጋጅ ለመሆን፣ መከላከያ ሚኒስቴር ገባሁ። የእምነት እንጂ የፖለቲካ ሰው ባለመሆኔ መከላከያ ሚኒስቴርም ቢሆን ለመንፈሴ አልተመቸውም። ጭራሹኑ ባይብስ! ነፍሴ ተጨነቀች! "አብዮት ወይም ሞት" በሚባልበት ዘመን። የእምነቴን ምንነት ወደምፈትንበት የትግል ሜዳ መግባቴን ብዙም ሳልቆይ አወቅሁት! አንገቴን አቀርቅሬ ያ ክፉ ቀን እስኪያልፍ አባት የሌላቸውን እነዚህን ሕጻናት ባሳድግ አይሻልም እንዴ? የኔ ሳይሆን የብዙ ሥጋ ዘመዶቼ ጥያቄ ነበር።

"ዳቦና ወተት የሚያስፈልጋቸው ሁለት ሕጻናት ይዞ፣ ሰው እንደፈለገው መሆን እንዴት ይችላል? ያውም ጦር ኃይሎች ቤት! ሁሉን በጠመንጃ ኃይል በሚያስሩበት በዚህ ቀውጢ የአብዮት ዘመን፣ አንቺ ከእነማን ትበልጫለሽ? ይልቁንስ እነዚህን ምስኪን ልጆች ደግሞ እናት አልባ እንዳታደርጊያቸው ተጠንቀቂ!"

የማስታወቂያም ሆነ የመከላከያ ሚኒስቴር ሥራዎቼ ለእኔ የመነጠሪያና የመመዘኛ ሰፍራዎች ነበሩ። ከክርስቶስ ጌታዬ ሌላ አዛዥና ጌታ ላይኖረኝ ከነፍሴ ጋራ የተማማልኩባቸው፤ የውሳኔ ሰፍራዎች!

ውሳኔዬ፡ "የቀረው ይቀራል እንጂ የኮምዩኒዝም አገልጋይ አልሆንም" ሆነ። ስድስት ወር ሳይሞላኝ ሥራውን ልለቅ መወሰኔን ለቅርብ አለቆቼ ገለጽኩ። ሌላ ሠራተኛ እስኪፈልጉ ቢያንስ ለሦስት ወር እንድቀጥልላቸው ጠየቁኝ። ሰስቱን ወር በጭንቅ ቀጠልኩ። የኮንትራት ጊዜዬ የሚያልቅበትንና ከዚያም ሰፈር የምሰናበትበትን ጊዜ በናፍቆት ጠበቅሁት። ዘጠኝ ወር ባጠቃላይ። እንደባለፈው ጊዜ አሁንም አምላኬ የመሸጋገሪያ ድልድይ ከሰጠኝ ብዬ ጋዜጦችን አገላብጫለሁ። ጊዜያዊ ሥራ እንኳ ፈልጌ አላገኘሁም።

ወላጆቼና ወንድሜ ጉዳዩ በጥብቅ አሳሰባቸው። በተለይም አባቴና ወንድሜ ሊመክሩኝ ይዘውኝ ቁጭ አሉ። እኔ ግን በልቤ የቆረጥኩበት ጉዳይ ነው። የኮንትራት ጊዜዬ ከማለቁ በፊት ቀደም አድርጌ መልቀቂያ ደብዳቤ ሰኞ ለማቅረብ ወሰንሁ። ሁኔታውን ይከታተሉ የነበሩ የቅርብ ጓደኞቼም አሳሰቧቸዋል። በደብዳቤው ላይ እጃቸውን ጭነው ሊጸልዩልኝ ስለፈለጉ ዐርብ ዕለት የጾም ጸሎት ፕሮግራም አቅደው ጓደኞቼ እኔ ቤት ለአዳር ተገናኙ።

እነዚሀ ዛሬም ከ43-46 ዓመት ዕድሜ ባለው እህትማማችነት በቤቱ ያቆየን ጓደኞቼ ናቸው። በቁጥር 13 ስንሆን ሁላችንም የተገናኘነው እግዚአብሔር ልባችንን ከለወጠልን ወዲያ ገና ወጣቶች ሳለን ነው። ማንኛችንም ገና ትዳር ሳንይዝ ጀምሮ ማለት ነው። ባሎቻችንንም እግዚአብሔር ሲሰጠን አብረን ጸልየናል። አንዳችን ለሌላችን ሚዜ ሆነናል። በዓመታቱ መካከል የሆነውን ስናየው በደስታው ቢሆን በኀዘኑ ሳናውቀው የማንተጣጣ ሆነን ራሳችንን አገኘነው። እርስ በእርስ ባለው ጉዳያችን ብቻ ሳይሆን፣ ለአገርም ሆነ ለቤተክርስቲያን ጉዳይ በጾም በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት የመውደቅ ልባችን ብዙ አቀራረበን።

ስለዚህ እግዚአብሔር በዚህ ፍቅራችን ላይ የተመሠረተ ጠንካራ ሕብረት እንዲኖረን የፈለገ መሆኑ ገብቶን ተወያየንበት። እስካሁን ሳይገባን የተጓዝነውን ጉዞ ከእንግዲህ አውቀንና አስተውለን ለመጓዝ ተነጋገርን። አምላካችን በዚህ ሕብረታችን ውስጥ አልፎ ሊሠራ ስለሚፈልገው መለኮታዊ ዐላማው እንድንተጋም ተስማማን። የመገናኛችን ዋና መሠረት መንፈሳዊ እንዲሆን ከዚያ ውጭ ተርፎ የሚፈሰው ግን እግረመንገድ የሚሆን ጉዳይ እንዲሆን አደረግነው። እህት ጓደኝነታችንን በቅደም ተከተሉ አስቀመጥነው። ባጭሩ የታቹን ወደላይ የኋላውን ወደፊት አዙረን እንድናስተካከለው እግዚአብሔር ረዳን።

በልቅሶና በኀዘን ሰሞን ብቻ እንደ እድርተኞች መገናኘታችንን ትተን እኛን ባዋደደን በእግዚአብሔር አጀንዳና ሃሳብ ውስጥ እንድንገናኝ ወሰንን። በሳምንቱ መሀል ረቡዕ ለጸሎትና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ እንዲሁም በየዐርቡ እየጾምን ለአዳር ጸሎት እንድንገናኝ ተስማማን። "የረቡዕ ሕብረት" የሚልም መጠሪያ ስም ሰጠነው። እዚህኛው ደረጃ የደረስነው ጥበቡ ሶማሊያ ከተወሰደ በኋላ በ70ዎቹ መጀመሪያ ላይ ነው።

"የረቡዕ ሕብረት" በእኔና በጥበቡ ታሪክ ውስጥ እንደድርና ማግ በውስጣችን ያለፈ እንደሸማኔ መወርወሪያም ለታሪካችን መልክና ውበት ለመስጠት እግዚአብሔር ከተጠቀመበት ክቡር ሕዝቡ መኻል በቢይ ሥፍራን የያዘ ነው። በረቡዕ የእህቶች ሕብረትም እግዚአብሔር በመካከላችን ማፍሰስ ከጀመረው በረከት የተነሳ ኋላ ላይ ባሎቻችንም አብረውን ፕሮግራሞቻችንን መካፈል ጀመሩ። እግዚአብሔር ለዓመታት የተጠቀመባቸውን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ የቤተሰብ አማካሪዎች፣ ሽማግሌዎች፣ ዲያቆናትና ወንጌላውያን ከዚህ ሕብረት ሲያወጣ አሳይቶናል።

ጥበቡ ገና ወደሶማሊያ መወሰዱ ሳይታወቅ ይሙት ይትረፍ ባልተረጋገጠባቸው በመጀመሪያዎቹ አስጨናቂ ቀኖች ከእኔ በፊት የጭንቀቱን ገፈት የቀመሱት እነዚህ ጓደኞቼ ናቸው። በጾም በጸሎት በእንባ በእግዚአብሔር ፊት በመውደቅ ጥበቡ በሕይወት ለመኖሩ እርግጡን የሚያውቅ ያን ሰው እስኪያገኙ ከተንቆራጠጡት መኻል እነዚህ ጓደኞቼ ናቸው። ኋላም መራራውን መርዶ ሊያረዱኝ፣ ሊያለቅሱኝ አይዞሽ ሊሉኝ ክንዶቼን ደግፈው በአምላኬ ፊት ሊያቆሙኝ፣ አምላኬ በዙሪያዬ እንደ አጥር ካቆመልኝ ሕዝብ መኻል እነዚህ ጓደኞቼ ዋነኞቹ ናቸው።

ከመክለከያ ለመሰናበት ባደረግሁት ውሳኔዬ መሠረት ሊጸልዩልኝ በዚህ ዐርብ ምሽት እነዚህ እህቶቼ ወደቤቴ መጥተዋል። ጸሎቱን ከመጀመራችን በፊት ነገሬን በጥሞና ሊያዳምጡ ለተቀመጡት ጓደኞቼ እንዲህ አልኳቸው። ~

"ያው ውሳኔዬ ግልጽ ነው። ዛሬ ጥበቡ ከጎኔ ስለሌለ ለእነዚህ እግዚአብሔር ለሰጠን ሕፃናት የሚያስፈልጋቸውን ዳቦና ወተት ማቅረብ ከእኔ እንደሚጠበቅ አውቃለሁ። ሆኖም ግን እምነትንና ረቂቅን ለማሳደግ ብዬ እየሱስን በገንዘብ አልለውጠውም። ራሴንም ሆነ ልጆቼን በምድር ለማኖር ብዬ እግዚአብሔርን ለሚያስከደው የኮምዩኒዝም አይዲኦሎጂ አገልጋይ አልሆንም። የእግዚአብሔር ቃል "ጻድቅ ሲራብ ዘሩም እህል ሲለምን አይቼ አላውቅም" ይላል። የእኔ ፈንታ ቃሉ የሚለውን አምኖ መውጣት ነው። የእግዚአብሔር ፋንታ ደግሞ የገባውን ቃል መፈጸም ነው።"

ግልጽ ነው በቃ ! በጾም በጸሎት በቆየት እህቶቼ መሀል የሰንብት ደብዳቤዬን በእግዚአብሔር ፊት ዘርግተን ጮህን ወደ አምላካችን ! በዚህ ጉዳይ ላይማ የሚደረግ ተጨማሪ ውይይትና ምክክር አልነበረም !

የጠበቁትን የሥራ መልቀቂያ ባቀርብላቸውም ሃሳቤን መቀየር እችል እንደሁ በድጋሚ ጠይቀውኛል። የሚገርመው እንዲያ ነፍሴ እየተጨነቀች የምሰራውም ሥራ ተወዶ እንድቀጥል መጠየቄ ! ምንም እንኳ የጠመንጃ ቤት ቢሆንና ሥራውን እንድቀጥልላቸው ቢፈልጉም የኮንትራት ሠራተኛነት መብቴ ተጠብቆ ሲያሰናብቱኝ በሰጋት ለነበሩ ሁሉ እፎይታ ነበረ። እንዲት ቀን ያህል እንኳ በተጨማሪ ብቆይ ሕይወቴ የሚያልፍ እስኪመስለኝ ለደረሰኩት ለእኔም ትልቅ እፎይታ ሆነ ! ሰዎች ሁሉ "እግዜር ያውጣሽ እንግዲህ" የሚሉ ይመስል ነበር በአስተያየታቸው።

* * * *

# 12

## አንቆርጫ !

ከእነዚያ እህቶቼ መካል ከሶስቱ ጓደኞቼ ጋር ተመሳሳይ ሁኔታ ነበረን። የሶስታችንም ባሎች ከአገራችን ውጭ ናቸው። የእህታችን የአጥናፍ ብርሃኑ ባለቤት ጋይም ከብረአብ እንግሊዝ አገር ሲሆን፣ የእህታችን ሶፊያ ዓለማየሁ ባለቤት ' ያለው ከበደ' አሜሪካ ነው። የእኔ ውድ ጥበቡ ደግሞ በምርኮ ሶማሊያ። ሶስታችንም ደግሞ የአባት እጦትና ናፍቆት የሚያብሰለስላቸው ልጆች ያሉን እናቶችም ነን። ስለዚህ ከሌሎቹ ይልቅ እኛ ሶስታችን በዚህ በጋርዮሹ ጉዳያችን ምክንያት ጾም ጸሎት እናበዛለን። እነሱ ባሎቻቸው ወዳሉበት ሄደው የአንድነት ኑሮአቸውን ለመጀመር፤ አጥብቀው ይጸልያሉ። እኔም እንደነርሱ ባሌን ለማግኘት አጥብቄ እጸልያሁ። ሁላችንም እንደ ወፊቷ ብር ብለን እንዳንሄድ እንደግድግዳ ፊታችን የቆመ ችግር ይዞናል ! የአጥናፍ ችግር ነርስ በመሆኗ ደርግና ጤና ጥበቃ፤ የሶፊ ችግር አሜሪካ ኤምባሲ የእኔ ደግሞ ሶማሊያ ! ሶስቱም በቀላሉ የማይደፈሩ የናስ ደጆች ናቸው ! አንዳንዴ ሶስታችን ስንጸልይ ለማደር አጥናፍ ቤት እንገናኛለን። አጥናፍ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አጠገብ ከሚኖሩት ወገኖቻችን መሀል ቤት ሰርታ ትኖራለች። አንድ ቀን ሶፊ ፈጽሞ አስቤው የማላውቀውን ሃሳብ አቀረበችልኝ።

"ሊሽ እኔና አንቺ ቤት ሠርተን በአንድነት ብንኖር ምን ይመስልሻል?"

"ሶፊዬ ! እንዴት አድርገን? ቤት መሥራት እንዲህ ቀላል ነው?"

ጓደኛችን ሶፊን ሁሌም በምታመነጨው ሃሳብ፣ በሙያዋ፣ በቀልዷ በሳቅ በጨዋታዋ እናደንቃታለን። እና በመጀመሪያ የምትቀልድ ነው የመሰለኝ። ሁኔታዋንና አነጋገሯን ሳየው ግን ስታስብበት ስለቆየችበት ጉዳይ እንደምታወራ ገባኝ።

"ቀላል ነው ሊሽ ! እግዚአብሔርም ይረዳናል። ደርግ ባሁኑ ጊዜ ቦታ የመመሪትና ቤት የመሥራት ዕድል ለሁሉም ሰጥቷል። በተለይ ከከተማ ወጣ ካልን። ለምሳሌ ኮተቤ አንድ ሰው 500ካሬ ሜትር መመሪት ይችላል። እኔና አንቺ 500ካሬ ለያንዳንዳችን ማለት ነው"

"ሶፊዬ ጥሩ ሃሳብ ነው፤ ግን እኔ..."

"ሊሽ ! ሁለት ቤት መሥራት አይጠበቅብንም። በሁለታችንም መሬት መካል ላይ አንድ ቤት ሠርተን እስከጊዜው እዚያ አብረን እንኖራለን !"

"ሶፊዬ በእኔና በአንቺ አቅም እንዱስ ቤት ቢሆን እንዴት ይሰራል?"

"የቤት ፕላን አለኝ ማዘጋጃ ቤት ማቅረብ የምችለው። ያን ዓይነቱን ቤት አሁን ለጊዜው መሥራት አንችልም፤ እስከዚያ ግን በአስቤስቶስ በቀላሉ ሠርተን መግባት እንችላለን። ሰሞኑን አንዳንድ በአስቤስቶስ የተሰሩ መጋዘኖች አይቼ ለመኖሪያስ ቢሆን ብዬ ተመኘሁት።"

በሶፊ መሪነት በሀሳቧ እየሳቅሁ እየተገረምኩም፣ ተያይዘን ኮተቤ ሄድን። እውነትም ሶፊ እንዳለቺው መሬት ይታደላል! የቀበሌ ሠራተኛ ቦታ እንዲያስመርጠን ተሰጥቶን ከሰውዬው ጋራ ወጣን። በደብረ ብርሃን መንገድ ግራና ቀኝ ሰንጥቆ የሚያልፈው ለጥ ያለ ሜዳ ነው። ቤቶች በርቀት ከመታየታቸው በቀር ባዶ ሜዳ ነው። "ከመንገድ በላይ ያለውን ነው ወይንስ ከመንገድ በታች የምትፈልጉት?"

እኔና ሶፊ እዚያው ተመካከርን። "እዚያ ማዶ ከመንገድ በላይ ያለው ትልቁን ግንብ አጥር ይዞ ጎን ለጎን እንዲሰጠን እንፈልጋለን" አልን። ድርሻችን ተለክቶ 30ብር እያንዳንዳችን ከፍለን መሬቱን በየስማችን ተረከብን! በጥቂት ቀናት ውስጥ በሶፊ ሃሳብ አመንጪነት የታለመቺው ቤት እውን ሆነች!

ያቺ የአስቤስቶስ ቤት ብዙ ታሪክ አላት። ከመጀመሪያዋ ሌሊት አንስቶ የማንረሳቸው ብዙ የአዳር ጸሎት ፕሮግራሞች ከ1970-1973 ዓ.ም በረቡዕ ሕብረታችን አካሂደንባታል። ከከተማ ራቅ ያለ በመሆኑ ጓደኞቻችን "አንቆርጫ" የሚል ቅጽል ስም ለአካባቢው አወጡለት። ቤታችን ከውጪ ስትታይ ሞላላ ቅርጸ-ቢስ ስለሆነች አንዳንዶች "33 ቁጥር አውቶቡስ" የሚል ስም የሰጧትም ነበሩ። አንድ መኝታ ቤት፣ ሳሎን፣ ኩቺናና ዕቃ ቤት ያላት ውስጧ ቀለል ያለና የደስ ደስ ያላት ቤት ወጣት! በዚያች ቤት ቋሚ ነዋሪዎች ሶፊና ሽጅዋ ሔርሜን እኔና እህቴ ሰንዱ ከሠራተኛችን ከታፈሱ ጋራ ነበርን። የእኔ ልጆች እምነትና ረቂቅ ወላጆቼ ሊንከባከቧቸው ግድ ስላሉኝ ናዝሬት ናቸው። እኔ እንዳመቸኝ እየሄድኩ ላያቸው ተስማማን፤ እስከጊዜው።

በጥቂት ጊዜ ውስጥ በአካባቢው ለሚገኙ ወገኖች በተለይ ለኮተቤ የመምህራን ማሰልጠኛ ተማሪዎች የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማካሄድ ጀመርን። በዚያች አንድ ትልቅ ግንብ አጥር ስር ተተግነን በሰራናት ቤት ውስጥ ሆነን በግራና በቀኝ ያለውን ሜዳ፣ "እግዚአብሔር ሆይ ውረሰው" እያልን ስንጸልይ አስታውሳለሁ። ትንሿ ቤታችን ውስጥ ትልቁ እግዚአብሔር ይመላለስ ነበርና ትላልቅ መንፈሳዊ ሥራዎች ሰራባት። ሰዎች ድነዋል፣ ተጽናንተዋል፣ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል። "ከኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ እናንተ ቤት ለጸሎት እንመጣ ነበር" ያሉኝ ወገኖችም እስከ ዛሬም አልፎ አልፎ ያጋጥሙኛል።

አንድ ቅዳሜ እቤት ሳለሁ በር ተንኳኳ። በርከት ያሉ የጌጃ ሰፈር ቃለሕይወት ምዕመናን ናቸው። ያን "ውረሰው" እያልን እግዚአብሔርን ስንለው የነበረውን አካባቢያችንን፣ ሊወርሱት/ ሊመሩ መምጣታቸው ኖሯል! ከመካከላቸው የቦታው ከከተማ መራቅ ያስጋቸው ሰዎች "እነዚያ ሁለት ሴቶች እንኳ ከመኻል ከተማ እርቀው መኖር ከቻሉ እኛ የማንችልበት ምክንያት የለም" ብለው ለመወሰን እንዴት እንደረዳናቸው ነግረውናል። ባንድ ጊዜ አሥራ ስድስት ቤተሰቦች ቤት ሠርተው ገቡ! ደስታችን ብዙ ሆነ፤ የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜም በዛልን።

አንድ ቀን ኃይለኛ ነፋስ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ወረደ። ዘንቦና ነፍሶ ቢያባራ ጥሩ ነበር። እኔና ሶፊ ቁጭ ቁጭ ያደረግነውን የአስቤስቶስ ቤታችንን ጣሪያ እያነሳ ወዲያ ማዶ አሽቀንጥሮ ጠበቀን እንጂ! ከሥራ ወደቤት ስመለስ የደረስኩት ቤታችንን ዝናብ አሹቋት ነው! ደግነቱ ባብዛኛው ጣሪያው የተጎዳው የኩችናችንና የዕቃ ቤታችን ነበር። ጊዜው ስለመሸ ምንም ማድረግ አልተቻለም።

መኝታ ክፍላችን አለመነከቷ ኮከብ ስንቆጥር ከማደር አውጥቶናል! ወገኖች ግን የሆነውን ሲሰሙ አዘኑ። ብዙዎችም የእኔና የሶፊ ነገር ገረማቸው! ባልታሰረ ጣሪያ ስር መኖራችንን ባወቁ ጊዜ የቤተክርስቲያን መሪዎቻችንና መሀንዲስ ወንድሞቻችን እነዚያም ጎረቤቶቻችን ሁሉ ልባቸው ተነካ፡ አዳዲስ አስቤስቶስ ከነማሰሪያው ገዝተው አምጥተው ጣሪያችንን በቅጡ እያሰሩ አለበሱልን!

ከጥቂት ጊዜ በኋላ አምላካችን ጸሎታችንን ሰማና በመጀመሪያ የእህታችን የአጥናፍንና የልጆቿን በር ከፍቶልን ወደ ባለቤቷ ወደ ጋይም ሄደች። ዓመት ባልሞላ ጊዜ የሶፊንና የልጇን በር እንዲሁ ወለል አደረገልንና ወደ ባለቤቷ ሄደች! የእኔና የልጆቼ ከጥበቡ የመገናኛው ጊዜ በእግዚአብሔር እጅ ውብ ሆኖ እንደሚፈጸም ከሙሉ እምነት ጋር ሆኜ በፊቴ ወደሚጠብቀኝ አገልግሎት አቀናሁ።

ከመከላከያ ከወጣሁ በኋላ "ከእንግዲህ የምሰራው ከእምነቴ ጋር በማይጻረር ክርስቲያናዊ ድርጅት ውስጥ ብቻ መሆን አለበት" ስል በውስጤ ቆርጫለሁ።



የረቡዕ ኅብረት ጓደኞቼ



የረቡዕ ኅብረት ልጆች

****

*ብርሃን!*

ለሦስት ወራት ያህል ልቤ የሚፈቅደውንና ለመንፈሴ የሚመቸኝን ሥራ ፍለጋ በጊዜው የነበሩትን ክርስቲያን ተቋማት በሮች ማንኳኳቴን አስታውሳለሁ። ፍለጋዬን ያቆምኩት አድራሻዋ አራት ኪሎ ከነበረው "ብርሃን መጽሔት" ቢሮ ስደርስ ነው። ዋና አዘጋጅዋ ወንድማችን አቤሴሎም ሞገስ ነበረ። በሩን ከፍቼ ስገባ ካገኘኋቸው የብርሃን ሰራተኞች አንዱ ወንድማችን አምሳ አለቃ ገዛኸኝ ደስታ ነበር። በዘፈን ዓለም የነበረውን የመድረክ ዝነኛ አስተዋዋቂነት፣ ስለተገለጠለት የክርስቶስ ፍቅር ንቆ ጌታ ክርስቶስን በስደትና መስቀሉን በመሸከም የተከተለ ቆራጥ! ጋሽ ገዛኸኝን ሳየው ደስ አለኝ፤ በእምነቱና በሕይወት ምስክርነቱ የማከብረው ወንድም ስለሆነ። ጸሐፊዋ እቴነሽ እንዲሁም የምሩ ሌላው የብርሃን መጽሔት ቢሮ ሠራተኞች ናቸው። የመጣሁበትን ጉዳዬን ስነግረው ጋሽ ገዛኸኝ አፍታም ሳይቆይ ወንድም አቤሴሎም ቢሮ ይዞኝ ገባና አስተዋወቀኝ። አቤሴሎም ፈገግታ በተሞላው ፊቱ ተቀብሎ ስንነጋገር እንዲህ አለኝ፤

> "መቼም ለዚህ ሥራ በጣም የምታስፈልጊን ሰው መሆንሽ ጥያቄ የለውም። በጥራትም ሆነ በብዛት ብርሃን ተዘጋጅታ ብትወጣ ፈላጊዎቿ ብዙዎች ናቸው። ትልቁ ችግራችን ግን አንቺን በሙሉ ጊዜ ሠራተኛነት የምንቀጥርበት ባጀት ነው። ያለሽን የሥራ ልምድና



እምነትና ረቂቅ በሦስትና በአራት ዓመታቸው

ብቃት የሚመጥን የወር ደሞዝ ብርሃን የላትም።"

"አይ! ምንም አይደል ስለገንዘቡ። ግማሽ ቀን ሥራስ እንዴት ነው?"

"እሱማ ይቻላል እኔ እንዲያው ከብዶኝ ነው እንጂ! አንቺ በዚህ ሁኔታሽ ብቻሽን የምታሳድጊያቸው ሕፃናት ይዘሽ!"

"እግዚአብሔር ይባርክህ ስለ ቅን ሃሳብህ፤እኔ ግን ያለምንም ሥራ ከምቀመጥ ግማሽ ቀንም ቢሆን ሥራውን ብጀምር ደስ ይለኛል።"

ብርሃን መጽሔት ውስጥ የግማሽ ቀን ሠራተኛነቴን በደስታ ተቀበልኩ። በጸጥታ ለመሆንና ለመጻፍም እንዲያመቸኝ አንዲት ትንሽዬ ክፍል ቢሮዬ ሆነች። ትላልቅ ጠረጴዛና ወንበር የለመደው ስጋዬ እንኳ አልተቀየመም። ነፍሴ ሐሴት አደረገች። መንፈሴም አረፈ። ወዲያውኑ ወደሥራዬ ተሰማራሁ። ድንገትም ራሴን አገኘሁት! ተመችቶት! በማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ ኋላም በመከላከያ ያጣሁትን ራሴን!

"እግዚአብሔር ሆይ አንተን ሳላገለግልበት፤ የመንግሥትህን ሥራ ላልሰራበት ምን አደርጋለሁ እዚህ??" መልስ ያጣሁለት የዓመታት ጥያቄዬ ተመለሰ! ያን ሁሉ መሰናክል ያለፈው የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን የአንድ ዓመት ኮርስ ለምን እንዳስፈለገ ገባኝ፤ ውስጤ በደስታ እየፈነደቀ እኔንና ሥራውን ያገናኘንን አምላኬን ባረክሁት። የምጽፋቸው ወይንም እንዳዘጋጃቸው የሚመጡልኝ ጽሑፎች በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ የተመሰረቱ ናቸው፤ የእግዚአብሔርን ሕልውና የሚያሳዩ የሰው ልጆችን የሕይወት እንቆቅልሽ የሚፈቱ ናቸው። ለመጀመሪያ ጊዜ በምሰራው ሥራ ደስተኛ የሆንኩባት ብርሃን የአምላኬን ሁሉን ቻይነት የምገልጥበት መድረክ ሰጠችኝ። ምናልባትም የብርሃን መጽሔትን አገልግሎት ሊያጨናግፍ ይችላል ብዬ ስላሰብኩ ስሜን በመጽሔቷ ላይ ላለማውጣት ከአቤሴሎም ጋራ ወሰንን።

የሃሳባውያን ሃሳብ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር አምላክ ሕያው እንደሆነ ብርሃን እውነትን ወደብርሃን የማውጣት ተልዕኮዋን ቀጠለች። ተጨባጭ ማስረጃ ለሚፈልገው አይዲኦሎጂ በተጨባጭ የተረጋገጡ ነገሮችን ይዛ መቅረቧ በዛ። ሊስተባበሉ የማይችሉ ታላላቅ ተአምራዊ ፈውሶች ኢንተርቪው ከተደረጉት ባለታሪኮች ጋር ይወጣሉ። ደርግ ወንጌልን ለማፈን ስደት በቤተክርስቲያን ላይ ባጧጧፈበት ሰዓት ብርሃን የክርስቲያኖች ልሳን በመሆን አስደናቂ አገልግሎት መስጠት በዛላት።

ደቡብ ውስጥ (ይርጋለም ይመስለኛል) በአንዲት ሴት ሕይወት ስለተፈጸመ ተአምር ለማጣራትና ከእርሷም ጋር ቃለመጠይቅ ለማድረግ አቤሴሎም ሄደ። ነገር ግን በጉጉት ከምንጠባበቀው ታሪክ ጋራ ወንድሜ አቤሴሎም ታስሮ ወህኒቤት እንደ ገባ ተረዳን። ብርሃን ግን እውነትን የመግለጥ ተልእኮዋ ሊታሰር አልተቻለም። አንድ የብርሃን አዲስ እትም በወጣ ቁጥር ተፈላጊነቷ እንደጣፋጭ ትኩስ ኬክ ነበርና የደርግ መንግሥት ይቺን የ እውነት ድምፅ ለማፈን መረቡን ዘረጋ።

"እነማን እንደሆናችሁ እናውቃለን! ጸረ አብዮት ሥራችሁን ብታቆሙ ይሻላል።" "ከደርግ ጽሕፈት ቤት ነው" እየተባለ ወደቢሯችን የሚደወልልን ስልክ ልንሰራ የማንችልበት ሰዓት እየተቃረበ የመምጣቱ ማስጠንቀቂያና ቀይ ምልክት ነበር።

እኔም ለእኔነቴ ማስጠንቀቂያ ሰጥቼዋለሁ። በየትኛውም ሰዓት ብርሃን በምታስተላልፈው

እውነት ምክንያት አድራሻዬ እስር ቤት ሊሆን እንደሚችል አስቤ ራሴን አዘጋጅቻለሁ። የሚቀጥለው የደርግ ዒላማ እኔ ልሆን ስለምችል በውስጤ ውሳኔዬ እየጠበቀ መጥቷል። የአቤሴሎም ዕጣ መቼ ለእኔ እንደሚደርስ ለላውቅምና ልሰራ የምችልባት አንዲት ቀን ብቻ እንደተሰጠው ሰው ሆኜ ራሴን በሥራ ጠመድኩት። ጠዋት ከቤት ልጆቼን ስሜ ወጥቼ ማታ ታሪኩ ሌላ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ለቆራጥነት ረድቶኛል። አቤሴሎም እስር ላይ በመሆኑም የብርሃን እትም ከጊዜው እንዳይዘገይ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶችን ከጋሽ ገዛኸኝ ጋራ እየተረዳዳን ተረባረብን።

ከብርሃን ሌላ ቤተክርስቲያንም ከባድ ስደት ላይ የነበረችበት ዘመን ነበር። ስደት ለሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን አዲስ ነገር አልነበረም። በኃይለሥላሴም ዘመን የኖረችበት ነው።

የንጉሡን ሥልጣን የገረሰሰው ደርግም ቢሆን ቤተክርስቲያኒቱን የአብዮቱ ጠር ብሏታል። ምዕመኑ የስደቱን አይቀሬነት ልቡ እያወቀው "ቁልፉን ስጡን ቢሉን እንኳን..." ሲል በሰራው የቤተክርስቲያን ሕንፃ የጀመረውን አገልግሎት ደርግ አስቁሞ ሕንፃውን ወርሶታል። የአንድን ሕንፃ ደጅ ሰይጣን ዘጋሁ ሲል፣ እግዚአብሔር ደግሞ የብዙ ምዕመናንን ቤቶች ለአገልግሎት በመክፈቱ በቤተክርስቲያን በኩልም ሥራ የበዛልን ዘመን ነበር። በቤተክርስቲያን "የቅዱሳን አገልግሎት" ኋላም ደግሞ ከዲያቆናት አንዷ በመሆን የድርሻዬን አገልግሎት ለማበርከት እሮጣለሁ። ከሥራ ሰዓት ውጪና በእሁድ በቅዳሜው እጅግ ብዙ የቤት ለቤት አገልግሎት ዕረፍትም የሌለው ሁኔታ እንደነበረ አስታውሳለሁ።

****

*ወርቁ!*

የፋሲካን በዓል ከወላጆቼና ከልጆቼ ጋር ለማሳለፍ ከጓደኛዬ ከሶፊና ከልጅዋ ከሔሪዬ ጋር ናዝሬት ሄደናል። በዚህ ወቅት አብራን ትኖር የነበረችውን እህቴ ሰንዱን ወደ ናይሮቢ ኬንያ ሸኝተናታል። እጮኛዋ ጥበቡ ዓለማየሁ ኬንያ በሚገኘው ስኮት ባይብል ኮሌጅ ይማር ነበር። ትምህርት ቤቱ ለእሷም ስኮላርሺፕ ሰጥቷት ነው።

ልጆቼ እምነትና ረቂቅ ከርሜ ባየኋቸው ጊዜ ሁሉ የእያት ቅምጥሎች ለወላጆቼ ዓይን ማረፊያዎች ሆነው በጥሩ እንክብካቤ ተይዘው ስለማገኛቸው እጽናናለሁ። "የእናትነት ፍቅሬንና እንክብካቤ አትድዬባቸው እንዳይሆን" የሚል ሃሳብ ውስጤን ያብሰለስለዋል። ሆኖም ግን እኔጋ ቢሆኑ በባተሌነቴ የበለጠ ልጎዳቸው እንደምችል ይታወቀኛል። በእናቴ ተመልካችነት በጥሩ ሞግዚት ንጽሕናቸውና ምግባቸው በሚገባ ይጠበቃል። የቤቱ "ንግስቶች" ናቸው። እስከልጎዳቸው ድረስ ጨዋታቸውንና ምቾታቸውን የሚያግድ ነገር እንዳይኖር ከመንገዳቸው አባቴ ያስነሳላቸዋል። እናቴም ቢሆን ያው ናት። እንዳንዴ ለየት ያሉ እንግዶች የሚመጡ ከሆነ ሳሎን ሶፋዎች ላይ የምታደርጋቸው መደገፊያ ትራሶች ልዩ የጠረጴዛ ልብሶችና ጌጦች እንግዶች ከተሸኙ በኋላ እምነትና ረቂቅ መጫወቻ ስለሚያደርጓቸው አባቴ እየሳቀ፡- "በይ፣ በይ፣ አልማዜ! አይተንልሻል ይበቃናል ቤት ማስጌጡ! ልጆቹ ይጫወቱ!" ይላት ነበረ። ናዝሬት ላያቸው በሄድኩ ቁጥር ወይንም እነሱ አዲስ አበባ ሲመጡ በናፍቆት እላዬ ላይ መንጠላጠል፤ እያቀፉ ጉንጮቼን መሳም በግራና በቀኝ አብረውኝ መቀመጥ የማይቀር ነው። እኔ ስሄድ ደግሞ ተራው የወላጆቼ ይሆናል። አባቴ ጥሩና አባታዊ ፍቅር በመስጠት ረገድ በጥበቡ አለመኖር የነበረውን ክፍተት ብዙ ሸፍኖልኛል።

ፋሲካን ውለን እንደነገ ወደ አዲስ አበባ ልንመለስ ከእራት በኋላ ወደየመኝታችን መሄጃችን ላይ ነው። ልጆቼን ጸልዬና ስሜ ሲነጋ ወደ አዲስ አበባ እንደምመለስ ነግሬ አስተኛቻቸዋለሁ። እኛም የቤተሰብ ጸሎታችንን ጨርሰናል። በአካባቢው የሌለሁ መስሏት እናቴ ድምጽዋን ዝቅ አድርጋ

ለጓደኛዬ እንዲህ ስትል ሰማኋት፥

"ሶፊዬ እባክሽን ለአንዳንድ ጉዳይ የማውለው ገንዘብ ስለቸገረኝ የወርቅ ጌጦች አሉኝ ወስደሽ ብትሸጪልኝ?"

ጆሮዬ በሰማው ነገር ልቤ በትልቅ ኃዘን ተመታ። እንባዬ ድቅን ድቅን አለ፤ ብቻ በአምላኬ ፊት ባስቸኳይ መንበርከክ ፈለግሁ። ሌሊቱ እሰኪነጋ ከተንበረከክሁበት አልተነሳሁም!

እናቴ ጌታ ክርስቶስን ካወቀችበት ጊዜ አንስቶ ለእግዚአብሔር ቤት በደስታና በፍጹም ፍቅር የተለያዩ ስጦታዎችን ያበረከተችበትን ጊዜዎች አስታውሳለሁ። ወርቅም ቢሆን። የዛሬው የልቤ ኀዘን ምክንያቱ ለወርቅ ስላለኝ ፍቅር አይደለም። አምላኬ ከእልፍ የተመረጠ ወርቅ ከሆነልኝ ወዲያ ያ ሁሉ የወርቅና የጌጣጌጥ ፍቅር ከውስጤ ተጠራርጎ መውጣቱን አውቃለሁ። ወርቅ ከችግር የተነሳ መሸጡ ነው ያሳዘነኝ። ወላጆቼ በሚችሉት ሁሉ እኔን ለመርዳት የኔንና የጥበቡን ልጆች በሚያሳድጉበት በዚህ ጊዜ በመሆኑም ቁስሌን ከፋኛ ነካካው። ጥበቡን ለሥራው እንደወሰደው ሥራውንም ሲጨርስ ወደእኛ እንደሚመልሰው እግዚአብሔር ተናግሮኛል። እኔንና ልጆቼን በሚመለከት እግዚአብሔር ሙሉ ኃላፊነትን እንደወሰደም በተግባር ዐይቼዋለሁ። ደግሞ እግዚአብሔር እኮ "....እርሱ የሚተወውን ሸለቆ እኔ እሞላዋለሁ።..." ብሎኛል "ጥበቡ ወደሶማሊያ በምርኮ ተወስዷል" የሚለውን ክፉ መርዶ በሰማሁ ቀን ሳለቅስ። ስለዚህ እኔም በዚህ ምሽት መልሼ፥-

"ብለኸኝ የለ እግዚአብሔር ሆይ? ይህን ያልከኝ አምላኬ ከጎኔ እያለህ እንዴት? ይህ ሸለቆ እንዴት ባንተ አልተሞላም ? ባሪያህን ለሥራህ እንደወሰድከው የተናገርከኝ አንተ እያለህ እንዴት? እሱ ያንተ የጌቶቹ ጌታ የሠራዊት አምላክ ሠራተኛ ሆኖ እንዴት?"

ብቻ የእኛ ባላደራ የሰማዩ አባቴ እያለ በሰማሁት ነገር፡ልቤ እጅግ መሰበሩን የሆዴን ብሶት ነገርኩት። በእንባዬ እግሮቹን አጠብኩ። የአምላኬንም ታማኝነት እስከዚያችም ምሽት ያደረገልኝን ምሕረትና ቸርነት በፊቱ እየቆጠርኩ በእንባ አመሰገንኩት። ይህም ዛሬ የሰማሁት ቢሆን በእርሱ ዐይን ፊት እጅግ ቀላል እንደሆነ በማመን ንግግሬ ስሜቴና ሀሳቤ ሊገባው በሚችል በአምላኬ ፊት ሰሀታት አሳለፍኩ። ሌሊቱም ወለል ብሎ ነጋ። ጌታም በዚያች በተንበረከኩባት ስፍራ መጥቶ ነበርና ልቤ በሚያስደንቅ መጽናናት ተሞላ። ከዚያ የጸሎቴ ስፍራ ስነሳ አምላኬ ዙፋን ስር ያፈሰስኩት እንባ እንደታብሰ ጸሎቴም እንደተሰማ በሙሉ እርግጠኝነት ተነሳሁ። የሌሊቱ እንባና ኀዘን ከላዬ ተገፏል። የምስጋና መንፈስ ተላብሼ ነፍሴ በዝማሬ ተሞልታለች። "ሶፊዬ ባለፈው ሌሊት ጌታ በዚህ ይመላለስ ነበር " አልኳት።

ወደ አዲስ አበባ ከሶፊ ጋር ስንመለስ የሚደባብሰው የእግዚአብሔር መንፈስ አሁንም ይሰማኝ ነበር። ከምስጋና ዜማ ሌላ እንደበቱ እንዳች መናገር አልቻለም። በቀጥታ ወደ ትንሿ የብርሃን ቢሮዬ ገብቼ በፊቴ የተደቀነውን ሥራዬን በምስጋና ተያያዝኩት። ድንገትም የቢሮዬ በር ተንኳኳ። ጋሽ ገዛኸኝ ነበረ፤ እሱም በምስጋና እግዚአብሔርን እየባረከ እንዲህ አለ፥-

"ሊሸ ዛሬ ሌሊት መንፈስ ቅዱስ ስላንቺ ብዙ ሲጸልይ በውስጤም እግዚአብሔርን ስባርክ አደርኩኝ። የሚገርም ሌሊት ነበረ። የእግዚአብሔር መንፈስ ስላንቺ የብርሃንን የቦርድ አባሎች ማነጋገር እንዳለብኝ ተናግሮኛል። የዛሬው ሥራዬ እሱ ይሆናል። እግዚአብሔር ባንቺ መምጣት ብዙ ባርኮናል። ብርሃን የሚያሰራሽ በግማሽ ቀን ሰራተኝነት ነው። አንቺ ግን ሙሉ ቀን እዚሁ ነሽ። ወንድማችን አቤሴሎም ከታሰረማ እጥፍ ሆኗል የተጫነሽ ኃላፊነት።"

ይደንቃል የእግዚአብሔር ሥራ! በዚያች በማትረሳኝ ቀን ሁለት ነገር በተከታታይ ሆነ። ጋሽ ገዛኸኝ በእርግጥ ከእግዚአብሔር መንፈስ በነበረ ሃሳብ ተነድቶ ነበር የወጣው! ሲመለስ የብርሃን የቦርድ አባላት እኔን የሙሉ ጊዜ ሠራተኛቸው አድርገው የወር ደሞዜ በእጥፍ ከፍ እንዲል ወሰኑ!

ተገርሜ አምላኬን በምስጋና እየባረክሁ ሳለ ከወርልድ ቪዥን ቢሮ አንድ ስልክ ተደወለልኝ። "ሊሻን እባክሽን የሚመችሽ ከሆነ በትርፍ ጊዜ የሚሰራ የትርጉም ሥራ አለን ዛሬ ብቅ ብለሽ ብንነጋገር?!"

*ሥራው፡-* ልጆቻቸውን ለማሳደግና ለማስተማር የገንዘብ ድጎማ ላደረጉላቸው አሜሪካውያን በአማርኛ የሚጽፉትን ደብዳቤ ወደ እንግሊዘኛ መመለስ። ወርልድ ቪዥን ሄጄ ሥራውን በዚያኑ ቀን ተረክቤ ተመለስኩ! የእግዚአብሔር ቃል፡- "ማታ ለቅሶ ይሆናል ጠዋት ግን ደስታ" ያለው ትገዘ አለኝ። ያለፈውን ሌሊት ለቅሶዬን ወደ ደስታ የለወጠልኝን አምላኬን እያመሰገንኩ በ33 ቁጥር አውቶቡስ ሳላውቀው "እንቆርጫ" ቤታችን ደረስኩ። ከዚያን ቀን በኋላ የወር ገቢዬን ከዚህ በፊት የሰራሁባቸውን መሥሪያቤቶች ሦስት ጊዜ የሚያጥፍ ሆነ! አምላኬም እንደተናገረኝ ጥበቡ የተወውን "ሸለቆ" በድንቅ እየሞላውና በአባትነቱ እየሸፈነው አኖረን።

****

## *"ምስኪኖችን ትሰበስብልኝ ዘንድ..."*

የኔ ውድ ጥበቡ! ደናን ወህኒ ቤት ለታጎረው ምስኪን ሕዝብ ቀኑን ሙሉ በእግዚአብሔር ጸጋና ኃይል ማድረግ ስለቻለው ሁሉ እያሰበ፡- "እግዚአብሔር ሆይ "ምስኪኖችን.." ያልከኝ እነዚህን ማለትህ ነው? በእርግጥ እግዚአብሔር ሆይ ይህ ከአንተ ብቻ ምሕረት የሚያሻው ምስኪን ሕዝብ ነው! ለዓላማህ በዚህ ስለተገኘሁ አመሰግንሃለሁ!"

ያ ምስኪን ሕዝብ... ሕጻን፣ ሴት፣ አሮጊት፣ ሽማግሌ... በዐይነ ሕሊናው እያለፈ፡- "እግዚአብሔር ሆይ እነዚህ ሁሉ ምስኪኖች ናቸው። የዚህን ሕዝብ መከራ ተካፋይ አድርገኸኛልና እውነተኛ አገልጋይህ ሆኜ እንድገኝ እርዳኝ።"

በዚህ ሃሳብ ውስጥ እያለ ቀን ላይ አንድ የሰማው ጭምጭምታ ትውስ አለው። እስረኞቹን ከደናን ወደሌላ ቦታ የማንቀሳቀስ ጭምጭምታ። ወዴት ሊወስዱት ይሆን ይሄን መከረኛና ምስኪን ሕዝብ?

ወሬው እውን ሆነ። ከባድ የጭነት መኪናዎች ሶማሌዎቹ አቅርበው እስረኛውን እያጣደፉ ይጭኑት ገባ። ግን ወዴት? ጉዞው የተጀመረው ማታ ሆን ተብሎ ነው። ያለምርጫው ተገዶ ለሌላ ፍዳ የተጫነው ሕዝብ አቅጣጫውን መለየት እንዳይችል ተፈልጎ ነው። ጥበቡና ልጆች፣ ሴቶችና ሕሙማን ወደ ኋላ በሁለተኛውና በሶስተኛው ቀን ነው የተወሰዱት። ቦታው የሶማሌ መንግሥት የሩዝ እርሻ ሲያቋቁም እንደሰፈረ ጣቢያ የተጠቀመበት መጋዘኖች ያሉበት ስፍራ ነው። ከደናን ለሚጋዙት ወገኖቻችን ግን በቂ መታጎሪያ የለውም። ስለዚህ ቀድመው ያጓጓዙዋቸው ምርኮኞች የተወሰዱት ለተከታይ ወገኖቻቸው ጊዜያዊ ተጨማሪ መታጎሪያ ስፍራ ለማስለቀቅ ነው።

እነዚህ ወገኖቻችን ከደናን ወደዚህ አዲስ ስፍራ ሲወሰዱ እንዴት ያለ የጭንቅ ጉዞ እንደተጓዙ ሲተርኩት ያሳዝናል። ጨለማን ተገን አድርገው የጀመሩት ያ አሰቃቂና ረዥም ጉዞ፣ በጭንቅ የተፈጸመው ቁጢጥ እንዳሉ ነበር። ቆሞ ማየት፣ ለሽንትም ሆነ ለመጸዳዳት ከተጫኑበት መውረድ ሳይፈቀድላቸው። በተቅማጥና በሆድ ሕመም የተያዙ ሰዎች መኖራቸው እየታወቀ። ሕይወት እንዳላቸው የሰው ልጆች ሳይሆን በድንና ነፍስ አልባ ነገሮች የጫኑ ይመስል ያን ሕዝብ ይዘው ወደማያውቀው ስፍራ ነጎዱ። ከስቃይ ወደስቃይ፣ በስቃይ ለሌላ ስቃይ!! ሲጓዙ ውለውና አምሽተው እኩለ ሌሊት ሲሆን አንድ ቦታ ደረሱ። ለዚያ ሁሉ ሕዝብ የሚበቃ የመታጎሪያ ቦታ እንኳ የሌለበትና አስጨናቂ ስፍራ ነው። ከኢትዮጵያ የሚነሳው የዋቢ ሸበሌ ወንዝ ሶማሊያ ድረስ ከተጓዘ በኋላ አሸዋ ወስጥ ሰምጦ የሚያልቅበት። "ሐዋይ" ይሉታል። ስፍራው ጨፌና ረግረግ ቦታ፤ የወባ ትንኝ እባብና ጊንጥ ዘንዶ.. የጫካ አውሬዎች መናኸሪያ ነው። እስረኞቹ ወደዚያ የተወሰዱበት

ዋና ምክንያት ለሶማሌ መንግሥት የሩዝ እርሻ ለከባድ የጉልበት ሥራ ተፈልገው ነው። ከኢትዮጵያ ድንበርም ራቅ ያለና ወደመኻል የገባ ስለሆነ ሶማሌዎቹ ለጥበቃ እንዲመቻቸው ታቅዶ ነው።

****

*"የእውነት ያለህ! የፍርድ ያለህ!"*

ይህ በሶማሌ ምድር በግፍ የተገደሉት የቁጥራቸው መጠን የማይታወቅ የምንዳዬና የብዙ መሰል ወገኖቻችን ደም ድምጽ ነው። ምንዳዬ የአዲስ አበባ ልጅ ነው። ከደናን ወደ ሐዋይ በተወሰዱ ጥቂት ጊዜ ውስጥ አንዱን ቀን ነው። ሕዝቡን የሚያሰፍሩበት በቂ ቦታ ሳይኖራቸው ስላንቀሳቀሱት ባንድ ቤት ሦስት መቶና አራት መቶ እያደረጉ አጉረውታል። ይህን የቦታ ጥበት ለማቃለል እስረኞቹ በወታደር ታጅበው የሆነ ነገር እየሰሩ ነው። ድንገትም ውካታና ግርግር ተፈጠረ። የተከመሩትን እንጨቶች ሲሰቡ አይጦች ግር ብለው ወጡ። ምንዳዬ በትልቅ ድንጋጤ በርግጎ ከአይጦቹ ለመሸሽ ባደረገው ሙከራ ወታደሩን ሳያውቅ ገፍትሮ ጣለው። በስፍራው የነበረው አቶ ተሰፋዬ በለጠ በዕለቱ ስለተከሰተው ዘግናኝ ሁኔታ እንዲህ አለ።

*"ምንዳዬ በዚያ መልኩ የበረገገው የአዲስ አበባ ልጅ በመሆኑና አይጦች በዚያ መጠን አይቶ ስለማያውቅ ነበረ። ወታደሩን ደጋግፈን አነሳነው፤ መሣሪያውንም ሰጠነው። ወታደሩ ግን" መሣሪያውን ሊቀማኝና ሊያመልጥ ነበረ" ሲል በሀሰት፣ ሁኔታውን ከሩቅ ያይ ለነበረ ሁሰማን ቡር ለሚባል መቶ አለቃ ተናገረ።*

*ቋንቋውን የሚያውቁ ሰዎች ለመቶ አለቃው ሊያስረዱ ሞከሩ። እኔም በእንግሊዘኛ እንዳስተረጉም ተጠራሁ። ቁጭ ባልንበት ግን የፊጥኝ የታሰረው ምንዳዬ በጥይት ተገደለ። እሱ የፊጥኝ ታስሮ እፊታችን ሲገደል እኔ በከባድ የራስ ምታት ከዚያን ቀን ጀምሮ ታመምኩ። ለምንም አይነት መድኃኒት ያቃተ፣ ልጁ በተገደለበት ሰዓት እየለየ የሚመጣ ከባድ የራስምታት በሽታ ነበር።*

*በዚያ ከባድ ራስምታት እየታመምኩ ሳለ አንድ ጊዜ ለሕጻናት የሚሰጥ ነጻ ቴምር መጣ። "ተሰፋዬ! ቴምሩን ከሚያድሉት ሰዎች መኻል አንተን መድቤያለሁ" አለኝ። ሰዓት ጠብቆ እንባዬን እንደዝናብ ለሚያንዠቀዥቀው ራስምታት ዶክተር ጥበቡ የተጠቀመበት ሳይኮሎጂ እሱን ነበረ። ከልጆች ጋር እየተንጫጨ ቴምር ማደል። ያን ቴምር በየቀኑ በማደል ሥራ ውስጥ ተሰማርቼ ሳለሁ አንድ ቀን ያ ሲያሰቃየኝ የኖረው ራስምታት ከላዬ ተገፎ አገኘሁት። ሌሎች ወገኖቻችን የአእምሮ በሽተኞች ሆነው አገር ስንገባ ቀጥታ ወደአማኑኤል ሆስፒታል የተወሰዱ አሉ። እኔ ግን ዛሬ ዘመን ተጨምሮልኝ፣ ባለአእምሮ ሆኜ በአገር አቀፍ ኃላፊነት ቤተክርስቲያንን አገለግላለሁ። እኔን ባዩ ቁጥር የቃለሕይወት ቤተክርስቲያን መሪዎች ዶክተር ጥበቡን ብዙ ያመሰግናሉ። እዚያ ሳለን ብዙ ጊዜ ተስፋ እየቆረጥኩ በግራ በቀኝ የሚሞቱትንም እያየሁ "አይ የኔ ነገር! ከዚህ ሁኔታ ማን ሊያወጣኝ ይችላል? በቃ! እዚሁ ሞቼ መቅረቴ ነው" ብያለሁ። ይሄን ደግሞ እኔ ብቻ ሳልሆን ብዙዎቹ ብለውታል፤ ተስፋ ከመቁረጥ የተነሳ። ዶክተርን ግን ዝም ብዬ ሳየው ሕይወቱ ራሱ "ትምህርት ቤት" ነበር ለእኛ። እንባበን እንባበን የማንጨርሰው። እኛ ደከመን ብለን ልብሳችንን የሚያጥብልን ስንፈልግ፣ እሱ የራሱን ልብስ ሲያጥብ እናየዋለን። እንደ ዶክተር እንኳ የራሱን ልብስ ሲያጥብ እኛ ምን ማለታችን ነው!" ብለን ራሳችንን እናበረታታለን።*

*ዶክተር በዚያ እስር ቤት የሚያደርገውን ሁሉ ሳስተውል፣ "ይሄ ሰው ሌላ ቦታ ለመኖር ብዙ እድል እያለው ለዚህ ሕዝብ ብሎ አይደለም ወይ ይሄን ሁሉ ስቃይ የሚያየው?" እላለሁ። ዶክተር የጥቅም ሰው አልነበረም። ሞቃዲሾ ሄዶ ለመኖር ሲችል እሱ ግን ከወገኖቹ ጋር መሆን መረጠ። ወገኖቹ*

*እየተሰቃዩ ደልቶት እንዲኖር አልፈቀደም። ለሶማሌዎቹም ተርፎ ነበር። ሶማሌዎቹ "የእግዚአብሔር ባሪያ" ወይም "ኢ.ላህ" ይሉት ነበር። አንዲት ሶማሊያዊ ምጥ ይዟት ስትሰቃይ ዶ/ር ጥበቡ አዋለዳት። የተወለደውን ልጅ "ጥበቡ" አለችው። በየመንደሩ ለህክምና ሲዞር የሚያገኘውን መድኃኒት እየሰበሰበ ለምርኮኞች ያመጣ ነበር። ትንሽ ገንዘብ ካገኘም የሚያውለው ለምርኮኛው ጥቅም ነበር። እሥር ቤት በየጠዋቱ ድብደባ የነበረብን ቢሆንም በእርሱ የተነሳ ግን ከብዙ ሥቃይ ድነናል። ባለሥልጣኖቹ ይቀርቡታል ጭንቀታችንን የሚያደርስልን እሱ ነበር። ዶ/ር ጥበቡ መንፈሳዊ አገልግሎትም ይሰጥ ነበር። በቀን ሦስት ጊዜ የጸሎት ጊዜ ነበረው። ሌሊት ተነስቶ መጸለይ ይወዳል። ሲጸልይ ድምጹን ከፍ አድርጎ ስለሆነ ሶማሌዎቹ ካልሰሙት ምን ሆነ ይላሉ። ዶክተር፣ መምህራችን አባታችን ጠበቃችን አጽናኛችን ሁለንገራችን ሆኖ ነው ለምድራችን ያበቃን፤ ባለአደራሽም ያደረገን። ስም የመስጠት ስልጣኑ ቢኖረኝ ዶክተር ከምለው ሐዋርያው ጥበቡ ብዬ ብጠራው ነበር የምመርጠው። ምክንያቱም በሶማሊ ምድር ቤተክርስቲያን የመሰረተ ሰው ዶክተር ጥበቡ ነው። ለሶማሌዎች ወንጌልን የመሰከረ ዶክተር ጥበቡ ነው። ጀርባ ለሰጠነው ሁሉ ወደትክክለኛ መስመር የመራን፣ ዘመን እንዲጨመርልን የረዳን ዶክተር ጥበቡ ነው።"*

ሶማሌዎቹ ግን በሐዋይ ያዘጋጁትን ጨካኝ ዕቅዳቸውን በሥራ ለመግለጥ ጊዜ አላባከኑም። አሁንም የደናኑን ታሪክ በመድገም ሕዝቡ የገዛ ራሱን ወህኒ ቤት እንዲሰራ ወደ ግዳጅ ሥራ አሰማሩት። በእስረኛው ጉልበት ከአካባቢው ደን ለወህኒው ሥራ የሚያሰሯቸውን በየቡድኑ ለዩ። ጫካ ሄደው ለወህኒው የሚሆኑ እንጨቶች የሚቆርጡ፤ የተቆረጠውን ወደ ወህኒው የሚያመጡ። የመጣውን ደግሞ ለመታጎሪያቸው የሚሰሩ። ሳርና ሰንበሌጥ ሰብሳቢ፣ ተሸካሚና፣ ቆፋሪ ... ተመረጡ። ቤቱም ሆነ ወንዱ የመከራ ገፈቱን የሚካፈልበትን ዘግናኝ የመኖሪያ ስፍራ እንዲያዘጋጅ አስገደዱት። የሴቶችና የወንዶች ካምፕ ለየብቻ ሆኖ በአጥር ተለየ። የእስረኞቹን እንቅስቃሴ በውስጥም ሆነ በውጭ የሚቆጣጠር የጥበቃ ኃይል ተቋቋመ።

ለተቀሩት እስረኞች አሮጊቶች፣ ሽማግሌዎችና ልጆች ሁሉ እንኳ ሳይቀር የወህኒው መኮንኖች ያለርህራሄ ያዘጋጁት አስከፊ ዕቅድ ነበር። በየጠዋቱ እያሰለፉ በሩዝ እርሻው ላይ ለጉልበት ሥራ ማሰማራት። የሥራው ዓይነት ሁሉም አስጨናቂና በሰብዓዊ ፍጡር ላይ ይደረጋል ተብሎ ለማመን የሚያስቸግር ዓይነት ነበር። ትልልቆቹን ሴቶችና ወንዶች እስከወገብ በሚደርስ ረግረግ ውሃ ውስጥ የሩዝ እርሻው ላይ ቀኑን ሙሉ ያሰሯቸዋል። ልጆች ደግሞ በእርሻው ላይ የሰማይ አዕዋፍ እንዳያርፉ ሲያባርሩ ይውላሉ። የጠዋቱ ቁር የቀኑ ሐሩር ፀሐይ የሚፈራረቅበት ያ ሕዝብ ሲደከመው ማረፍ አይፈቀድለትም። ማለዳ የሚዘፈቁበት እንደበረዶ የሚቀዘቅዝ ረግረግ ውሃ በላዩ ስፍሮ ካደረው የወባ ትንኝ ሠራዊት ጋር እስረኞቹን ይረከባቸዋል። ረፋዱ ላይ እያገረረ ለሚመጣው ሙቀት ያቀብላቸዋል። ከፀሐዩ ግለት ለጥቂት ጊዜ እንኳ መጠለል እንዳይችሉ ደግነው የሚጠባበቋቸው ጨካኝ ወታደሮች ባይነ ቁራኛ ይከታተሏቸዋል። እንዲያውም "ለግመኸል " በሚል ሰበብ ሌሎችም አይተው መቀጣጫ እንዲሆኑ አንዳንዶችን እያወጡ የሚፈጽሙባቸውን የቅጣት አይነት ለመግለጽ ይሰቀጥጣል።

ጥበቡ የወገኖቹን እበሳ እያየ የልቡ ኀዘን ከፍ ያለ ቢሆንም እዚህም እንደ ደናኑ ወህኒ ቤት የብቻው መኖሪያ ተሰጥቶታል። ወገኖቹን በሚመለከት ግን የስፍራ ለውጥ ተደረገ እንጂ የመከራቸው መጠን አለመቀረፉን እያየ ያዝናል። ጥበቡ ሌላም የሚታየው ነገር አለ። መከራው ሳያንሰው ያን ሕዝብ በአጣዳፊ ሞት ሊረፈርፍ የሚችል እንደአስፈሪ ጥቁር ደመና ያቆረዘዘ ከባድ የጤና ችግር። በዚያ እስር ቤት ላይ የሚያንዣብበው የበሽታ አይነት እጅግ አሳስቦታል። ስለዚህም የሚከሰተውን

ችግር የሚቋቋምበት ቅድመ ዝግጅት ከወዲሁ ለማድረግ ቆርጦ ተነሳ። ሐዋይ እንደደረሰ የመጀመሪያ ሥራው ያደረገው የወህኒውን ክሊኒክ ማቋቋም ነው። አብሮት በትጋትና በሕብረት የሚሰራው የቀብሪደሃሩ ሆስፒታል ቡድን አሁንም እንዳለ ነው። ቡድኑ አንድ ጤና መኮንን ሦስት ነርሶች የላብ ቴክኒሽያንና የጤና ረዳቶች አሉት። ጤና መኮንኑ የተያዘው ከደገሀቡር ሲሆን ሶስቱ ነርሶችና የተቀሩት በሙሉ ከቀብሪደሃር ነበሩ። የጥበቡን ማንነት ከደናን እስከሐዋይ ፈትነው ዐይተውታል። ስለሕዝቡ የሚያደርገውን ተጋድሎ ሙሉ ለሙሉ የሚደግፉትና አይዞህ የሚሉት አጋሮቹ ነበሩ።

የሐዋይ እስርቤት የመጀመሪያው የዝናብ ወራት በዚያ መከረኛ ሕዝብ ላይ ሌላ መከራ ጨምሮበታል። በሳርና ሰንበሌጥ ከዳን የተሸፈነው የመታጎሪያው ጣሪያ ዶፉን በእስረኛው ላይ ይለቀው ጀመር። ቀን እንደዚያ ባለ የሥራ ድካም የዋለ ሕዝብ ሌሊት ጎኑን ለጥቂት ሰዓት እንኳ ማሳረፊያ አጣ! ወህኒው ያለበት ረባዳ ቦታ ላይ ስለነበረ ዝናቡ ባጠራቀመው ውሃ ደጁና አካባቢው በጭቃ ተዋጠ። የወህኒው ምግብ አቅራቢ ትላልቅ የጦር ሠራዊት የጭነት መኪናዎች ሐዋይ መድረስ አልቻሉም። ያደረጉት ሙከራ ወህኒው የነበረውን ደካማ የመገናኛ መንገድ ወደ ማጥ ጭቃ ለወጠው። በጥራቱ አጅግ ደካማ የነበረው ያም የተለመደው "ምግብ ተብዬው" እንኳ ለዚያ መከረኛ ሕዝብ መሰጠቱ ቀረ፤ የምግብ እጦቱ የንጽሕናና የጽዳት ጉድለቱ የወባ ትንኞቹ ... ሕዝቡን ለተላላፊ በሽታ ለተቅማጥና ለትውከት አሳልፎ ሰጠው። በተቀማጥ ምክንያት ራሱን ለመርዳት ወደ ውጭ ወጥቶ በጠመንጃ ሰለተረሸነው አንድ ሰው ጥበቡ እንዲህ ብሎ ነበር፡-

ሙሉ ሰው ነው ወደ አርባ ዓመት የሚሆነው። ስሙ በላይ ይባላል ። ተቅማጥ ይዞት በእርምጃው ጠደፍ ጠደፍ እያለ ወደጓሮ ይሄዳል። የወህኒው ዙሪያ ገና አልታጠረም፤ ሰዉም ለመጸዳዳጃ ስፍራ ስላልተዘጋጀለት የሚወጣው በየወህኒው ጓሮ ነበር። በላይ ቲቅማጥ አጣድፎታል። በዚያውም መጠን እግሮቹ ይጣደፋሉ ምቹ ስፍራ አግኝተው እስኪቆሙ። የወህኒው ወታደር ጥድፊያውን አየ። ጥላቻውንና በቀሉን ለመወጣት ምቹ ጊዜም አገኘ።

"ቁም! ቁም ነው የምልህ! ባትቆም ጭንቅላትህን ነው በጥይት የማፈርስልህ!"

በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በላይ ቆመ።

"ልታመልጥ ነበር አይደል ሃሳብህ? ተይዘሃል! ከእጄ ማነው የሚያስጥልህ?"

"ኧረ ፈጽሞ አይደለም! ሆዴ ታሞ ለመጸዳዳት ወጥቼ ነው!"

ወታደሩ ኦጋዴን የነበረ ሶማሌ ነው፤ ለእርሱ ጥሩ የበቀል መወጫ እድል ነው። እያዳፋና እያጣደፈ ወደአለቃው መኮንን ይዞት ገባ። መኮንኑም ጥሩ አጋጣሚ የሚጠባበቅ ይመስል ነበር።

"ምንድነው ችግሩ?"

ሊያመልጥ ወደጫካው ሲሮጥ ነው የያዝኩት"

"ኧረ እኔ ሆዴን አሞኝ ውጪ ለመጸዳዳት ...."

በላይ አልቻለም የሆዱን ህመም ከዚያ ወዲያ ለመያዝ። በእግሮቹ ላይ መውረድ ጀምሯል። ወታደሩ የበላይን ንግግር ሊያስጨርሰው አልፈለገም ዝም በል ብሎ እየተሳደበ በጥፊ ሲመታው። መኮንኑ የወታደሩን ጠብመንጃ ተቀበለ። "ግድየለም ከዚህ በኋላ የማምለጥ ችግር አይገጥምህም!" በላይ በእርግጥ ሆዱን የታመመ ሰው መሆኑ በግልጽ እየታየ ያለ አንዳች ርህራሄ በያዘው ጠብመንጃ ተኩሶ ገደለው። የእውነት ያለህ! የፍርድ ያለህ!

****

*የሩዛ እርሻ!*

ይህን ከመሳሰለው የግፍ ግድያ በተጨማሪ ጥበቡን ሲያስጋው የቆየው ህመም በያይነቱ መከሰት ጀመረ። ወባ፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ ተቅማጥ፣ ተስቦ… ሌላ ሌላም ተላላፊ በሽታ የሚገድላቸው እስረኞች ቁጥር ከቀን ወደቀን እየጨመረ መጣ። በዶፍ ዝናብ የጨቀየውን መሬት እየቆፈረ የገዛ ወገኑን እሬሳ እስረኛው ከብዙ ልብ ስብራትና ኀዘን ጋር ቀበረ። ሊድኑ የሚችሉትን ወገኖቹን ከመድኃኒት እጥረት የተነሳ፣ ሞት ሲነጥቅበት የጥበቡ ኀዘን ደግሞ እጥፍ ድርብ ሆነ። የኔ ውድ! እስካሁን አምላኩ በአሳሪዎቹ ፊት ስለሰጠው ሞገስ ለዚህ ምስኪን ሕዝብም ሐኪም ብቻ ሳይሆን ጠበቃና ተመልካችም እንደሆነ ያውቃል።

"አምላኬ ሆይ! እባክህ አንድ ጊዜ ደግሞ በላዬ ሞገስህ ይብዛልኝ! ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ከዚህም የሞት ጥላ የምንወጣበትን መንገድህን አሳየኝ! እስከዛሬ የረዳቺኝ መልካሚቱ እጅህ በላዬ ላይ ትገለጥ!" ነበር ጸሎቱ።

የሕመምተኛውና የመድሃኒቱ መጠን አልተመጣጠኑም። ጥበቡና የሥራ ጓደኞቹ ቀኑን ሙሉ መድኃኒት ሲያድሉ የሚውሉበት ጊዜ ተደጋገመ። የወባና የሌላ ሌላም ማስታገሻ መድኃኒት ያዳረሱትን ያህል ይሰጣሉ። ጥበቡ ግን ከመድኃኒት እደላው ይልቅ የታየው የተሻለ መንገድ አለ። ወደ ወህኒው ዳይሬክተር ወደ ኮሎኔል አህመድ ሁሴን በቀጥታ ሄደ።

"የሰዎች ሞት ቁጥር በየቀኑ እየጨመረ ነው። አስቸኳይ መፍትሄ ካልተፈለገ በዚህ ጉዳይ ኃላፊነት መውሰድ እየከበደኝ ነው።"

"እስከዚህ ድረስ ችግር አለ እንዴ?"

"እስካሁን ድረስ አርባ ሰዎች ሞተውብናል። በዚህ መጠን ሰው የሚሞት ከሆነ በሩዝ እርሻችሁ ላይ የሚሰራላችሁ ሠራተኛም አታገኙም"።

ኮሎኔሉ አሁን ገና ለጥበቡ ጆሮ ሰጠው። የሩዝ እርሻው ሥራማ መጓደል የለበትም! የሶማሌ መንግሥት ከዓለም ዕይታ ሰውሮና መብቱን ገፎ ከባድ የጉልበት ሥራ የሚያሰራውን ሕዝብ በሕይወት ማኖር አለበት። በነፃ ጉልበቱን በግፍ የሚገፈውን ያን ሕዝብማ በሕይወት ማኖር የግድ ነው!

"ያን ያህል ሰው በእርግጥ ሞቷል ነው የምትለኝ?"

"ከስፈለገ የስም ዝርዝራቸውን አቀርብልሃለሁ ለሞት የተቃረቡም ደግሞ አሉ!"

አህመድ ሁሴን ደነገጠ። እንዲህማ ከቀጠለ ጉድ ሊፈላ ነው።

"ምንይሻላል ትላለህ ዶክተር?"

"ሕዝቡ ለበሽታ ከመጋለጡ በፊት መከላከል ይቻላል።"

"መከላከል? እንዴት ይቻላል?"

"አካባቢውን በማጽዳትና የሕዝቡን ንጽህና በመጠበቅ ልብሶቻቸውን በበርሜል በመቀቀል መከላከል ይቻላል። በተቅማጥ ለሚተላለፈው በሽታ ከዳን ያላቸው መጸዳጃዎች ይሰሩ። የምግብ ማብሰያውም ስፍራ አንድ የተላላፊ በሽታ ጎሬ ስለሆነ፣ ጽዳቱ የተጠበቀ ሊሆን ይገባል። እነዚህ ባስቸኳይ በተግባር ካልዋሉ በዚሁ ወህኒ ቤት ሞት እያንዣበበ ነው፤ የሚጠብቀንም አስከፊ ነገር ነው። አሁንም ህመሙ ለተከሰተባቸው ሰዎች አስፈላጊዎቹ ማስታገሻ መድሃኒቶች ባስቸኳይ ካልደረሱልን እልቂቱ ይቀጥላል።"

አህመድ ሁሴን ከጥበቡ በሚፈልቀው ሃሳብ እየተደነቀ ለዚህ ከባድ ችግር መፍትሄ ሊገኝ መቻሉንም ከዚሀ አስገራሚ ሰው በመስማቱ ከድንጋጤው መለስ ብሏል።

"እሺ ዶክተር ሥራው በአፋጣኝ ይጀመራል። ያልካቸውንም የመድኃኒት ዝርዝሮች

ብታቀርብልኝ ባበቸኳይ እንዲደርስህ አደርጋለሁ።

ኮሎኔል ሁሴን በጥበቡ የቀረበለትን ሃሳብ ተግባራዊ አድርጎታል። በሐዋይ ካምፕ ውስጥ መጠነኛ መሻሻልም አስከትሏል። ለዚህም ጥበቡ እንደልማዱ አምላኩን ተንበርክኮ አመስግኖታል፣ በዚህም ሰው ፊት ስለሰጠው ሞገስ። በወገኖቹና ምሕረት በማያውቁት አሳሪዎቻቸው ጥበቡን እንደ መካከለኛ ሰው አድርጎ ያስቀመጠውንም የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ሃሳብ በሚገባ ተረድቶታል።

"እግዚአብሔር ሆይ ለዚህ ሕዝብ ያለኝን ተልዕኮ በታማኝነት እንድወጣው አሁንም ጸጋህ ይርዳኝ!" የመጨረሻ ጸሎቱ ነበር በዚያን ምሽት።

የጥበቡ የሕክምና ሞያ ተገልጋዮች በሐዋይ ወህኒ ቤት ያሉት ወገኖቹ ብቻ አልነበሩም። የአካባቢው ኑዋሪ ሶማሌዎችም በእርሱ እንዲታከሙ ወታደሮቹ ይዘውት ይወጣሉ። ጥበቡ ከሰይጣን ሌላ ጠላት የለውም። ሶማሌዎቹም ቢሆኑ ጥበቡ እንደጠላቶቹ እንደማያያቸው አውቀውታል። አንዳንድ የሶማሌ ወታደሮች ግን ጥበቡን በቁጥጥራቸው ስር ያዋሉት አንድ ተራ ምርኮኛ እንደሆነ ሊያሳውቁት ቃጥተዋል። በጉልበታቸውም ተመክተው ጥበቡ ሊያደርግ ሕሊናው በማይፈቅድለት በአንዳንድ ሁኔታዎች ሞክረውታል። "አሞኛልና የፈቃድ ወረቀት እንድትጽፍልኝ እፈልጋለሁ" ለሚለው ወታደር ሁሉ ጥበቡ እስረኛ ስለሆነ፣ ወዲያውኑ ሥራ ከመግባት ነጻ የሚያደርጋቸው የሐኪም ወረቀት እንዲጽፍላቸው ይጠብቃሉ። ጥበቡ በሚያደርግለት ምርመራ ወታደሩ በጥሩ ጤንነት ያለ ከሆነ፣ የሚቀበለው ምላሽ አጭርና ግልጽ ነው፡- "ሙሉ ጤነኛ ስለሆንክ የፈቃድ ወረቀት ልጽፍልህ አልችልም"

ሌላው አይነት ፈተና ደግሞ ያለ የሌለ የመድኃኒት ዝርዝር ጽፈው ያመጣሉ። "በተጠቀሰው መሠረት መረከብህን ፈርመህ ተቀበለን" ይሉታል። እነርሱው ባሉበት ካርቶኑ ተከፍቶ ሲታይ ግን ከዚያ ዝርዝር ከግማሽ በላይ በቁጥርም ሆነ በአይነት ጎዶሎ ሆኖ ጥበቡ ስለሚያገኘው መልሱ፥

"የተቀበልኩትን ትክክለኛ የመድኃኒት አይነትና ቁጥር እንጂ ባልተረከብኩት ነገር ልታስፈርሙኝ አትችሉም"

አንዳንድ ወታደሮች የጥበቡ ሕይወት በእነርሱ እጅ እንደሆነች ያስባሉ። የአንዳንዶቹም ዛቻና ቁጣ "ቆይ ብቻ ሌሊት እንገናኛለን!" አይነት ይመስል ነበር። ጥበቡ ኃይለሥላሴ ግን ሕይወቱ በአምላኩ እጅ እንደሆነች የሚያምን ስለሆነ፤ ለእንዲህ አይነቱ ዛቻ እንደማይንበረከክ ደናንም ሆነ ሐዋይ ታውቋል። በእርግጥም ሕይወቱ በእግዚአብሔር እጅ ስላለች እንጂ በምሽትና በውድቅት "በሽተኛ እይልን" እያሉ ከካምፑ ውጪ የሚወስዱት ወታደሮችም ነበሩኮ! "ሊያመልጥ ሲሮጥ ገደልኩት" በሚል ሰበብ ቁጥሩ ጥቂት ያይደለ ወገን እንደ ምንዳዬና እንደ በላይ ቀርቶ የለ?

****

*ዋቢሸበሌ!*

ጥበቡ ከእውነት ውጪ፣ ሌላ ሕይወት እንደሌለው ሶማሌዎቹ እየገባቸው መጥተዋል። በአንፃሩ ደግሞ በገዛ አለቆቻቸውና መኮንኖቻቸው ዘንድ ኢትዮጵያዊው ምርኮኛ ሐኪም ተደማጭነቱ ከፍተኛ መሆኑን አይተዋል። ከመኮንኖቹ ጋር አብሮ እንዲበላ፣ ሻይ እንዲጠጣ፣ ይጋብዙታል። አለቆቻቸው ከሞቀዲሾ ካምፑን ለመጎብኘት ሲመጡም አብሯቸው እንዲቀመጥ ይጠሩታል። ከመኮንኖቻቸው ይልቅ ከእሱ መስማት ይፈልጋሉ። በተለይ የሁሉም የበላይ አዛዥ ጄኔራል እስማኤል። "ምን ችግር አለ እንድሰማው የምትፈልገው? የመድኃኒት? የምግብ?" ... ይሉታል። ብቻ የሆነ ሞገስና ተወዳጅነት በጠላቶቹ ፊት ማግኘቱ እየጎላ መጥቷል።

የሐዋይ ካምፕ ሥራ አሁንም አልቆ አላለቀም። የእስረኞች ወገኖቻችን ጉልበት ለዛፍ ቆረጣውና ሸከማው መበዝበዙ ቀጥሏል። እስረኞቹ ባቆሟቸው ግድግዳዎች ላይ እንጨትና ማገር ለመጨመር ነው ሰበቡ። ኋላ ግን ወታደሮቹ በወገኖቻችን ላብ የሚቆረጠውን ደን በአካባቢው ለሚገኙት ፈረዎች ሁሉ መቸብቸብ ጀመሩ። በነጻ ጉልበትና በግፍ የተገኘ ገቢ አይደል? እነሱን ምን ቸገራቸው። የጉልበት ሥራ ብዝበዛው በቂ ምግብ ባገኝ እንኳን በሆነ ደግ ነበር። በመቱ በገፋ ቁጥር ለእስረኞች ወገኖቻችን የሚታደለው ምግብ ከቀን ወደቀን እየተመናመነ ከሄደ ወራት ሆኖታል። ሕጻን ሽማግሌው ሴቱ ወንዱ ያለበቂ ምግብ ለተለያየ የበሽታ አይነት ተጋለጠ።

ሞት ጨካኝ ማጨጃውን ይዞ መግባት ሲጀምር ጥበቡ ተጨነቀ። በአምላኩ ፊት ተንበርክኮ መላና ምሪት ፍለጋ ጸለየ። ከጸሎቱ በኋላ እግሮቹ ሲጣደፉ ያገኘው ወደካምፑ ዳይሬክተር ወደ ኮሎኔል አህመድ ሁሴን ቢሮ ነው!

"ሕዝቡ በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ ነው። አሁንም አስቸኳይ እርምጃ ካልተገኘ በሩዝ እርሻህ ላይ የምታሰማራው ሰው አይተርፍህም!"

አህመድ መስማት አማይፈልገው ነገር ቢኖር የእስረኞቹን እልቂት ነው። ለእነርሱ አዝኖ ሳይሆን፣ በሕይወት ኖረው የግፍ ጉልበት ሥራ እንዲሰሩ። እናም ደነገጠ። ምን መላ አለውና አይደነግጥ? ይህን ከመሰል ድንጋጤ ባለፈው የጥበቡ ጥበብ ጥቂት አስጉዞት ነበር።

"ጥሩ ዜና አይደለም የምትነግረኝ ዶክተር። ምን ማድረግ ይሻላል? የምግብ እጥረቱ አሁን በመላው ሶማሊያም ጭምር ነው። አቤት ብልም የሚሰማኝ አላገኝም . ."

ድንገትም ከጥበበኛው ጥበቡ እንደበት የመከንኑን ጭንቀት የሚያስወግድ መፍትሄ ተገለጠ!

"የዋቢሸበሌ ወንዝ! ወንዙእኮ የሚያመጣቸውን አሳዎች አጥምደን ለሕዝቡ ማቅረብ እንችላለን። ዓሳ ደግሞ_በምግብነቱ በራሱ ብቻ የተሟላ ነው።"

የኮሎኔል ሁሴን ዐይኖች በመገረም የሚያዩት ምርኮኛው ጥበቡ ንግግሩን ቀጠለ።

"ከእስረኞቹ መካከል ከሩዝ እርሻው ሥራ ተቀንሰው አሳ ለማጥመድ ወደወንዙ ይውረዱ። ዐሳ ማጥመጃ መረብ ይሰጣቸው። እስረኛው አሳ ከተመገበ ብዙ የበሽታ አይነት ለመቋቋም አቅም እንደሚኖረው ላረጋግጥልህ እችላለሁ"።

ከዋቢሸበሌ የተገኘው የዓሳ ምርት እስረኛውን ሕዝብ በእረገጥም ረድቶታል። ከብዙ ጉዳት በኋላ ቢሆንም እንኳ ከባሰና አስከፊ ከሆነ እልቂት ጥበቡ ከወገኖቹ ጋር ተርፏል። ለዐሳ አጥማጅ ሥራ የተለዩት እስረኞችም የሩዝ እርሻው ከባድ የጉልበት ሥራ ቀርቶላቸዋል። የዋቢሸበሌ ዓሳዎች ለሕዝባችን ጤንነት እጅግ ጠቅመውታል። የቀደመ ጉዳት ያደቀቀው ሕዝብ ሆኖ ነው እንጂ!

ይህም ሁሉ ሆኖ የሳምባ ነቀርሳው የወባውና ተቅማጡ ኃይል በሕዝባችን ላይ እያየለ መጥቷል።

ዝንቦችና ልጆች አብረው ይውላሉ። ረግረጉና ጨፌያማው አካባቢ፣ ሕዝቡ የሚጠጣው ያልተጣራ ውሃ፣ ሁሉም የበሽታ ፋብሪካ ሆኗል። አንድ ቀን ግን እስካሁን በካምፑ ውስጥ ከተገለጡት የበሽታ ዓይነቶች ሁሉ የሚከፋውና እጅግ የሚፈራው ኮሌራ ከእነሞት አጀቡ ከተፍ አለ!

ጥበቡ! የኔ ውድ ጥበቡ! ገና የመጀመሪያውን ሕመምተኛ ሲያይ ማረጋገጫ ላቦራቶሪ አላስፈለገውም! ምንም እንኳ ተቅማጥና ትውከት በሐዋይ ካምፕ የተለመደ ቢሆን! ከጥበቡ ዐይን ኮሌራ ሊሸሸግ አስመስሎ ገብቶ ሕዝቡን በሞት ሊጠራርግ አልቻለም! ኮሎኔል ሁሴን አስቸኳይ የሕክምና እርዳታ ከሞቃዲሾ እንዲያስመጣ ጥበቡ አስታወቀው! ኮሎኔሉ አፍታም ሳይቆይ ስልክ ወደሞቃዲሾ! "ኮሌራ ጊቢዬ ገብቷል አስቸኳይ እርዳታ! ፍጠኑ!"

ጥበቡ የራሱን አስቸኳይ እርምጃ ወሰደ! በሐዋይ ካምፕ ውስጥ ሌላ ራሱን የቻለ ካምፕ

ለይቶ ኮሌራ የያዛቸውንና ምልክቱ የታየባቸውን ሁሉ ወደዚያ አዛወራቸው! ለወንዱ አንድ ለሴቱ አንድ! ኮሌራ ግዙን ጠቅልሎ ከዚያ ጊቢ ተሸንፎ ወጣ! ድሉም የጥበቡና ሌትና ቀን አብረውት ታግለው ኮሌራን ያሸነፉት የሕክምና ቡድኑ ሆነ! ኋላ ላይ፣ የኮሌራ ካምፕ የነበረውን ወደ ቲቢ በሽተኞች ሆስፒታል ቀይሮታል።

ሲስተር በላይነሽ ከቀብሪደሃሩ ነርሶች መኻል አንዷ ነች። ስለኮሌራውም ሆነ ስለጥበቡ የምትናገረው አላት።

*"መቶና መቶ ሠላሳ ሰው ባንድ ክፍል ተኝቶ ከኮሌራ ማን ሊተርፍ ይችል ነበር? ዶክተር ጥበቡ ባደረገው አስደናቂ ጥረት ነው ለመትረፍ የተቻለው። ዶክተር ከተማረው በላይ እግዚአብሔር ጥበብን የሰጠው ሰው ነው"*

*ሲስተር በላይነሽ ስለእኔ ውድ በተጨማሪ ስትናገር፥-*

*"ዶክተር ጥበቡ ለሕዝብ የተፈጠረ ሰው ነው። የደሙ አይነት እንኳ ለሰው ሁሉ የሚሆን ስለሆነ ቀብሪደሃር በነበርንበት ጊዜ ደም ለሚያስፈልጋቸው ሕመምተኞች በየወሩ ይለግስ ነበር። ከዚያ ቀውጢ ቀን በኋላ ሶማሌዎች በወሰዱን በ15 ቀናችን ነው እንደገና ከዶክተር ጋር ለመገናኘት የቻልነው። እናም እንዲህ አልኩት።*

*"አሁን ምንድነው መጨረሻችን ዶ/ር?"*

*"አይዞሽ! ለአምስት ዓመት ፕላን አውጪ።"*

*"እንዴ ዶ/ር! አምስት ዓመት እዚህ? በእንዲህ ያለ ሁኔታ?"*

*"አይዞሽ! ምንም አይደለም በላይነሽ! ቀደም ብለን ብንሄድ ጥሩ ይሆንልናል። ብንዘገይ ደግሞ ልብሽን ሰፋ እንድታደርጊ፣ አእምሮሽን እንድታዘጋጂ ይረዳሻል እንጂ አምስት ዓመት እዚህ እንቆያለን ማለት አይደለም። እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባናል እዚህ በመሆናችን!"*

*"እግዚአብሔርን ማመስገን? እንዴት? ስለምን ዶክተር?"*

*"እኛ እዚህ ባንሆን ኖሮ እኛ ባንንከባከበው ኖሮ፣ ይህ ሕዝብ ምን ሊደርስበት እንደሚችል አስበሠው እስቲ! ምንም ባናደርግለት እንኳ አይዟችሁ ማለት ትልቅ ነገር ነው። እግዚአብሔር እዚህ ሲያመጣን ትልቅ ዓላማ አለው"*

*አከላም እንዲህ ትላለች ሲስተር በላይነሽ*

*"እኔ ከነርስ ትምህርት ቤት ገና እንደተመረቅሁ ቀብሪደሃር ተመድቤ ሥራ በጀመርኩ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ነው የተማረክሁት። እና አይዞሽ እያለ እያበረታታኝ ያን ሕዝብ በምችለው ሁሉ ለመርዳት እኔም እንድፍጨረጨር ረድቶኛል። ሰው በብዛት ይታመማል። የምንሰጠው መድኃኒት ግን የለንም። ሊድን የሚችለውን ሰው በመድኃኒት እጥረት ምክንያት ሲሰቃይ ሲብስም ሲሞት ማየት ልብ ይሰብራል፣ ያስለቅሳል። አንዳንዴ በእኔ ደረጃ ዝም ብዬ ማየት ብቻ ይሆናል። በየክፍሉ በንገባ ሰዉ ያቃስታል እዚያም ለቅሶ እዚያም ስቃይ ነው። ሕፃናት ቢኃይለኛ ትኩሳት ተቀማጥና ትውከት ተይዘው ይሞታሉ። በዚህ ላይ ረሃብና ሌላ ሌላም ብዙ ችግር አለ። ጭንቅ ሲለኝ ለወታደሮች ነግሬ ዶክተርን ማስጠራት ብቻ ነው። እሱ ሲመጣ መድኃኒት በእጃችን ባይኖርም ሕመምተኞቹን የሚላቸው ይደንቀኛል።"አይዞአችሁ! ይሻላችኋል። ነገ መድኃኒት እንፈልግላችኋለን" እያለ ይደባብሳቸዋል። እሱ ደግሞ የወሀኒዉን አዛዦች ተለማምጦና አባምኖ ሲብስም ተሟግቶ መድሃኒቶችን ያመጣልን ነበር። ለዚያ ሁሉ ሕዝብ በሕይወት መኖር እግዚአብሔር የተጠቀመበት ዶክተርን ነው እላለሁ።"*

# 13

## ቁስሌን ነካኩብኝ!

አይ የኔ ነገር! የውዴ የጥበቡ ነገር ሲነሳ ማቆሚያም የለኝ! እግዚአብሔር በእርሱ ስላደረገው ነገር እያወራሁላችሁ የኔንና የልጆቻችንን ታሪክ እረሳሁት! ብርሃን መጽሔት ውስጥ ስሰራ ነው የተውኳችሁ! የእግዚአብሔር ሥራ በዝቶልኛል! እንዳቅሚቲ በመጽሔቱ፣ በቤት ለቤት አገልግሎቱና በጸሎት ሕብረቱ፣ በድቁናው... ብቻ ምንም ዕረፍት የለም! ወድጄው በፍቅር አምላኬን አገለግለዋለሁ! ልጆቼም በወላጆቼ እንክብካቤ በጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት በመኮትኮት ላይ ናቸው። በ1972 ዓ.ም. እምነትና ረቂቅ ሦስትና አራት ዓመታቸው ላይ ሕጻናት መዋያ ገብተዋል። ናዝሬት በሚገኘው ቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት። የአባቴ መኖር ለልጆቼ የሚመች ትከሻና ፍቅር ስለሰጣቸው ብዙ ልቤን አሳርፎታል።

በዚህ መሀል ግን የጥበቡ ከእኛ ጋር አለመሆን፣ ብዙ ሆደ ባሻ ቢያደርገኝና ዕንባዬም በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ያለገደብ ቢወርድ፣ እንዲህ ያለው ዕንባ በአድራሻው በአምላኬ ፊት ስለሚፈስ፣ ተጽናንቼ ተጠግኜም እነሳለሁ። ከገጠሙኝ አንዳንድ ሆድ የሚያስብሱ ሁኔታዎች ለመውጣት ግን ጊዜ እንደወሰደብኝ አልደብቃችሁም።

የጥበቡ እናት እማማ ፀዳለን እወዳቸዋለሁ፤ መልካምና ቅን ሴት ናቸው። የሚወዱት ልጃቸው በሶማሌ መወሰዱን ከሰሙ ጊዜ አንስቶ በተገናኘን ቁጥር ያለቅሳሉ፤ እምነትና ረቂቅን እንዲያዩአቸው ስወስድላቸው፣ እነርሱንም ሲያዩ ያለቅሳሉ፣ እና እኔም አብሬያቸው አለቅሳለሁ። በዚህ መሀልም እያመማቸውና ሕመሙ እየጠናባቸው መጣ፣ በሕመም አልጋቸውም ላይ ሆነው ላያቸው በሄድኩ ጊዜ ሁሉ ያለቅሳሉ አብረን እናለቅሳለን። ስሜታቸው ሀዘናቸው ስብራታቸው እየገባኝ እየተረዳኋቸው፣ ሀዘናቸው ሀዘኔ ስለሆነ ስብራታቸውም ስብራቴ ስለሆነ አብሬያቸው አለቅሳለሁ። ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ግን ሀዘኔ ከፍ ያለ ነበረ። ሳያዩት እንደናፈቁት በሞት በመለየታቸው፣ መጽናናት እስኪያቅተው ልቤ ክፉኛ በኀዘን ተመታ። ከዚያም ቀጥሎ ታላቅ ወንድሙ አቶ ግሩም ኃይለሥላሴ መሞቱ ተሰማ። ግሩምን አንዲት ቀን ብቻ ለጥቂት ደቂቃዎች ከጥበቡ ጋር አግኝተነው አስተዋውቆኛል። ከዚያ በኋላ አልተገናኘንም። ለቅሶዬ ግን ብዙ ዓመት እንደሚያውቀውና እንደቀረብኩት ያህል የመረረ ሆነብኝ። በውስጤ የተቀበረውን ከውዴ ከጥበቡ የመለየት ቁስሌን እየነካኩብኝ አልቃሻና ሆድ የባሳት ሴት አድርገውኛል።

ከእነዚህ ሁሉ በኋላ ደግሞ፣ መስከረም 23/1973 ዓ.ም. ከባዱና ከፍተኛው ሀዘኔ እጅግ የምወደውና የማከብረው አባቴ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለየን ነበር። በጥበቡ አለመኖር ምክንያት የገጠመኝ ኀዘን መጽናኛዬና "አይዞሽ" ባዬ፣ የእግዚአብሔርም ነገር የገባው አባቴ ነው። በምክር ቢሆን በሃሳብ፣ ብዙ የደገፈኝ ደግና ቸር ሰው። የጥበቡንም ዳግም ከቤተሰቡ መቀላቀል በጉጉት የሚጠባበቅ ሰው። የባለደራነቱ ሽልማት ጥበቡን በዐይኑ ማየት እንዲሆንለት የሚሻው አባቴ፣ ባልጠበቅነው ሰዓት ከእኛ በሞት ተለየ። እንኳን እውን ሆኖ፣ ድሮ ያኔ በደህናው አገር ገና ለገና አባቴ ቢሞትስ ብዬ በማሰብ ብቻ፣ እንባዬ የሚፈስበትም ጊዜ እንደነበረ አስታውሳለሁ። የእሱ ሞት በቁስሌ ሁሉ ላይ፣ ከፉኛ ጥዝጣዜ ጨመረብኝ። ልጆቼ እምነትና ረቂቅስ? ከዛሬ ነገ ይመጣል እያሉ የሚጠባበቁት አባታቸው ገና ሳይመጣ፣ የአባዬን ከቤቱ መታጣት እንዴት ይችሉታል ብዬ ስለእነሱም አለቀስኩ። ከዋልኩ ካደርኩባቸው ወደመራራ ኀዘን እንደሚከቱኝ ስለማውቅ ውስጤን እንዳይዙብኝ ከራሴ ጋር የታገልኩባቸው ነበሩ። ሰይጣን ግን በቁስሌ ላይ እንጨት ሊሰድበት በዚህ በከባድ የሀዘኔ ዕለት እንኳ ያልርህራሄ በላዬ ተነሳ።

ለአባቴ ሕይወት እልፈት ምክንያት የሆነው ወትሮ ያለበትና የሐኪም ክትትል ያደርግ የነበረበት የደምብዛትና የልብ ችግር አይደለም። ድንገተኛ የአንጀት መቆለለፍ ገጥሞት ጳውሎስ ሆስፒታል ቀዶ ጥገና ተደርጎለት ነው። በጊዜው የእህቴ የሲስተር አየለችና የእኔም የቅርብ ነርስ ጓደኞች ብዙ ስላሉን ባስቸኳይ ነው ሆስፒታል ያስገባነው። ጓደኞቻችን የአባቴ ጨዋታው ቀልዱ፣ ለሰዎች ያለው ፍቅሩና ግልጽነቱ ስለሚመቻቸው ሁሉም ይቀርቡታል። ከቅርበታቸው የተነሳ አባቴን "አጉኔ" እናቴን "አልሚ" እያሉ ይጠሯቸዋል። አባቴ ግን ዛሬ በጽኑ ተይዟል።
ከአባቴ ጋር በተለይ የመጨረሻው ዓመት መሆኑ እኔ አልገባኝም እንጂ በቂና ሰፊ የብቻችን ጊዜ እግዚአብሔር ሰጥቶኛል። በተለያየ ምክንያት ከናዝሬት አዲስ አበባ ሲመጣ አንዴም ደግሞ ሆስፒታል በልቡ ምክንያት ገብቶ በእግዚአብሔር ስላለው ሕይወትና ስለጥበቡም ተወያይተናል። እንደሚዋደዱ አባትና ልጅ የሰከነ ጊዜ አምላኬ በተደጋጋሚ ሰጥቶናል። አባቴ በእግዚአብሔር ያረፈ መሆኑን አውቃለሁ። ሀዘኔ ግን ገና ጥቂት ያጓጉዘኛል፣ ይሸፍነኛል ብዬ ያሰብኩት አባቴ፣ ለምን ቶሎ ጥሎኝ ሄደ፣ ብዬ ስለራሴና ስለሚወዱት ስለእነዚያ ህጻናት ልጆቼ ነበር።
የአባቴን አስከሬን ይዘን ወደናዝሬት ሄድን። ዘመድ አዝማዱ ተሰብስቦ ሲለቀስ ዋለ ቀብሩ በማግስቱ ሊሆን። ብዙዎች ተኝተዋል። ሌሊት ላይ የአባቴ አስከሬን ወዳረፈበት ክፍል ላየው ብሄድ አጣሁት! እናቴ አልተኛችም ፈጠን ፈጠን ብላ በድንጋጤ ወዳለሁበት ክፍል ገባችና በሩን መለስ አደረገችው። ምን ሊሆን ይችላል ብዬ በይኖቼ ፈጠ ሳለ፦ "አይዞሽ! አይዞሽ!" ሰዎቹ እርኩስ ቤት ገብተን አንቀድስም ብለው አስከሬኑን በመስኮት አውጥተው ወስደውታል።"
ገባኝ!

"ማን ቀድሱልን አላቸው ታዲያ"

"አይ እኛ ነፍሱ ወዳምላኳ በሄደ ሰው አስከሬን ላይ አንከራከርም። የአባትሽ ነፍስ ወደ እግዚአብሔር እቅፍ እንደሄደች እናውቃለን"

ገረመኝ!

"ጠላቴ ያገኘኝ መስሎት ነው! ዋናው ነገር አባቴንም አላገኘው። እሱ ነገሩን ከምላኩ ጋር ጨርሶ ከምድር የተሰናበተ ሰው ነው! አይዞሽ አንቺ እማዬ!"

አባቴ ከአሥር ዓመት በፊት ቤቱን ካስጨነቀው የአንደርቢ አስማት፣ ከእነዚያ አራት የስቃይና የማይረሱ ቀናት በድንቅ ያወጣውን፣ የጌታን የስሙን ታላቅነት አይቷል። በቤታችን ላይ ሰይጣን

የከፈተውን ጦርነት ላንዴና ለመጨረሻ የከብሩ መታሰቢያ ያደረገውን የጌታ የእግዚአብሔርን ታዳጊነት የመሰከረ ሰው ነው።

****

## የቀብር ቦታው ተአምር!

እስከሬኑን ወስደው ለዘመዶቻችንና ለነበሩት ሰዎች ትምህርትና መቀጣጫ አይነት ነገር አድርገው ሊጠቀሙበት እንደሞከሩ ሰማሁ፣ አዘንኩ። ጠዋት ላይ መልሰውልን የምንወደው ልጆቹ፣ ዘመድ አዘማድና ጓደኞቹ አባቴን ለመሰናበት ወደ መቃብሩ ቦታ ይዘነው ሄድን። ከአባቴ ቀብር በኋላ ከአዲስ አበባ ከናዝሬትና ከየዳርአገሩ የተሰበሰበውን ሕዝብ "ለማሰናበት" የተደረገው ንግግር፡-

"እኒህ አዛውንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ሃይማኖታቸውን ጠብቀው በክብር የሄዱ ሲሆኑ፣ በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ግን ተገንጣይ ሃይማኖት ተከታዮች አሉ። ሃይማኖት እንደሸሚዝ ከመቀያየር ያድናችሁ። እናንተም ባሎች ሚስቶቻችሁና ልጆቻችሁ ሃይማኖታቸውን እንዲጠብቁ ተቆጣጠሩ...."

ሰይጣን በሀዘኔ ላይ ኀዘን ሊጨምርብኝ፣ በዚህ ጊዜ እንኳ ላይተወን ምን ያህል ጨካኝና ርህራሄ የሌለው እንደሆነ አየሁ። እናቴንም ትከሻዋን ያዝ አደረግሁና "አይዞሽ የኔ እናት! ይህ በክርስቶስ ስላለው እምነታችን የምንሸከመው መስቀላችን ነው።" የእናቴ መልስ የኀዘኔን ጥላ ገፈፈው፤ "ልጄ! ለኔማ ይሄ ክብሬ ነው! ነፍሴን ከዘላለም ስቃይ ላተረፋት ሌላም ካለ በሆንኩለት!"

አውቃለሁ እናቴ የጌታ ነገር የገባት ሴት እንደሆነች አሁንማ አሥር ዓመት እኮ አልፏታል! ያኔ እንኳ ገና ጌታን እንደተቀበሉ በዐመታቸው የነበረው የስደት ወላፈን ከእኛ ቤት አራት እራሷን ሆና ፖሊስ ጣቢያ ከቷት ነበረ። እስላ ውስጥ በአጋንንቱ ዓለም ይታወቅ የነበረው ታናሽ ወንድሟ ጋሽ ኃይሉ እንግዳወርቅና ባለቤቱ እንዲሁም የሰባ አምስት ዓመት ዕድሜ የነበራቸው ወላጆቼ የሚጠሯቸው መበለት እማማ ጌጤ! እነዚህ አብረዋት በታሰሩ ጊዜ ፖሊሶቹ፡-

"አሁን እናንተ በመመንከሻችሁ ጊዜ እንዴት በእዚህ ዕድሜያችሁ ልጆች በከረሜላ ያታልሏችኋል?" ለሚለው የፖሊስ ጥያቄ፤ የአጎቴ መልስ፡-

"ምነው ያኔ ድቤ እየመታሁና እያስመታሁ የአልኮል የሲጃራና የጫት ሱሰኛ ሆኜ አገር ምድሩን ሳስት ጥፋተኛ ብላችሁ አላሰራችሁኝ? አሁን እኔ የሰላም ሰው በመሆኔስ ጥፋቴ እምኑ ላይ ነው?" ሲሆን፡-

የእማማ ጌጤ መልስ ደግሞ፡-

"እሱ ባለቤቱ "ራስሽ ላይ ለምን ያን ጨርቅ አልለጠፍሽም" ሲል ከበሩ ይመልሰኝ! እኔ ግን እውነትና ሕይወት መንገድም የሆነውን ክርስቶስ ኢየሱስን በማግኘቴ ጥፋተኛ አይደለሁም። ሌላውን ትርፍ ንግግር ትተህ የምትጥፈውን ጣፍ! (የምትጽፈውን ጻፍ)"

እያሉ እናቴና አብረዋት የነበሩት ቤተሰቦቼ የማያሻማ መልስ ሰጥተዋል።

"ጥፋተኞች ነን" ብላችሁ ፈርሙ ሲባሉ "አሻፈረን" ብለው ስለከበረው እምነታቸው ዋጋ ከፍለዋል። ስንቅ ያቀብል የነበረውም ሆነ በመጨረሻ ዋስ ሆኖ ያስፈታቸው አባቴ ነበር።

"ወዮ አባቴ ምነው ነፍስ ዘርተህ እንደበትህን ከፍተህ በተናገርክ! በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን መዳን ተቀዳጅተህ በሞት አሻጋሪነት በአምላክህ እቅፍ ዘላለማዊውን ድንቅ ሕይወት መጀመርህን ትገልጽላቸው ነበር!" በቃ.. ለለቀ እንግዲህ! አልኩ በልቤ።

ወንድሜን ገብሩንና ሌሎች ዘመዶቻችንን ሁሉ አስቤ! "ለእነሱ የምሰብከው የመዳን

ጉዳይ እንዲህ ሲያስወግዘን ባደባባይ!" "ኧ! ወንድሜ ገብሩና ገና ወደ ጌታ እንዲመጡልኝ የምጸልይላቸው የቅርብ ዘመዶቼ! ክርስትና እንዲህ በሕዝብ ፊት ውግዘት የሚያስከትል መሆኑን ሲያዩ ምን ይላሉ? እኔም ሆንኩ የቅርብ ጓደኞቼ ለእነዚህ ሁሉ የምንመሰክርላቸው የጌታን ተአምር አድራጊነት፣ ፈዋሽነቱንና ጸሎት መላሽነቱን...እንጂ የምንሸከመውን መስቀል አልነበረም!" አልኩኝ። የኔውስ ግድየለም! ግን ለእናቴ እና ሌሎቹም ጌታን ላገኙት በዕድሜ ትልልቅ ለሆኑት ዘመዶቼ አዘንኩላቸው። በሕዝብ መካከል እንዲያ መባላቸው። እናም አላዋቂው ልቤ አዘነ።

አላዋቂ ነበርኩ እውነትም! ለካስ፣ "ሰው የደረሰበት ኃዘን ሳያንሰው እንዲህ ይወቀሳል እንዴ?" ብዙዎችን አስብሎ አስቆጥቶም ኖሯል! ይሄም ብቻ አይደለም! የሰው ልጆች የልብ ቁልፍ ያለው እግዚአብሔር ለካስ በወንድሜ ገብሩም ልብ ሥራ ጀምሮ፣ በዚያ በአባቴ የቀብር ስፍራ፣"እኔ ደግሞ ከዛሬ ጀምሮ የእናቴንና የቤተሰቤን እምነት እከተላለሁ!" ወደሚል ታላቅ ውሳኔ እንዲደርስ አድርጎት ኖሯል! ለካስ ጀግናው ክርስቶስ አባቴን ወደራሱ ሲሰበስብ ለእኛ ደግሞ 12 ዓመት ያስቆጠረ ዕንባና ጸሎት ሊመልስ ወንድሜን ከዓለምና ከሰይጣን መዳፍ ማርኮ እንበርክኮታል።

በአባቴ የመቃብር ስፍራ በወንድሜ ልብ ውስጥ የተካሄደውን ተአምራዊ ውሳኔ ማንኛችንም አላወቅንም። ወንድሜ በአባታችን ሞት እጅግ ልቡ ተነክቶ ከባድ ኀዘን ወድቆበት እንደነበር አውቃለሁ። ወንድሜ በተፈጥሮው ብዙ የዕንባ ሰው አልነበረም በአባታችን ሞት ግን ሀዘኑ ጥልቅና በገሃድም የሚታይ ነበር። በዚህ በሀዘኑ ጊዜ ከቀብሩ ዕለት በኋላ የዓለም ጓደኞቹን እስኪታዘባቸው ድረስ ከአጠገቡ አጥቷቸዋል። በምትኩ የወላጆቻችን ቤት ከንዳ እስከ ድንኳን በፍቅር ታጥቀው ባገለገሉን ክርስቲያን እህቶችና ወንድሞች ተሞልቷል። ባጠገቡ ሆነው ያጽናኑት ሀዘኑን የተካፈሉት ያው ለረዥም ዓመታት የሚያውቃቸው የእኔ ጓደኞች ናቸው። ፍቅራቸው እውነተኛና ለበጣ የሌለበት መሆኑ በራለት፤ አስተዋለ። መዝሙሩ የሚነገረው የእግዚአብሔር ቃል በሙሉ ለልቡ ጠገን ሆነለት። ሁሉም በስውርና በውስጡ ያደረገውን ክቡር ውሳኔ የሚያጸናለት "እሰይ አበጀህ" እያለ በልቡ የሚያስተጋባ አዋጅ ነበር።

ግሩም ድንቅ ነው ያምላክ ሥራ! አባታችንን እግዚአብሔር ሲወስደው ወንድሜን ገብሩን ደግሞ ለቤተሰቡ አባትና አጽናኝ አድርጎ ሰጠን! የመንፈሳዊ ሕይወት እድገቱ የቃል መረዳቱ የጸሎት ጥማቱ... በጣም የሚያስገርም ዓይነት ሆነ! ለብዙ ዓመታት የጸለይንለት ወንድሜ ወደ ጌታ መምጣት ብዙ መጽናናት ለልቤ አድርጓል! ወንድሜ ገብሩ ላለፉት 32 ዓመታት ጸንተው በመቆም እግዚአብሔርን ካስከበሩትና በረከት ከሆኑት ቅዱሳን አንዱ ሆኖ ይኖራል!

ውዴ ጥበቡ! የወንድሜ ገብሩን ከዘላለም ገሃነም ማምለጥ በምን ላውራው? ደስታው ወሰን አይኖረውም ነበር! የወንድሜን መለወጥ ለማየት አበክረው ከሚጸልዩለት መኻል እንደነበር አውቃለሁ። የሰው ልጆች ሁሉ "ነገ" ብሩህ እንዲሆን ምኞቱ ነው እንኳንስ ከዚያ በስቲያ ያለው "የዘላለም ዕድሜ"! እናም ውዴ በሶማሊያ በእግዚአብሔር ፊት በተንበረከከ ቁጥር ስለኔና ስለልጆቻችን ሁሌም በጸሎት ሲቀርብ በዚያ ካምፕ ውስጥ ያለው የሰፊው ቤተሰቡ ጉዳይ የማይቀር ነው። እሱ ባለበት በሐዋይ የምርኮኞች ካምፕ የእግዚአብሔርን ፊት የሚፈልግበት ጉዳይ አለው!

****

*እንደማያልፍ የለም!*

"ወደ ሺ የሚጠጉ ልጆች እግዚአብሔር ሆይ!"

"እግዚአብሔር ሆይ! እነዚህ ሁሉ ወጣቶች አሁን ካልተማሩ ዕጣ ፈንታቸው ምንድነው? አንድ ቀን ወደ ምድራችን ትመልሰናለህ እምናለሁ! ሊስትሮ? ሚሊሽያ? በረንዳ አዳሪ? ካልተማሩስ ከዕድሜ እኩዮቻቸው ተቀላቅለው መኖር ይችላሉ?

ካምፑ ውስጥ ልጆች ባየ ጊዜ ሁሉ ውስጥ ውስጡን ሲብላላ የቆየ ጥያቄና ጸሎትም ነው። ከአቅሙና ከሚችለው ሁሉ በላይ ሆኖበታል። ሐዋይ ለግሉ በነበረችው በመጀመሪያዋ ጠባብ ሰፍራም ቢሆን፣ ያ ሰውን ሁሉ የሚወድ ልበ ሰፊው ጥበቡ፣ ወደራሱ ያስጠጋቸው አሥር ልጆች ነበሩት፤ ጥበቡ የራሱ አድርጎ ወስዶ የአባትነት ፍቅርና እንክብካቤ ሊሰጣቸው ጀምሯል። ግን የተቀሩት እጅግ ብዙ ልጆችስ? ጥበቡን አላስቆም አላስቀምጥ ያለው ከባድ ሸክም ሆኖበት ያለዕረፍት ሲያስብ ሰንባብቷል። ከአድካሚ የሩዝ እርሻ ሥራ ወገቡ እስኪንቀጠቀጥ እግሩ እስኪዝል ውሎ የሚመለሰውን መከረኛ ሕዝብ፣ ጥበቡ ምን አፍ አለውና "የተማርክ አስተምር" ብሎ ወደወገኖቹ ይውጣ? ልጆቹስ ቢሆኑ፣ ውሏቸው ሩዝ እርሻው ላይ አይደል? ጥበቡ በልቡ የሚያልማቸው ተማሪዎችም ሆኑ አስተማሪዎች የመላእክት ጉልበት ካልተሰጣቸው ስጋ በለበሰ ሰው አቅም ከቶ የሚታሰብ አይሆንም!

ብቻውን አልቻለውም በቃ! አገር ቤት ሳሉ ሥራቸው መምህርነት የነበረ ስድስት ፕሮፌሽናል መምህራን ካምፑ ውስጥ አሉ። የማስተማር ብቃት ያላቸው ዩኒቨርሲቲን ያገባደዱ ተማሪዎች፣ እንዲሁም አንድ አግሮኖሚስት አንድ ጤና መኮንንና ሦስት ነርሶች ደግሞ አሉ። "እነዚህን ወጣቶች የማስተማር ታሪክ የጣለብን ኃላፊነት አለብን። እያለ ለመሰል እስረኛ ጓደኞቹ የልቡን ሸክም ማዋየት ጀምሯል። ነገሩ ብዙዎችንም እደሰበ የመጣ ጉዳይ ነው። ግን ምን ማድረግ ይቻላል? ሕዝቡ ካለበት ሁኔታ የተነሳ የእነዚህን ወጣቶች ዕጣ ፈንታ፣ "መሃይምነትና ሞት የተፈረደበት!" ብሎ ፋይሉን እንዲዘጋው የተገደደ ይመስላል። "ያገሬ ሰው እዬዬም ሲደላ ነው" እንደሚል፣ ያ መከረኛ ሕዝብ የገዛ ራሱ ሰቆቃ እያለ "ምን ደልቶት" ስለወጣቱ ነገ "ወዮ" ይበል?? "ሁሉን የምትችል አምላክ ሆይ መንገድህን አሳየኝ! ብርሃንህን አብራልኝ!"

የካምፑ ዳይሬክተር ኮሎኔል አህመድ ሁሴን! ጥበቡ በጸሎቱ ውስጥ ይሄን ሰው አሰበ። ሰውዬው ጥበቡን እንደትልቅ ባለውለታው ይቆጥረዋል። ካንዴም ሁለት ሶስቴ ካምፑ ላይ ሊደርስ ከሚችል ከፍተኛ የተላላፊ በሽታና እልቂት የጥበቡ ምክርና ጥበብ ከጉድ አውጥቶታል! በሁሴን እይታ "ሩዙ እርሻ ላይ የሚያሰራው ሠራተኛ እንዳያጣ" ጥበቡ አድኖታል። የእኔ ውድ ጥበቡ እይታና አጀንዳ ግን ሌላ ነው። "የባርነትና የግፍ ቀንበር የወደቀበትን ያን ታላቅ ሕዝብ ጤናውን ጠብቆና ከሞት ተናጥቆ፣ ላገር ለምድሩ ማብቃት" ነው!

ዛሬ ጥበቡ የኮሎኔሉን በር የሚያንኳኳው የዚህን ሰው ማንነትና ሰብዐዊ ርህራሔ የሚመዝን፣ የሚፈትሽም ከባድ ጥያቄ ሊጠይቀው ነው። ደግሞም፣ ኮሎኔሉ ትልቅ ውለታ እንዲውልለት ጥበቡ ሊጠይቀው ነው።

"ኳኳ ኳኳ!"

"ግባ! ማን ልበል? ..ሰላም ዶክተር ምን ልታዘዝ?"

በተረጋጋ መንፈስ ሆኖ ጥበቡ ጉሮሮውን ጠራረገ። ስለሕዝቡም የጤንነት ሁኔታ ገረፍ ገረፍ አደረገለት። እናም ወደዚህ ሰው ያመጣውን የልቡን ሸክም ጥበብ በተሞላው አነጋገሩ እንዲህ ሲል ጀመረ።

"ኮሎኔል ሁሴን፣ ከሩዝ እርሻ ሲመለሱ፣ ልጆች ካምፑ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያሉ

ለዲሲፕሊንም ያስቸግራሉ። ወደ እርሻውም የማይሄዱ ትናንሽ ልጆች አሉ፤ እጉል እጉል በመል ሊያበጁ የሚችሉ፣ ካላስተማርናቸው። ምን ይመስልሃል አንድ የሆነ ቦታ ላይ ሰብስበን ትምህርት ብንጀምርላቸው?"

ጥበቡ የኮሎኔሉን ልብ ለመሰለል የሰነዘረው የመጀመሪያ ጥያቄ ነበር። እምላኩ እግዚአብሔር ግን ፈጣን በሆነ አሰራሩ አስደነቀው።

"እስማማለሁ ዶክተር ጥሩ ሃሳብ ነው ቢማሩ!"

ለካስ አህመድ ሁሴን ደግሞ ደጋግሞ ባየው በጥበቡ ማንነት ተረቷል። በምርኮ ለተያዙትም ወገኖቻችን መልካም ለማድረግ "ቅን" ከነበሩት መኮንኖች አንዱ ይህ ሰው ሆኖ ተገኘ! እስረኞቹን በሚመለከት ጥበቡ የሚያቀርብለትን ሃሳብ "እሺ" የሚልና የሚተባበር ሰው!

የኮሎኔሉን "እሺታ" ያገኘው ጥበቡ አስቸኳይ እርምጃዎች ወዲያውኑ ወሰደ። አብረዋቸው እያደሩ ከሚያስተምሯቸው ትልልቅ ሰዎች ጋር መቶ ልጆች የሚይዝ እስር ቤት ለወንዶች አዘጋጀ። ለሴቶቹም ካምፕ እንዲሁ! የዱቄት ወተት ወረቀቶች ለደብተርነት አገለገሉ። ከባትሪ ድንጋይ ቀጥቅጠው በሚያወጡት ጥቁር ቀለም ከርቶኖች ቀብተው፣ ብላክ ቦርድ ሰሩ! የአባኮዳ (ትልቅ አሞራ!) ኩስ እንደ ጠመኔ (ቾክ) አገለገለ! የካምፑ አመራር ለተማሪዎቹ የሚሆኑ እርሳሶች አቀረበ። ጥበቡ አሁንም ከኮሎኔል ሁሴን ማግኘት የሚፈልገው አንድ ፈቃድ ቀርቶታል፤- ለአስተማሪዎቹ!

"ስድስቱን መምህራንና ሠላሳ የሚያህሉ አጋዥ መምህራን ወደሩዝ እርሻ የጉልበት ሥራ እንዳይላኩ ፈቃድ!"

ፈቃዱ በይፋ ተሰጠ! እነዚህ መምህራኖችና ረዳቶቻቸው ያንን በልጅነት የምርኮኝነት ዕጣ የወደቀበትን የወጣት ትውልድ ኃላፊነት ተረከቡ! በጨካኝ የባርነት ጨለማ ውስጥ ለተጣለው ተተኪ ትውልድ የዕውቀት ጮራ ሊፈነጥቁለትም ቆራጥ ውሳኔ አደረጉ። ጥበቡን ጨምሮ መምህራኖቹ፣ እንዲሁም አግሮኖሚስቱ አቶ ንጉሤ፣ ጤና መኮንን ቡርቃና ነርሶቹ . . ሁሉም ተመካከሩ። ምሁራኑ ጥቂት ቢሆኑም እንኳ ከየአእምሮአቸው የሚያስታውሷቸውን የትምህርት ዐይነቶች አውጣጡ። ለየክፍሉ የሚያስፈልገውን ካሪኩለም ከእነዚህ ወገኖቹ ጋር ተባብረው ቀረጹ። እነዚያ የጥበቡን ልብ ያስጨነቁት የኢትዮጵያ ልጆች ትምህርት ሊማሩ፣ ሁሉ መልክ መልክ መያዝ ጀመረ!!

ትምህርቱ እንዲቀጥል በኮሎኔል ሁሴን የወሀኒው አመራር ስር ተአምራዊ ድጋፍ አግኝቷል። መምህራኖቹ ግን የሚያስተምሩባቸው በቂ መጻሕፍት (ቴክስት) የላቸውም። ተፈላጊዎቹ መጻሕፍት ባብዛኛው በሱማሊኛ ቋንቋ የተጻፉ ስለነበሩ። ቆርጠው የተነሱትን መምህራን ያም አላገዳቸውም! ከአእምሮአቸው በሚያፈልቁትና በሚያስታውሱት መጠን ለማስተማር ታላቅ ተጋድሎ ላይ ናቸው። ጥበቡ ኃይለሥላሴ፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ የሶማሊኛ ቋንቋ መናገር ማንበብና መጻፍ ተምሯል። ተፈላጊዎቹን የሶማሌ መጻሕፍት እየተረጎመ ኖት ማውጣትና ማቅረብ የቻለ ቡድንም ተቋቁሟል። ሱማሊኛንም የትምህርት ቤቱ እንቅፋት ላይሆን አንከባለሉት!

ኦ! የኔ ጥበቡ! ከልባዊ ፍቅሩና ከሰው ወዳድነቱ የመነጨው ይሄ የትምህርት ተቋም አይደለም ለገዛ ወገኖቹ፣ ለነጻነቱ ጠላቶች ለሶማሌዎቹ እንኳን የዕወቀት ጮራን ፈነጠቀላቸው። የሶማሌ ወታደሮችም ትምህርትና ዕውቀት ፍለጋ ወደወህኒው ትምህርት ቤት መቀላወጥ ጀመሩ። ለጥቅማቸው ሲሉ ምሁሮቻችንን በአክብሮት ማየትና መለማመጥ ጀመሩ። ወህኒው ውስጥ ያልነበሩ ተፈላጊ የእንግሊዘኛ መጻሕፍትንም ወታደሮቹ ለራሳቸው ሲሉ እየገዙ ማምጣት ጀመሩ። ለተማሪዎቹ የሚያስፈልገውን ደብተርና እርሳስም ማቀራረብ ጀመሩ። ያልነበረ፣ ታይቶና ተገምቶ የማይታወቅ የመተሳሰብና የመቀራረብ አየር ምናልባትም ለመጀመሪያ ጊዜ በወገኖቻችንና በሶማሌዎቹ መካከል

መንፈስ ጀመረ! የሚታይ የሚጨበጥ ፍሬም አፈራ።

ሐዋይ ከተማሩት ወታደሮች መኻል ስኮላርሺፕ አግኝቶ ወደ ካናዳ ሲጓዝ ናይሮቢ እኔና ጥበቡ ያገኘነውን ሶማሌያዊ አልረሳውም። እንዴት በጥበቡ አንገት ላይ እንደተጠመጠመና የጥበቡን ምላሽ ያየ ምን ያህል ይደነቅ ነበር! በሚያስገርም ልባዊ ፈንጠዝያ ሆኖ ሶማሌውን በቋንቋው ሲያወራው እጅግ የሚወደውንና የሚናፍቀውን አብሮ አደግ ጓደኛውን ያገኘ ይመስል ነበር።

የሐዋይ ወህኒ ትምህርት ቤት ይተነፍስ የነበረውን የነጻነት አየር የሚበክሉ አንዳንድ ችግሮች መፈጠራቸው ግን አልቀረም። ለወጣቶቻችን የተደረገውን በጎነት ከሚቃወሙት ወታደሮች መካከል ልጆቻችንን ለግል ሥራቸው ወስደው ጉልበታቸውን የሚበዘብዙ ነበሩ። "የሩዝ እርሻው ሥራ ተበደለ" በሚል ሰበብም ትምህርት ቤቱ እክል እንዲገጥመው ጥረት የሚያደርጉቱ ደግሞ ሌሎቹ ነበሩ። የትምህርቱ ተቃዋሚዎች በሚፈልጉት መጠን የተሳካላቸው ግን ኮሎኔል ሁሴን ሲቀየር ሆነ። የተተካው የካምፑ ዳይሬክተር በጥላቻ የተሞላ ነበረ። "እስረኞቹ ሥራቸው በሩዙ እርሻ ላይ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ለሶማሌ መንግሥት ማበርከት ነው እንጂ መማር አይደለም" ሲል ለወህኒው አመራር ትእዛዝ አስተላለፈ። የትምህርት ቤቱንም ሕጋዊነት ሻረ።

ወገኖቻችን ግን ለወጣቱ የፈነጠቀው የዕውቀት ብርሃን ደብዝዞ እንዳይጠፋ ስውር ትግላቸውን ቀጠሉ። ትምህርት አሰጣጡ በሚሥጥር ነጎደ! ማታ በየወህኒው፣ ቀን በየዛፍ ጥላውና በየወህኒው ጓሮ ቀጠለ። የጥበቡ መኖሪያም አንዱ የሚሥጥር ትምህርት ቤት ሆነ። ወታደሮቹ እሱን ስለሚያከብሩት ዘልቀው አይገቡም። ልጆቹ ለትምህርት ያላቸው አስደናቂ ጉጉት፣ መምህራኑ ለማስተማር በልባቸው የታመቀባቸው ትጋት፣ የተጫነባቸውን ቀንበር ከምንም እስከማይቆጥሩት ድረስ ቆራጦች አደረጋቸው።

እዚህ ላይ፣ ከጥበቡ ጋር ሆነው የየድርሻቸውን የታሪክ ኃላፊነት በክብር የተወጡትን ሳልጠቅስና ሳላደንቅ ባልፍ በጀለኛ እሆናለሁ፤ ሁሉም ቢያወሩት/ቢጽፉት አስደናቂ ታሪክ ያላቸው ናቸውና። እንጀታቸው እየታጠፈ፣ ጉሮሯቸው በውሃ ጥም እያረረ በቆራጥነትና በአስደናቂ መስዋዕትነት ያን ሁሉ ወጣት ከመሃይምነት ነፃ አወጡት! ከሰማኋቸው የመምህራን መስዋዕትነት የተሞላ ታሪክ ውዱ ጥበቡም የተገረመበትን የአንዱን ሰው ላውራላችሁ።

ስሙ አቶ ጥላሁን አትሬሶ ይባላል። "የኛ ሰው በሶማሊያ እስር ቤት" በሚል ርዕስ የወጣው መጽሐፍ ደራሲ ነው። ታሞ ወህኒው ሆስፒታል ተኝቷል። ጥበቡ ሊያየው በሄደ ጊዜ ሁሉ የሚያገኘው አጠገቡ አስቀምጦ ልጆች ሲያስተምር ነው። ሕመሙ እንኳ ልጆቹን ከማስተማር ስላላገደው የጥላሁን ልብ ምን ያህል ለዚህ ተጋድሎ እንደ ተሰጠ የኔ ውድ አይቶታል። ልጆች ለማስተማር በፈቃደኝነታቸውና በትጋታቸው እያደነቀ ከሚያነሳሳቸው የሐዋይ መምህራን መካከል አንዱ ጥላሁን እንደነበር አውቃለሁ፤ ከሕመሙ በላይ የእነዚያ ወጣቶች ነገር የተሰማው በመሆኑ። ከሰሩ ከሚያሳድጋቸው ስድስት ልጆች መሀል ከ1-5 ማእረግ የወጡበት ጊዜ ነበር። ትጉ አስተማሪነቱን ለማድነቅ ነው የጠቀስኩት። አቶ ጥላሁን ታሞ በተኛበት አልጋ አጠገብም በእሱ አስተባባሪነት የሚካሄድ የወህኒው "ላይብራሪ" ነበራቸው። መጻሕፍቱ በአይነት አንድ ቢሆኑም ተሰባስበው ወደ ጥላሁን ይመጣሉ። መጻሕፍቱን ወደ ወህኒው ለማስገባት ባብዛኛው የሶማሌ ወታደሮችም ተባብረዋል። ከካርቶን በተሰራ ሼልፍ ላይ የተደረደሩትን እነዚህ ብርቅዬ መጻሕፍት ተውሶ ለማንበብ የልጆቹ ጉጉት የሚያስገርም ነበር። ወጣቶቹ ሊያነቡ የሚፈልጓቸውን መጻሕፍት ለሥራ ወጥተው ሲመለሱ በሌላ ተቀድመው ሲያገኙ ምን ያህል ይሰማቸው እንደነበር አቶ ጥላሁን ይናገራል።

ሌሎች አድናቆት የሚገባቸው የኢትዮጵያ ልጆች አንዳንድ መኮንኖች የግል ሠራተኞች

አድርገው የወሰዷቸው ወጣቶቻችን ናቸው። በታማኝነታቸውና በጨዋነታቸው የተነሳ አሳሪዎቻቸው ለምርኮኞች ወገኖቻችን ርህራሄ እንዲኖራቸውና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያደርጉ ረድተዋል። ለመከራና ለባርነት በእጃቸው አልፎ በተሰጠው በዚያ ሕዝብ ላይ መኮንኖቹ ተጨማሪ መከራና ቀንበር እንዳይጭኑበት እነዚህ ታማኝ የኢትዮጵያ ልጆች አስገራሚ አስተዋጽዖ አበርክተዋል። አንዳንዴም የሕዝቡን ስሞታና ጭንቀት ወደ አለቆቻቸው በማድረስና ለማስለወጥ በመሞከር ረገድ የነበራቸው አስተዋጽዖ ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም! በካምፑ አለቆችና በምርኮኞቹ መካከል ሁኔታዎች ሲከረሩ በማርገብም የረዱ የሕዝባችን ባለውለታዎች ናቸው።

የኔ ውድ ጥበቡ! የአምላኩ የእግዚአብሔር ሃሳብ ገብቶታል። ሐዋይ ካምፕ ውስጥ እግር ጥሎት ወይንም አጋጣሚ ሳይሆን ያመጣው በእግዚአብሔር መለኮታዊ እቅድ መሠረት እንደሆነ አውቋል። ገና ዩኒቨርሲቲ ሳለ ትምህርቱን አቋርጦ "ጌታን ለማገልገል ካልወጣሁ" እያለ በጸሎት በነበረበት ጊዜ የመጣለት የእግዚአብሔር ድምጽ፣ የአሁን ያህል ይሰማዋል። በእርግጥ በትምህርቱ እንዲቀጥል እግዚአብሔር ለምን እንደተናገረው እጅግ ግልጽ ሆኖለታል። "ለዚህ ምስኪን ሕዝብ!"። ስለዚህ ያለእንቅልፍና ያለዕረፍት ለሕዝቡ እንዲሰጥ ስለረዳው አገልግሎት ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

ወህኒውን በሚመለከት የአካባቢው ጨፌያማነት አሁንም ልቡን አላሳረፈውም። የሕዝቡን ጤንነት የሚያውኩ የወባ ትንኞች ቆሻሻው ውሃ . . . ወዘተርፈ አሁንም በቢይ ችግሮች መሆናቸው ቀጥሏል። ስለዚህም ዘላቂ የሆነ መፍትሄ ሲያስብና ሲጸልይ ስነበተ። እንደማያልፍ የለም፤ የዚያም ጨካኝ የካምፕ ኃላፊ ዘመን አከተመና በሁለት ወጣት የካምፕ ዳይሬክተሮች ተተካ። አሊ ዑመርና ኢብራሂም ይባላሉ። ለእስረኛው ሕዝብ የሚያዝን ልብ አላቸው። ልጆቹንና ወጣቶቹን እንዳያመነጫጭቋቸው ወታደሮቹን ከለከሏቸው። እንዲያውም ከእስረኞቹ ጋር ኳስ ጨዋታ ሁሉ ይጫወቱ ነበር።

****

## *በታም መርጠህ ጨርስሃል ማለት ነው?*

እነዚህ አዲስ መኮንኖች እንደተቀየሩላቸው አንድ ቀን ጄኔራል እስማኤል አህመድ የሶማሊያ ወህኒ ቤቶች አጠቃላይ ዳይሬክተር የሐዋይን ካምፕ ለመጎብኘት መጡ። ጥበቡ ከዚህም በፊት በተደጋጋሚ ከእኚህ ባለስልጣን ጋር ስለወገኖቹ ደህንነትና ስለመድሃኒቶች እጥረት ስለካምፑ አጠቃላይ ሁኔታ ተነጋግሯል። ጄኔራል እስማኤል አስተዋይና መልካም ሰው እንደነበሩ ጥበቡ ይናገራል። ምርኮኞቹን በጥንቃቄና በአክብሮትም እንዲይዟቸው መኮንኖቻቸውን ጠንከር አድርገው ሲገስጽዋቸው የሰማውን ሲናገር እንዲህ ብሏል።

> "እነዚህ ዛሬ ምርኮኛ ሆነው በእናንተ እጅ የሚገኙት ሰዎች በሀገራቸው የተከበሩ ሰዎች መሆናቸውን አትርሱ። በሁለት ሀገሮች መካከል በሚሆን ጦርነት ሳቢያ ሰዎች ምርኮኞች ይሆናሉ። ኢትዮጵያና ሶማሊያ እርቅ ቢፈጥሩ ነገ ከእነዚህ መኻል በሹመትና በሥራ ወደእኛ ሊመጡ ይችላሉና በኋላ የምናፍርበት ነገር አናድርግ"

ካሉ በኋላ ስለአንድ ታሪክ ተናገሩ።

> "ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረራት ጊዜ ከማረካቸው ምርኮኞች መኻል አንዱ አቶ ከተማ ይፍሩ የታሰሩት ደናን እስር ቤት ነበር። በኃይለሥላሴ ዘመን አቶ ከተማ የኢትዮጵያ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው ወደ ሶማሊያ ለስብሰባ መጡ። ሄደው መጎብኘት የፈለጉት የመጀመሪያ ቦታ፣ ጣልያን በምርኮኝነት አስሯቸው የነበረበትን የደናን ወህኒ ቤትን ነበር። ስለዚህ እነዚህም ነገ በምን ሥልጣን ወደአገራችን ተመልሰው እንደሚመጡ ስለማናውቅ በጥንቃቄ ልንይዛቸው ይገባል።"

ጄኔራል እስማኤል መኮንኖቻቸውን መምከር ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም በተግባር ሲያደርጉት የኔ ውድ ያያቸው ይሄንኑ ነበር። ጄኔራሉ ጥበቡን ይወዱታል ያከብሩታልም። በመጡ ጊዜ ሁሉ ከራሳቸው መኮንኖች ይልቅ ለእስረኞቹ ከጥበቡ መስማትን ይመርጣሉ። ጥበቡ ኃይለሥላሴ ዛሬ ለእኚህ ጄኔራል የሚያቀርበው በቢይ አጀንዳ አለው።

"ጄኔራል፣ በዚህ በምንገኝበት ሁኔታ የእስረኛውን የጤንነት ኃላፊነት መቀበል አልችልም!" ጄኔራል እስማኤል የተለመደውን ጥያቄ ነው ከጥበቡ የጠበቁት።

"ምን ተቸገርክ ዶክተር? የመድሃኒቶች ችግር አሁንም አልተቃለለም?"

"ዛሬ እሱ ብቻ አይደለም ጥያቄዬ። ወህኒቤቱ የተቀመጠው ተላላፊ በሽታዎች መናኸሪያና መነሺያ መካከል ስለሆነ በመድኃኒት ርብርቦሽ የምናደርገውን ጥረት ሁሉ ውድቅ አድርጎብናል። እኛም መድኃኒት ማደላችንን አላቋረጥንም በሽተኞችም በቁጥርም ሆነ በአይነት መጨመራቸው አልቀረም።"

"ታዲያ ምንድነው መፍትሄው? ተጨማሪ መድኃኒት?"

አይደለም ጄኔራል! ካምፑ በጠቅላላ ከዚህ ከጨፌያማ ቦታ ተነስቶ ደረቅ መሬት ላይ በአዲስ መልክ መሰራት አለበት! የወባ ትንኞች፣ የኢንፌክሽንና የተላላፊ በሽታዎች ጎሬ ከሆነው ከዚህ ረግረግ ቦታ ሕዝቡን ማንሳትና አዲስ ካምፕ ሰርቶ ማስፈር አማራጭ የሌለው መንገድ ነው። የሕዝቡን የጤንነት ጠር በተሻለ ሁኔታ መቆጣጠር የሚቻልበት መንገዱ እሱ ብቻ ነው።"

ጄኔራል እስማኤል ዛሬ ከጥበቡ አፍ የሚሰሙት ጉዳይ አልጣማቸውም። በሌላ ጊዜ ሁሉ የጄኔራሉ ጆሮዎች ለጥበቡ ክፍት ነበሩ። ዛሬ ግን...

"ሊሆን አይችልም ዶክተር! ሌላ ካምፕ መሥራት ቀላል ነገር አይደለም!"

"የእስረኛው ጤንነት በተሻለ የሚጠበቅበትን ሁኔታ ካላመቻቻችሁ፣ ከሩዝ እርሻው ይልቅ እንግዲህ ሕዝቡ ሁሉ ህመምተኛ ሆኖ አልጋ ላይ መዋሉ ነው! ማለቁም ነው! ምርጫውን ለእናንተ እተዋለሁ!"

የሩዙ እርሻ! አሁን ገና ባይኑ በብረቱ መጣበት።

"እሺ ላስብበት ትንሽ ጊዜ ስጠኝ ዶክተር!"

የኔ ውድ! የጄኔራሉ ሃሳብ ትንሽ ዘንበል እንዳለለት አስተውሎ

"ብዙም እሩቅ ሳይኬድ ቅርብ ኪሎሜትር ላይ ደረቅና አመቺ ቦታ አለ!" አላቸው።

ጄኔራል እስማኤል በዚህ አስገራሚ ሰው እየተደነቁ ከፈገግታ ጋር

"ቦታም መርጠህ ጨርሰሃል ማለት ነው?!"

"አይ! ሃሳብ ማቅረቤ ነው። እዚሁ ቅርብ በክረምት ጎርፍ እማያሰጋው ጥሩ ቦታ አይቻለሁ።"

"መልከም ባስቸኳይ ሥራው እንዲጀመር አደርጋለሁ።"

"ሌላስ ምን ጉዳይ አለህ?"

ኦ! የኔ ጥበቡ! ይቺማ ብዙ ሲጸልይባት የቆየባት ምቹ ሰዓት ናት! ሊያልፋት አይፈልግም። አዲሶቹ

መኮንኖች ከዚህ በፊት በህጋዊነት ይሰራ ስለነበረው የወህኒው ትምህርት ቤትም ሆነ በተቀየረው መኮንን ስለመከልከሉ ገና ያወቁት ነገር የለም። ጄኔራሉ ደግሞ የሚያውቁት ወህኒው ውስጥ የተፈቀደለት ትምህርት ቤት እንደነበር ነው። ስለዚህ በሚያስገርም ጥበብ እንዲህ አለ።

"ጄኔራል መቼም በጣም ነው የማመሰግነው በእስረኛው ስም፤ ስለተፈቀደልን ትምህርት ቤት። በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ነው። የማቴርያል ችግር ግን አለብን። ደብተር እርሳስና መጻሕፍት . . . በዚሁ አጋጣሚ ሌላ ተጨማሪ ነገር የምጠይቀው አዲስ ከሚሰራው ካምፕ ውስጥ ትምህርት የምንሰጥበት ሰፋፊ ቤቶች እንዲሰሩልን፣ አንድ የወንዶች ትምህርት ቤት አንድ ደግሞ የሴቶች።"

"መልካም! የመድሃኒቶቹን ሊስት አዘጋጅተህ ለመኮንኖቹ ስጣቸው። ትምህርት ቤቱም በጥያቄህ መሠረት እንዲሰራ አደርጋለሁ።"

እስደናቂ ድል!! የኔ ጥበቡ ልቡ ቸከለ! ወጣቱን ከመሃይምነት መዳፍ የሚያላቅቅ ድል ከአምላኩ ያን ዕለት በይፋ ከወህኒቤቶች ሁሉ የበላይ ከሆኑት ከጄኔራሉ ተረከበ። ይህ ታሪካዊ የወህኒ ትምህርት ቤት ሁለት ጊዜ 12ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ወጣቶችን አስመርቋል። ተማሪዎቹ ወደአገራችን ከተመለሱ በኋላ በየክፍላቸው መጠን ፈተና ተሰጥቷቸው በከፍተኛ ውጤት አልፈዋል። ዛሬ ከሐዋይ ወህኒቤት የቀድሞ ተማሪዎች መኻል ፣ በትምህርታቸው የገፉ እስከማስተርስ ዲግሪ ያጠናቀቁ ይገኙባቸዋል። ለዓይነት ያህል ጥቂቶቹ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተናገሩትን አንብባችኋል።

የኔ ውድ! ሐዋይ ውስጥ ሌትና ቀን ይሰራል፣ ይጸልያል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ያነባል። የእንቅልፉ ሰዓት 3 ና 4 ሰዓት ብቻ ነው። ዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለ ጥናቱንና መንፈሳዊ ሕይወቱን አመጣጥኖ የያዘበት ዘዴ፣ ያጭር ጊዜ እንቅልፍ ልምምድ ሐዋይም ጠቅሞታል። ይህንና ሌላውንም አስመልክቶ ጤና መኮንን ቡርቃ ስለ ጥበቡ ሲናገር እንዲህ አለ።

"የእኔና የእሱ እምነት የተለያየ ቢሆንም በብዙ ስለእሱ የምደነቅበትን ሀቅ መሸሸግ አልችልም። ዶ/ር ጥበቡ አምስት ደቂቃ ዕረፍት ቢኖረው ያቺን ጊዜውን በጸሎት ወይንም መጽሐፍ ቅዱሱን በማንበብ ነው የሚያሳልፈው። አሥራ አንድ ዓመት ሳንለያይ በዚያ እስርቤት አብረን ኖረን በቅርብ ሆኜ አይቼዋለሁ። ሀያ አራት ሰዓት መጸለይ እና መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ የሚችል ሰው እንደሆነ ነው የተገነዘብኩት። ዶ/ር ጥበቡ በሳምንት ሁለት ወይ ሦስት ቀን ይጾማል ምግብ አይቀምስም። የዶ/ር ጥበቡን ያህል ጉልበትና አቅም በዚያ እስርቤት ውስጥ ያለው ግን ማንም አልነበረም። የሄንን እኔ ብቻ ሳልሆን እዚያ የነበሩ ሁሉ ይመሰክራሉ። ሀያ አራት ሰዓት ያለማቋረጥ የሚሰራ ሰው ነው። ዶ/ር ጥበቡ ሰውን በእምነት በዘር በዕድሜ ሳይለይ ሶማሌዎቹን እንኳን ሳይቀር የሚወድ ሰው ነው። የሰው ሁሉ ወዳጅ ነው። ዶ/ር ጥበቡ ከእስር ቤቱ መኮንኖች ጋር የቅርብ ግንኙነት ስለነበረው በትምህርትም ሆነ በመድኃኒት በኩል የሚያስፈልገንን የሚያስገኝልን እሱ ነበረ። የወንዶችና የሴቶች ካምፕ የተለያየ ስለሆነ አንድ ቀን እኔ አንዱጋ ብሆን፣ እሱ ደግሞ ሌላውጋ ይሆናል። ትምህርትን በሚመለከት ደግሞ ብዙ መጻሕፍትን በማግኘት ካሪኩለም በመቅረጽ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ዶ/ር ጥበቡ ነበረ። እያንዳንዱ ተማሪ ደግሞ ወደአገር ቤት ሲመለስ የየደረሰበትን ክፍል የሚገልጽ ሰርቲፊኬት አዘጋጅተን ለኢትዮጵያ መንግሥት እንድናቀርብ ያደረገውም ዶ/ር ጥበቡ ነው። በዚህም መሠረት ሐዋይ ያስተማርናቸው ተማሪዎቻችንን ሁሉ መንግሥት በያሉበት ክፍል ተቀብሎልናል። ይሄን ሃሳብ ያመነጨው ዶክተር ጥበቡ ነበረ።"

ከጤና መኮንን ቡርቃ ሌላ አሥራ አንድ ዓመታት ከጥበቡ ጋር በሶማሊ የቆዩ ሌሎችም

ወገኖቻችን አስገራሚ ትዝታቸውን አካፍለዋል። አንዱ አቶ ንጉሤ ነው። አቶ ንጉሤ ከመማረኩ በፊት ጎዴ ውስጥ የመልሶ ማቋቋም የሰፈራ ጣቢያው ዳይሬክተር ነበር። ውዱ ጥበቡ በልቡ የተወውን ተዝታ እንዲህ ሲል አካፈለን።

"አሥራ አንድ ዓመት በአንድ የመኝታ ቤት አልጋችን አጠገብ ላጠገብ ሆኖ ኖረናል።ዶ/ር ጥበቡ በዚያ እስር ቤት ሁሉ ጤነኛ ምንም ነገር ቢበላ የሚስማማው ሰው ነበረ። እኔ ግን የጨጓራ በሽታ ያመኝ ስለነበር ሐኪሜ እሱ ነበረ። በሕክምናውም ደግሞ ቅድሚያ ለሕመምተኞች ነበር። የተገኘው ነገር ለበሽተኛ ቅድሚያ እንዲሰጥ ይታገል ነበር። ታሞ እንኳ መድኃኒት የማይወስድ ሰው፤ አንዴ ወባ ይዞት ትኩሳት እያዘራቀው እኔና ቡርቃ አስገድደነው ሁለት የወባ ኪኒን ለምንን እንዳስዋጥነው አስታውሳለሁ፣፤ በአምላኩ ላይ የመደገፉ ብዛት አዳነው እንጂ የዋጣትስ ሁለት ኪኒን አረድታው አይደለም። እሱ ናይሮቢ ስለሚሄድ ስላስተማርናቸው ልጆች አደራ አለኝ። "እነዚህ ልጆች ትምህርታቸውን አገር ቤት እንዲቀጥሉ በተቻላችሁ መጠን ከሚመለከታቸው የመንግሥት ባለስልጣናት ጋራ ተነጋገራችሁ ስፍራ እንዲይዙ ተጣጣሩላቸው" ነበር ያለኝ።

****